# كتـــاب التوحيـــد

## الذي هو حق الله على العبيد

### اللغـــة الأمهريـــة (أثيوبيا)

شيخ الإسلام

**محمد بن عبدالوهاب**

إصدار

المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بالمعذر وأم الحمام

تحت إشراف وزارة الشؤون الإسلامية والأوقاف والدعوة والإرشاد

ت: ٤٨٢٦٤٦٦ فاكس: ٤٨٢٧٤٨٩ ص.ب: ٣١٠٢١ ، الرياض: ١١٤٩٧

٢٣

مطابع الحميضي ت 4581000 ف 4592217 الرياض

# ኪታቡ ተውሒድ

ቅንብር፡ ሸይኹል ኢስላም
መሓመድ ቢን ዓብዱልወሃብ

ሂላል ሊሚትድ

Kingdom of Saudi Arabia
The Cooperative Office for call and Guidance
to Communities at Al Ma'azar & Um Al-Hammam
Under the Supervision of the Ministry of Islamic Affairs
Endowment Guidance & Propagation
Tel: 4826466 - Fax: 4827489 - P.O.Box: 31021 Riyadh: 11497

# ኪታቡ ተውሂድ

ቅንብር

ሸይኹል ኢስላም

መሐመድ ቢን አብዱልወሓብ


<u>ተርጓሚና አሳታሚ</u>

ሒላል ሊሚትድ

የመጀመሪያ ዕትም ግንቦት 1990

ሁለተኛ ዕትም ታሕሳስ 1991

160239

አዲስ አበባ


መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| 1. መቅድም ........................................................................ | 1 |
| 2. ሸይኽል ኢስላም መሐመድ ቢን አብዱልዋሐብ አጭር የህይወት ታሪክ........................................................................ | 2 |
| 3. ተውሒድ ........................................................................ | 7 |
| 4. የተውሒድ ጠቀሜታና የሚያስሪያቸው ኃጢአቶች........... | 12 |
| 5. ተውሒድን (ከብክለት) የጠበቀ ጀነትን ይጎናፀፋል............. | 15 |
| 6. ሽርክን መጠንቀቅ ........................................................ | 19 |
| 7. ወደ «ላኢላህ ኢለላህ» ጥሪ ማድረግ ............................... | 21 |
| 8. የተውሂድና የላኢላህ ኢለላህ ትርጓሜ............................ | 25 |
| 9. ጉዳትን ለመከላከል ወይም ለማስቀረት ቀለበትን ማጥለቅ፣ ክርን ማንጠልጠል ወዘተ ከሺርክ ይፈረጃል....................... | 28 |
| 10. ስለ መጠበቂያ (ሩቃ) እና ተማኢም (ሂርዝ) የተነገሩ የሀዲስ ዘገባዎች ......................................................... | 30 |
| 11. በዛፍ፣ በድንጋይና መሰል ግዑዛን መባረክ ...................... | 32 |
| 12. ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት ስለማረድ ............................ | 35 |
| 13. ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት መስዋዕት በሚቀርብበት ቦታ ለአላህ መስዋዕት አይቀርብም ......................................... | 38 |
| 14. ከአላህ ውጭ ላለ አካል መሳል ሽርክ ነው....................... | 40 |
| 15. ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላትን ጥበቃ መሻት ሽርክ ነው........................................................................ | 41 |
| 16. ከአላህ ሌላ ያሉ ኃይላትን መንፈሳዊ እገዛ መሻት (ኢስቲጋሳ) ወይም እነርሱን መማፀን (ዱዓእ) ሽርክ ነው... | 42 |
| 17. ፍጡራን ሊመለኩ አይገባም ............................................ | 45 |
| 18. መለኮታዊ መልዕክት ....................................................... | 48 |
| 19. ምልጃ (ሽፋአ) ............................................................... | 51 |
| 20. አላህ የሚፈልገውን ሰው ወደ ቀጥተኛ መንገድ ይመራል.. | 54 |
| 21. ለሰው ልጆች ክህደትና ዲናቸውን መተው ምክንያቱ ለደጋግ ሰዎች ያላቸው የተጋነነ አመለካከት ነው............. | 56 |
| 22. የአንድን ደግ ሰው መቃብር ማምለክ ይቅርና ከዚያ ሰው ቀብር ላይ አላህን ማምለክ እንኳ በጥብቅ ተወግዟል........................................................................ | 60 |

| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| 23. ለደጋግ ሰዎች ያለን ፅንፈኛ አመለካከት መቃብሮቻቸውን ወደ ሚመለኩ ጣኦታት ይለውጣቸዋል............................ | 64 |
| 24. ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተውሂድን ከብክለት ተከላክለዋል፤ ለሽርክ የሚያበቁ መንገዶችን ሁሉ ዘግተዋል................................ | 66 |
| 25. ከዚህ «ኡምማ» ከፊሉ ጣኦት እስከ ማምለክ ይዘቅጣል.................................................................... | 68 |
| 26. ድግምት ............................................................................ | 72 |
| 27. የድግምት ዓይነቶች ............................................................ | 74 |
| 28. ጠንቋዮችና መስሎቻቸው .................................................... | 76 |
| 29. ድግምትን ስለመሻር (ኑሽረህ)............................................ | 78 |
| 30. በገድ ማመን (ተጠዩር).......................................................... | 79 |
| 31. ኮከብ ቆጠራ (አስተሮሎጅ).................................................... | 82 |
| 32. በጨረቃ እንቅስቃሴ ዝናብን ስለመሻት (አንዋእ)................. | 83 |
| 33. የአላህ ፍቅር .................................................................... | 86 |
| 34. አላህን ብቻ መፍራት ........................................................ | 89 |
| 35. አላህን ብቻ መመካት ........................................................ | 91 |
| 36. ከአላህ ቅጣት መዘናጋት ከተውሒድ ጋር ይቃረናል........... | 93 |
| 37. የአላህን ውሳኔ (ቀደር) በትዕግሥት ማስተናገድ (ሰብር) የኢማን አካል ስለመሆኑ ............................................... | 94 |
| 38. አንድን ተግባር ለታይታ መፈፀም (ሪያእ) ክልክል ስለመሆኑ ................................................................ | 96 |
| 39. አንድ ሰው በመልካም ተግባሩ የዚህችን ዓለም ፀጋ መሻቱ ከሽርክ ይፈረጃል ........................................................ | 98 |
| 40. ዑለሞችንና መሪዎችን አላህ ሐላል ያደረገውን ነገር ሐራም፣ ሐራም ያደረገውን ደግሞ ሐላል ሲያደርጉ መከተል እነርሱን አላህ (ረብ) አድርጎ መያዝ ነው............. | 100 |
| 41. ከአላህና ከመልዕክተኛው ዳኝነት ውጭ የሌሎችን ዳኝነት መሻት መናፍቅነት ነው ................................................ | 102 |
| 42. የአላህን ስሞችና ባህሪያት ስለመካድ................................. | 104 |
| 43. የአላህን ፀጋዎች መካድ ኩፍር ነው .................................. | 106 |
| 44. ለአላህ ባላንጣዎችን አለማበጀት ...................................... | 107 |
| 45. በአላህ ተምሎ የተነገረውን ያልተቀበለ .............................. | 109 |
| 46. «በአላህና በአንተበጎ ፈቃድ» በማለት ስለመናገር................ | 110 |
| 47. ጊዜን መራገም አላህን ማወክ ነው ..................................... | 112 |

| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| 48. «የዳኞች ሁሉ የበላይ ዳኛ» በሚሉና መሰል ስያሜዎች መጠራት ............ | 113 |
| 49. የአላህን ስሞች ስለማላቅና ለዚሁ ሲባል ስምን ስለመቀየር. | 114 |
| 50. በአላህ፣ በመልዕክተኛው ወይም በቁርዓን መቀለድ ............ | 115 |
| 51. «ይህን ገንዘብ ያገኘሁት በጉልበቴና በእውቀቴ ነው» ማለት ከተውሂድ ጋር ይቃረናል............ | 117 |
| 52. ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላትን ማምለክን የሚገልፁ ማናቸውም ዓይነት ስሞች የተወገዙ ናቸው............ | 121 |
| 53. ለአላህ መልካም ስሞችና ባህሪያት አሉት ............ | 123 |
| 54. ለአላህ ሰላምታ ማቅረብ የተከለከለ ነው............ | 124 |
| 55. «አላህ ሆይ! ከፈለግክ ምህረትን ለግሰኝ» ማለት የተከለከለ ስለመሆኑ ............ | 125 |
| 56. «የኔ አገልጋይ» ወይም «ባሪያዬ» ማለት የተከለከለ ስለመሆኑ ............ | 126 |
| 57. በአላህ ስም የጠየቀ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደሚገባው............ | 127 |
| 58. በአላህ ፊት (ክብር) የሚጠየቀው ጀነት ብቻ ስለመሆኑ ............ | 128 |
| 59. ቁጭት ............ | 129 |
| 60. ንፋስን መሳደብ ስለ መከልከሉ ............ | 130 |
| 61. አላህን በክፉ መጠርጠር ስለመከልከሉ ............ | 131 |
| 62. የአላህን ዕቅድና ኘላን (ቀደር) መካድ ............ | 133 |
| 63. ሳዓልያን የሚጠብቃቸው አስከፊ ቅጣት ............ | 136 |
| 64. መሐላን ማብዛት ስለመከልከሉ ............ | 138 |
| 65. ስለአላህና መልዕክተኛው የጥበቃ ቃል ኪዳን (ዚመህ)........ | 140 |
| 66. ከአላህ መብት ጋር የተያያዘ መሐላ............ | 143 |
| 67. አላህ ወደ ፍጡራኑ ባማላጅነት (ሸፊዐ) አይላክም............ | 144 |
| 68. ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ለተውሂድ ጥብቅና መቆማቸውና የሽርክን መንገዶች ሁሉ መዝጋታቸው............ | 145 |
| 69. ለአላህ ተገቢውን ክብር አልሰጡም............ | 147 |

# መቅድም

ኪታቡ ተውሒድ በታላቁ ዳዒ እና የተሐድሶ አራማጅ (ሙጀዲድ) በሸይኹል ኢስላም ሙሐመድ ኢብን አብዱል ዋሐብ ከምዕተ ዓመታት በፊት ተከትቦ ለንባብ የዋለ እውቅ የተውሒድ መጽሐፍ ነው:: በየዘመናቱ በመላው ዓለም ተቀባይነትን አግኝቷል:: የበርካታ ሠዎችን ህይወት ለውጧል:: እምነትና አመለካከታቸውን ፈር አስይዟል:: በሚሊዮኖች ላይ ተጽእኖውን አሳድሯል:: አሁንም የብዙዎችን ህይወት በመለወጥ ላይ ነው::

አቂዳ (ተውሒድ) አብይ የኢስላም ክፍል እንደመሆኑ እምነትና አመለካከትን ቁርዓንና ሐዲስ በሚሹት መልኩ ለመቅረጽና የሠለፎችን የአስተሣሠብና የአኗኗር ስልት በመከተል በዚህችም ሆነ በቀጣዩ አለም ለስኬት ለመብቃት የእኒህ ታላቅ ዳዒ እውቅ መጽሐፍ የሆነው «ኪታቡ ተውሒድ» ጠቃሚነቱ አጠያያቂ አይደለም::

መጽሐፉ ካለው ጠቀሜታና በአገራችን እያገኘ ከመጣው እውቅና አንፃር ወደ አማርኛ መልሠነው ህዝባችንን የእኒህ ታላቅ የተውሒድ ሠው የእውቀት ማዕድ ተቋዳሽ ብናደርግ የላቀ ፋይዳ እንደሚኖረው ተሰማን:: እናም ለትርጉም አበቃነው::

የአረብኛ መጽሐፍትን ወደ አማርኛ መመለስ እጅግ አስቸጋሪና ፈታኝ ተግባር ነው:: ቢሆንም ግን የፀሐፊውን ስሜት፣ መልዕክትና አመለካከት ሳናዛባ እንዳለ ለአንባቢያን ለማቅረብ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል::

ስራችን ከስህተት የራቀ፥ ከግድፈት ያተጠበቀ ነው ለማለት አንደፍርም :: የማይሳሳት አላህ ብቻ ነውና::

ስህተቶችን ፈፅመን ሊሆን ይችላል:: እናም የአንባቢያን የእርምት አስተያየት በእጅጉ ያስፈልገናል:: ወደፊት ለንባብ የምናውላቸውን ሥራዎቻችንን በተሻለ ጥራት ለማቅርብ ይረዳናል::

አስጀምሮ ላስጨረሰን አላህ ምስጋና ይገባው::

***ሒሳል ቢሚትድ***

# ሸይኹል ኢስላም መሐመድ ቢን አብዱል ዋሐብ
# ዕውቅ ሐዳሲ

## ውልደት

ሸይኹል ኢስላም መሐመድ ቢን አብዱልዋሐብ በ1115 ሒጅሪያ ከሪያድ 70 ኪሎ ሜትር ርቃ በምትገኘው ኡያይናህ ከተማ ተወለዱ:: ቤተሠቦቻቸው የተከበሩና በዒልም እውቀታቸው ታዋቂ ነበሩ:: አባታቸው ሸይኽ አብዱልዋሐብ ቢን ሱለይማን በጥልቅ የእውቀት ምንጭነታቸው፣ በመልካምና ሰናይ ምግባራቸው፣ በማራኪ ባህርያቸው፣ ለኢስላም በሚከፍሉት መስዋዕትነት የታወቁ ነበሩ::

## ትምህርት

ሸይኹል-ኢስላም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በመንደራቸው ከአባታቸው ያገኙ ሲሆን በ10 ዓመታቸው ቁርዓንን መሐፈዝ ችለዋል:: ከዚሁ ጎን ገና በዚያ ለጋ እድሜያቸው በተለያዩ ዓሊሞች የተጻፉትን የተፍሲር፣ የሐዲስ እና ፊቅህ ሥራዎችን ያጠኑ፣ ያገናዝቡ ነበር::

ከቀደምት ምሁራን የሸይኹል ኢስላም ኢብን ተይሚያህና ተማሪያቸው አልላመህ ኢብኑል ቀይም ስራዎች የበለጠ ተፅእኖ አሳድረውባቸዋል::

ለአቅመአዳም ሲደርሱ ወደ መካ በመሔድ ሐጅ አደረጉ:: በዚህ የመካ ቆይታቸው በቦታው ከሚገኙ ዓሊሞች አያሌ ዕውቀቶችን ቀስመዋል:: ጉዞአቸውን በመቀጠል መዲናንም ጎብኝተዋል:: በታዋቂዎቹ ሸይኽ አብደላህ ቢን ኢብራሒም ቢን ሰዒድ ነጅዲና ሸይኽ ሙሐመድ ሐያት ሲንዲ ስር ለረጅም ጊዜ ተምረዋል:: ለዕውቀት የነበራቸውን ጥማት ለማርካት ባለመቻሉ አስቸጋሪው የበረሐ ጉዞ እያንገላተቸው ወደ ኢራቅና በስራ ተጉዘው ከከተሞቹ የዒልም (የዕውቀት) ምንጭ ተጎንጭተዋል::

# የነጅድ ሁኔታ

በዚያ ዘመን የነጅድ ህዝቦች ከኢስላም ውጭ የሆኑ ተግባራት ውስጥ ተዘፍቀዋል፡፡ ኢስላም ለህዝቦቹ የፈነጠቀው ንፁህ ያልተበረዘ አሐዳዊ እምነት በተለያዩ ሠብዓዊ እጆች ተከልሷል፡፡ መቃብሮች፣ ዛፎች፣ ድንጋዮች፣ ዋሻዎች የሙት መንፈሶች የማይገባቸውን አምልኮ ተጎናፅፈዋል፡፡ መሠረተ-ቢስ ተረቶችና ፈጠራዎች የነዚህን አካላት ማንነት ለማጎን ይፈጠራሉ፤ ይነዛሉ፤ ከትውልድ ትውልድ ይወራረሳሉ፡፡ ጠንቋዮች እና አስማተኞች በህብረተሰቡ ላይ ይህ ነው የማይባል ተፅእኖ አሳድረዋል፡፡

በተራው ህዝብ ላይ የዘረጉትን ድር ለመበጣጠስ ደፍሮ የሚነሣ አንዳችም ሠው አልነበረም፡፡ በመካ፣ መዲና፣ የመንም ተንሰራፍቶ የነበረው ሁኔታ ከላይ ከተጠቀሰው የተለየ አልነበረም፡፡

# የዳዕዋው ተልዕኮ

የሙስሊሙን ኡማ አሳዛኝ ሁኔት የተረዱትና ያንገፈገፋቸው ሸይኽ ህዝቡን ወደ ቀጥተኛው ጎዳና ለመመለስ ቆርጠው ተነሱ፡፡ ይህንን ዓላማ ይዞ መነሣት ማለት በተንሠራፋው ፈሳድ ውስጥ እጃቸውን ያለበትንና የጥቅሙ ተቋዳሽ ከሆኑት አካላት ጋር ፍጥጫና ትግል መፍጠር መሆኑን ጠንቅቀው ተረድተዋል፡፡ ሸይኽ ሙሐመድ አብዱልዋሐብ ከፊት ለፊታቸው ከተጋረጡት ሐይሎች የሚደርስባቸው ጥቃት ምን ያህል ሊሆን እንደሚችል ያለ አንዳች ጥርጥር ገብቷቸዋል፡፡ ነገር ግን ሸይኹ ይህንን ታላቅ ኃላፊነት ለመሸከም ቆርጠው ተነስተዋልና ወደኋላ የሚመልሳቸው ሐይል ከቶም ሊኖር አልቻለም፡፡

ተልዕኳዋቸውን ጀመሩ፡፡ ሰዎችን ወደ ተውሒድ መጥራት፡፡ ሰዎች ወደ ቁርዓንና ሱና ፊታቸውን እንዲያዞሩ ጥሪ ማድረግን ተያያዙት፡፡ የሙስሊሙ ማህበረሰብ ቁርዓንና ሱናን ወደ ጎን ትቶ ዓሊሞችን በጭፍኑ መከተልን እንዲያቆም ምክራቸውን ለገሱ፡፡ የአላህ መፅሐፍና የረሱል ሱና ተገቢውን ቦታ ዳግም እንዲጎናፀፍ ታገሉ አታገሉ፡፡ ሸይኹ በከፍተኛ ጉጉትና ፅናት ነበር ትምህርት የሚለግሱት፡፡ ከብዙ ምሁራን ጋር ግንኙነት ፈጠሩ፡፡ በጋራ ለመስራትም ጋበዟቸው፤ በወቅቱ ተንሰራፍቶ የነበረውን ሽርክና ቢድአ ጠራርጎ ለማጥፋት፡፡ ከመካ፣ ከመዲናና ከየመን

በርካታ ምሁራን ጥሪያቸውን በመቀበል ድጋፋቸውን ለገሷቸው:: ለግላዊ ስሜትና አመለካከት ተገዢ በመሆን ድጋፍ የነፈጓቸው፡ ብሎም በፅኑ የተቃወሟቸው ምሁራንም ነበሩ:: ይህ ሁሉ ሆኖ ሸይኹ ዳእዋቸውን ስህተት ውስጥ ለተዘፈቀው ማኅበረሰብ ለማዳረስ ከቦታ ቦታ በትጋት ይንቀሳቀሱ ነበር:: በርካታ ቦታዎችን ካሰሱ በኋላ በመጨረሻ ዑየይነህ ደረሱ::

## ዑየይነህ መግባታቸው

በጊዜው የዑየይነህ ገዢ ዑስማን ቢንሐምድ ቢንማማር ነበር:: ሸይኹን በመልካም ሁኔታ ተቀበላቸው:: ለዚህ ኢስላማዊ ዳእዋ እንቅስቃሴያቸው የቻለውን ድጋፍ ሁሉ እንደሚያደርግ ቃል ገባላቸው::

ሸይኹ ባገኙት ድጋፍ በመበረታታት የእንቅስቃሴ አድማሳቸውን እያሠፉ ሔዱ:: ሌት ተቀን ሳይሉ ጥረው ግረው ተውሒድን መልሶ ለማቆም ሠሩ:: የስራቸው ውጤት መታየት ሲጀምር ብዙም አልቆየም:: በሺህዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከየአቅጣጫው በንፁህ ኢስላማዊ ትምህርቶች ልባቸው መማረክ ጀመረ:: ዳዕዋው ፍሬ መስጠት ጀመረ:: ከኡያይና ርቀው በሚገኙ አካባቢዎችም ፀረ-ኢስላም ዝንባሌዎች እንደ ገለባ እየተጠራረጉ ሔዱ::

## ኡያይናህ ወደ ዳሪያህ ስደት

የአል አህሳና አካባቢዋ ገዢ ሱለይማን ቢን ኡራይደር ስለ ሼይኹ ተወዳጅነትና ዕውቅና ማደግ ሲሰማ እንቅስቃሴውን በእንጭጩ ለመቅጨት ቆርጦ ተነሣ:: በመሆኑም አሚር ኡስማን ሸይኹን እንዲገለው ትዕዛዝ ያስተላልፋል:: አሚር ኡስማን የሱለይማንን ሐያልነት በመፍራት ጉዳዩን ለሸይኹ ያዋያቸዋል:: ሸይኹ ወደ ዳሪያህ እንዲሰደዱ ይስማማሉ በስተመጨረሻ::

የዳሪያህ ገዢ አሚር መሃመድ ቢን ሳዑድ ና የግዛቱ ህዝብ ለሸይኹ ከፍተኛ አቀባባል አደረጉላቸው:: የሙስሊሙን ህብረተሰብ ባህላዊ ሽርክ በማሠብና ቁርዓንና ሐዲስን መልሶ ወደ ህዝቡ ህይወት በማስረግ ምኞት ይብሰለሰሉ የነበሩት አሚር ሳዑድ አጋጣሚው አስደሰታቸው:: ስለኢስላም መርሆዎች በሠፊው ተወያዩ:: የረሱልን የዳዕዋ ስልት አንስተው አካሄዳቸውን ቀየሱ::

የእውነትን የበላይነት ለማረጋገጥ ጅሃድን ለመጀመር ወሰኑ:: በጋራ የሺርክ ሠራዊትን ጠራርጎ ለመጣል በአላህ ፊት ቃል ተገባቡ::

## ዳሪያህ-የዳዕዋ ማዕከል

ሸይኹ በዳሪያህ ባገኙት ሠላምና መረጋጋት አመቺ ሁኔታ በመጠቀም ኢስላምን ለህዝቡ ማስተማራቸውን ተያያዙት:: ህዝብ ይጎርፉል:: ከዳሪያ ብአራቱም አቅጣጫ በየቀኑ ለትምህርት የሚደርሰው ህዝብ ከተማዋን አጨናነቃት:: አሚርሙሐመድ ኢብን ሳዑድም ከቤተሰቦቻቸው ጋራ በመሆን ከተማሪዎቹ አንዱ ነበሩ:: ሸይኹ ደከመኝ ታከተኝ ሳይሉ ዳዕዋውን እስከ አለም ጥግ ለማድረስ ሌት ተቀን ሠሩ:: በተለያዩ የኢሰላም ቅርንጫፎች ወዘተ... ላይ ትምህርታቸውን በጥልቅ ሰጡ:: ዳሪያህ የመማሪያና የዳዕዋ ማዕከል ሆነች::

ህዝቦች ሲታለሉበት የነበረው ዝንባሌ እርግፍ አድርገው ልባቸውን ለሸይኹ መርሆዎች ከፍተው ማስረከባቸው፣ ለሸይኹ ከፍተኛ ፍቅር ማዳበራቸው፣ የሸይኹ ጠላቶች ጥላቻቸው እያደገ እንዲሄድ አደረገ:: የቅናት ዛር በብዙዎች ላይ ሠፈረ:: አስማተኛ፣ ዚንዲቅ፣ ወዘተ በሚል ስማቸውን ለማጥፋት ተሞከረ::

ከተቃዋሚዎች የሚደርሰባቸውን ዘለፋ ግን ሸይኹ ይመልሱት የነበረው ትህትና በተሞላበትና ግራሞትን በሚያጭር ሰናይ ባህሪይ ነበር:: በርግጥም ይህ አቀራረብ በተለያዩ አጋጣሚዎች ጥሩ ውጤት ማፍራት ችሏል::

ወደ ዳሪያህ በመምጣት ከሸይኹ የጠለቁ ዒልም ቀስመው የተመለሱ ዳዒዎች ወደ የክልላቸው በመሔድ ዳዕዋውን በፅናት ማራመድ ጀመሩ:: ዳዕዋው እንደ ሠደድ እሳት በአረቢያ ምድር ተዛመተ:: በተወሰኑ አካባቢዎች በሚገኙት የሽክር ይዞታዎች ላይ የጅሐድ ጦርነት እንዲከፈት የሚፈለገው ግፊት ጠነከረ::

## ከገዢዎች ጋር የሐሳብ ልውውጥ

ወቅቱ እየገፋ ሔደ:: የሸይኹል- ኢስላም ልፋት ፍሬ እየሠጠ መጣ:: በየክልሉ በየአቅጣጫው የተሰባጠሩት ገዛቶች መሪዎችና ዓሊሞች ህዝቡ የተዘፈቀበትን ሽርክ ትኩረት እንዲሰጡት ማድረግ ቻሉ- ሸይኽ መሃመድ አብዱል ዋሐብ::

ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በየአቅጣጫው መልዕክቶችን መላክ የጀመሩት:: በነጅድ፣ ሪያድ፣ ኸርጅ፣ ቃሲም፣ ሐይል፣ ዋሽም ሱዳይር እና በሌሎችም አካባቢ ለሚገኙ ሠዎች ደብዳቤዎችን ልከዋል:: ከአረብያ ሠላጤ ውጭ ለሚገኙ ኡለማዎች ደብዳቤ ልከዋል፤ ለኢራቅ፣ ሶርያ፣ ህንድ፣ የመን ወዘተ::

የሸይኹ መልዕክት በየአቅጣጨወ ተስፋፋ:: በህንድ፣ ኢንዶኔዥያ፣ አፍጋኒስታን፣ አፍሪካ፣ ሞሮኮ፣ ግብጽ፣ ሶሪያ፣.... አካባቢ የሚገኙ ዓሊሞች በሸይኹ ትምህርቶች በጥልቅ ተማረኩ:: ህዝቦቻቸውን ወደ ቁርዓንና ወደሱና ብቻ ጠሩ::

## ህልፈት

ሸይኹ ህይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለዳዕዋው መሳካት ሰጥተው ኖረዋል:: ከዳሪያህ ገዢዎች ከሙሐመድ ብን ሳዑድ እና ከልጁ አብዱልአዚዝ ባገኙት እርዳታ በመታገዝ እስከመጨረሻ እስትንፋሳቸው ታገሉ:: በ1206 (1792 ) ሒጅሪያ በወርሃ ዙል ቂዕዳ ለሁሉም ፍጡራን የተወሰነለትን የሞት ጽዋ ተጎነጩ:: አላህ ይዘንላቸው::

# ምዕራፍ አንድ
## ተውሒድ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴾

*«ጋኔንንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጅ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም።» (አል-ዛሪያት :56)*

﴿ وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِى كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولًا أَنِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَٱجْتَنِبُوا۟ ٱلطَّٰغُوتَ ﴾

*«በየህዝቡ ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ፤ ጣኦታትንም ራቁ በማለት መልዕክተኞችን ልከናል።» (አል-ነህል:36)*

﴿ وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَٰنًا ۚ إِمَّا يَبْلُغَنَّ عِندَكَ ٱلْكِبَرَ أَحَدُهُمَآ أَوْ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل لَّهُمَآ أُفٍّ وَلَا تَنْهَرْهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوْلًا كَرِيمًا ۝ وَٱخْفِضْ لَهُمَا جَنَاحَ ٱلذُّلِّ مِنَ ٱلرَّحْمَةِ وَقُل رَّبِّ ٱرْحَمْهُمَا كَمَا رَبَّيَانِى صَغِيرًا ۝٢٤

*«ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ:- እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤በወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፤ በአንተ ዘንድ ሆነው አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላቸው፤ አትገላምጣቸው፤ መልካምን ቃል ተናገራቸው። ለሁለቱም ከእዝነትህ የመዋረድን ክንፍ ዝቅ አድርግላቸው፤ ጌታዬ ሆይ ዐህፃንነቴ (በርህራሄ) እንዳሳደጉኝ እዘንላቸውም በል።» (አል-ኢስራእ:23- 24)*

﴿ وَٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا۟ بِهِۦ شَيْـًٔا ﴾

*«አላህንም ተገዙ፤ በርሱ ምንንም አታጋሩ፤» (አል-ኒሳእ:36)*

﴿ قُلْ تَعَالَوْا۟ أَتْلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمْ عَلَيْكُمْ ۖ أَلَّا تُشْرِكُوا۟ بِهِۦ شَيْـًٔا ۖ وَبِٱلْوَٰلِدَيْنِ إِحْسَٰنًا ۖ وَلَا تَقْتُلُوٓا۟ أَوْلَٰدَكُم مِّنْ إِمْلَٰقٍ ۖ نَّحْنُ نَرْزُقُكُمْ وَإِيَّاهُمْ ۖ وَلَا تَقْرَبُوا۟ ٱلْفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنْهَا وَمَا بَطَنَ ۖ وَلَا تَقْتُلُوا۟ ٱلنَّفْسَ ٱلَّتِى حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلْحَقِّ ۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ۝ وَلَا تَقْرَبُوا۟ مَالَ ٱلْيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِى هِىَ

أَحۡسَنُ حَتَّىٰ يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۖ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ لَا نُكَلِّفُ نَفۡسًا إِلَّا وُسۡعَهَاۖ وَإِذَا قُلۡتُمۡ فَٱعۡدِلُواْ وَلَوۡ كَانَ ذَا قُرۡبَىٰۖ وَبِعَهۡدِ ٱللَّهِ أَوۡفُواْۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ۝ وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِي مُسۡتَقِيمًا فَٱتَّبِعُوهُۖ وَلَا تَتَّبِعُواْ ٱلسُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمۡ عَن سَبِيلِهِۦۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ﴾

*«ኑ፤ በእናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር (በእርሱ ያዘዛችሁን) ላንብብላችሁ በላቸው፤ በእርሱም (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ፤ በወላጆችም በጐን ሥራ ሥሩ፤ ልጆቻችሁንም ከድህነት ፍራቻ አትግደሉ፤ እኛ እናንተንም እነርሱንም እንመግባችኋለንና፤ መጥፎ ሥራዎችንም ከእርሷ የተገለጸውንም የተደበቀውንም ሁሉ አትቅረቡ፤ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በሕግ ቢሆን እንጂ አትግደሉ፤ ይሃችሁ፣ ታውቁ ዘንድ (አላህ) በእርሱ አዘዛችሁ:: የየቲምንም ገንዘብ ብርታቱን (አካለ መጠን) እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በኾነች ኩኔታ እንጅ አትቅረቡ፤ ስፍርንና ሚዛንንም በትክክሉ ሙሉ፤ ነፍስን ችሎታዋን እንጂ አናስገድድም፤ በተናገራችሁም ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢሆንም እንኳ (እውነትን በመናገር)አስተካክሉ:: በአላህም ቃል ኪዳን ምሉ:: ይኻችሁ ትገሠጹ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ::» (አልአንዓም:151-153)* ኢብኑ መስዑድ እንዲህ ሲሉ መናገራቸው ተዘግቧል:-

«مَنْ أَرَادَ أَنْ يَنْظُرَ إلى وَصِيَّةِ مُحَمَّدٍ ﷺ التي عَلَيْها خَاتَمه فَلْيَقرَأْ قولهُ تعالى: ﴿ قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـًٔاۖ - إلى قوله - وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِي مُسۡتَقِيمًا﴾ .

*«ማህተማቸው ያረፈበትን የሙሐመድን (ሰ.ዐ.ወ) የኑዛዜ ቃል መመልከት የፈለገ:- ኑ፤ በእናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገር (በእርሱም ያዘዛችሁን) ላንብብላችሁ ብላቸው፤ በእርሱም (በአላህ) ምንንም ነገር አታጋሩ... »(አል አንዓም: 151-153) የሚለውን ቃል ያንብብ::»*

ሙአዝ ኢብን ጀበል (ረዐ) እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

«كُنْتُ رَدِيفَ النَّبيِّ ﷺ عَلَى حِمَارٍ فَقَالَ لِي، يَا مَعَاذُ! أَتَدْرِي مَا حَقُّ الله عَلَى العِبَادِ ومَا حَقُّ العِبَادِ عَلى الله؟ قُلْتُ الله وَرَسُولُه أعْلَمُ، قَالَ حَقُّ الله عَلَى العِبَادِ أَنْ يَعْبُدُوهُ وَلا يُشْرِكُوا بِهِ شَيئاً، وحَقُّ العِبَادِ عَلَى الله أَنْ لا يُعَذِّبَ مَنْ لا يُشْرِكُ بهِ

شَيئاً. قُلتُ: يَا رَسُولَ اللهِ! ﷺ أفَلا أُبَشِّرُ النَّاسَ؟ قَالَ: لاَ تُبَشِّرْهُم فَيَتَّكِلُوا».

«ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር በአንድ አህያ ላይ ከበስተኋላ ተሳፍሬ ተቀምጬአለሁ:: «ሙአዝ ሆይ! አላህ በባሮቹ ላይ ሰዎች ደግሞ በአላህ ላይ ስላላቸው መብት ታውቃለህን?» ሲሉ ጠየቁኝ:: «አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ» አልኳቸው:: «አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት እርሱን ብቻ ሊያመልኩና በርሱ ላይ ምንንም ኃይል ላያጋሩ ነው፤ ሰዎች በአላህ ላይ ያላቸው መብት ደግሞ በእርሱ ላይ ሌላን ኃይል ከማሻረክ ሃጢአት የፀዱ እስከሆኑ ድረስ ላይቀጣቸው ነው» አሉ:: «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የዚህን መልካም ዜና ብስራት ለሰዎች ልንግራቸው?» አልኳቸው:: «ብስራት አትንገራቸው፤ ይሳነፋሉና» አሉኝ::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የሰው ልጅና አጋንንት የተፈጠሩለት አላማ ተገልጿል::
2. አምልኮት (ኢባዳ) ተውሒድ ነው:: ሰዎች ከፍተኛ ተቃውሞ የሚገጥማቸው በተውሂድ፥ማለትም ተውሒድን ሊኖሩት ሲሞክሩ ነውና::
3. ተውሂድ የሌለው ሰው አላህን ፈፅሞ አላመለከም::

﴿وَلَآ أَنتُمْ عَٰبِدُونَ مَآ أَعْبُدُ﴾

*«እኔ የምገዛውን ተገዥዎች አይደላችሁም::» (አል ካፊሩን :3)*

የሚለው ቁርአናዊ ቃል ትርጓሜ ይኸው ነው::

4. መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የመላካቸው ጥበብ፣ አላማና ግብ ተብራርቷል::
5. እያንዳንዱ ህዝብ (Nation/ ኡመህ) መለኮታዊ መልዕክት ደርሶታል::
6. የነቢያት ሁሉ ዲን አንድና አንድ ብቻ ነው::
7. በጣኦት መካድ እስካልተረጋገጠ ድረስ አላህን ማምለክ(ኢባዳ) እውን ሊሆን አይችልም::

﴿فَمَن يَكْفُرْ بِٱلطَّٰغُوتِ وَيُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسْتَمْسَكَ بِٱلْعُرْوَةِ ٱلْوُثْقَىٰ﴾

*«በጣኦታት የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ለእርሷ መበጠስ የሌላትን ጠንካራ ዘለበት በእርግጥ ጨበጠ።» (አል-በቀራህ፥ 256)*

የሚለው ቁርአናዊ ቃል ይህንኑ በጉልህ ያሣያል። እጅግ ጠቃሚ ነጥብ ነው።

8. ከአላህ ሌላ ያለ ማንኛውም የሚመለክ ኃይል ሁሉ ጣኦት ይባላል።

9. ከአልአንዓም ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱ ሦስት የማያሻሙ (ሙሕከማት) የቁርአን አናቀፅ ከሰለፎች ዘንድ እጅግ የላቀ ትኩረት ይቸራቸው ነበር። አሥር ጠቃሚ ነጥቦችን አዝለዋል። የመጀመሪያውና ዋነኛው ሽርክን ማቀብ ነው።

10. በአል ኢስራዕ ምዕራፍ ላይ የሰፈሩ «ሙሕከማት» የቁርአን አንቀፆች ሊጤኑ ይገባል። 18 ጠቃሚ ነጥቦችን አካተዋል። አላህ:-

﴿ لَّا تَجْعَلْ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَتَقْعُدَ مَذْمُومًا مَّخْذُولًا ﴾

*«ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ፤ የተወቀስክ ትሆናለህና» (አል- ኢስራዕ :22)*

በማለት ጀምሮ

﴿ وَلَا تَجْعَلْ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَتُلْقَىٰ فِي جَهَنَّمَ مَلُومًا مَّدْحُورًا ﴾

*«ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ፤ የተወቀስክ ፥ የተባረርክ ሆነህ በገሃነም ውስጥ ትጣላለህና።» (አል-ኢስራዕ :39)*

ሲል ቋጭቷቸዋል።

የነኝህን ነጥቦች ክብደትና የላቀ ጠቀሜታ ሲገልፅ:-

﴿ ذَٰلِكَ مِمَّآ أَوْحَىٰٓ إِلَيْكَ رَبُّكَ مِنَ ٱلْحِكْمَةِ ﴾

*«ይህ ጌታህ ከጥበብ ወደ አንተ ካወረደው ነገር ነው።» (አል-ኢስራዕ :39) ብሏል።*

11. በአል ኒሳዕ ምዕራፍ ላይ የሰፈሩት አስር አናቅፅ ትኩረት ሊቸራቸው ይገባል። አሥሮቹ የመብት አናቀፅ (አያተል ሁቁቅ አል-ዐሽረህ) በመባል ይታወቃሉ።

﴿ وَٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ وَلَا تُشْرِكُوا۟ بِهِۦ شَيْـًٔا ﴾

*«አላህን ብቻ አምልኩ፤ በርሱ ላይ ምንንም አታጋሩ::» (አልኒሳዕ: 36)*

በሚል ይወጠናሉ::

12. የአላህ መልዕክተኛ ለህልፈት በተቃረቡበት ወቅት ያስተላለፏቸው ኑዛዜዎች::

13. አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት::

14. ሰዎች የአላህን መብት እስካከበሩ ድረስ በአላህ ላይ ሊኖራቸው የሚችለው መብት::

15. የመጨረሻውን እጅግ ጠቃሚ ነጥብ አብዛኛዎቹ የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች አያውቁትም ነበር::

16. ጠቃሚ ለሆነ ዓላማ ዕውቀትን መደበቅ ይፈቀዳል::

17. በሙስሊሞች ልቦና ውስጥ ደስታን መርጨት ሊሰጠው የሚገባው ከፍተኛ ክብደት::

18. የአላህን ወደር የለሽ እዝነትና ርኅራሄ በመተማመን ከተግባር መዘናጋት (ኢትቲካል) አግባብ አይደለም::

19. አንድ ሰው ስለማያውቀው ነገር ሲጠየቅ አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ በማለት መመለሱ ተገቢው ነው::

20. አንድን የዕውቀት ዓይነት ለተወሰኑ ሰዎች ብቻ ለይቶ መስጠት ይፈቀዳል::

21. የመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ትህትና የተሞላበት ባህሪ፤ ከባልደረቦቻቸው ጋር በአንድ አህያ ላይ ተፈናጠው ይጓዙ ነበር::

22. ከብትን ከአንድ በላይ ሆኖ መጋለብ ይፈቀዳል::

23. እነኝህ ነጥቦች እጅግ የላቀ ክብደት የሚሰጣቸው ናቸው::

# ምዕራፍ ሁለት
## የተውሒድ ጠቀሜታና የሚያስረያቸው ኃጢአቶች

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَلَمْ يَلْبِسُوٓاْ إِيمَـٰنَهُم بِظُلْمٍ أُوْلَـٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلْأَمْنُ وَهُم مُّهْتَدُونَ﴾

*«እነዚያ ያመኑትና እምነታቸውን በበደል (ሽርክ) ያልበከሉ ለነርሱ ሰላም አላቸው፤ እነርሱ የተመሩ ናቸው::» (አል-አንዓም :82)*

ዑባዳት ኢብን ሷሚት (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል:-

«مَنْ شَهِدَ أنْ لا إلـهَ إلاَّ الله وَحْدَهُ لاَ شَرِيكَ لَهُ وأنَّ مُحَمَّداً عَبْدُهُ ورَسُولُه، وأنَّ عِيسى عَبْدُ الله ورَسُولُه وَكَلِمَتُه أَلْقاهَا إلى مريمَ وَرُوحٌ مِنْهُ والجَنَّةُ حَقٌّ والنَّارُ حَقٌّ أدْخَلَهُ الله الجَنَّةَ عَلى مَا كَان مِنَ العَمَل.

*«አላህ አጋር የለሽ ብቸኛ አምላክ መሆኑንና ሙሐመድ ደግሞ መልዕክተኛውና ባሪያው መሆናቸውን የመሰከረ፤ዒሳ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ፣ እንዲሁም ወደ መሪም የጣለው ቃሉና መንፈሱ መሆኑን ያፀደቀ፤ ጀነትና እሳት እውነት እንደሆኑ ያመነ፣ ስናይ ምግባሩ የቱን ያህል ኢምንት ቢሆንም አላህ ጀነትን ይለግሰዋል::» (ቡኻሪና ሙስሊም)*

በኻሪና ሙስሊም ዑትባንን ጠቅሰው ባሰፈሩት ሌላ ዘገባ እንደተወሳው የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«فإنَّ الله حَرَّمَ عَلَى النَّارِ مَنْ قَالَ: لاَ إلـهَ إلاَّ الله يَبْتَغِي بِذَلِكَ وَجْهَ الله»

*«የአላህን ውዴታ፣ ምንዳና ቀረቤታ በመሻት ላኢላሃ ኢለላህ ያለ ሰው አላህ ከእሳት ነፃ አውጥቶታል::» ብለዋል::*

አቡ ሰዒድ አል ኹድሪይ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል:-

«قَالَ مُوسَى يَا رَبِّ عَلِّمْنِي شَيئاً أذْكُرُكَ وأدْعُوكَ بِهِ قالَ يَا مُوسَى لا إلـهَ إلاَّ الله. قالَ يَا رَبِّ! كُلُّ عِبادِكَ يَقُولونَ هذَا قَالَ

يَا مُوسى: لَوْ أَنَّ السَّمٰوَاتِ السَّبْعَ وَعَامِرَهُنَّ غَيْرِي وَالأَرْضِينَ السَّبْعَ فِي كَفَّةٍ وَلاَ إِلٰهَ إِلاَّ الله فِي كَفَّةٍ مَالَتْ بِهِنَّ لا إِلٰهَ إِلاَّ الله».

«ሙሳ (ዐሰ):- «ጌታዬ ሆይ! አንተን የማወሳበትንና የምማፀንበትን ቃል አስተምረኝ» ሲሉ አላህን ጠየቁ:: «ላኢላሀ ኢለላህ በል» አላቸው:: «ጌታዬ ሆይ! ይህማ ሁሉም ባሮችህ የሚሉት ነው፣ (ከዚህ የተለየ ነገር እሻለሁ)» አሉ:: «ሰባቱ ሰማያትና ከውስጣቸው ያሉትም፣ ሰባቱ ምድሮችም በአንድ ሚዛን ላይ ቢቀመጡና ላኢላሃ ኢለላህ ደግሞ በሌላ ሚዛን ላይ ቢቀመጥ ላኢላሃ ኢላላህ ሚዛን ደፍቶ ይገኛል::» አላቸው::» (ኢብ ሒባንና ሐኪም ዘግበውታል:: ሶሒሕ መሆኑንም አፅድቀዋል::)

ቲርሚዚ ሐሰን በሆነ ሰነድ እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ እንድምጫለሁ በማለት አነሰ(ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«قال الله عَزَّ وجَلَّ: يَابنَ آدَمَ لَوْ أَتَيتَنِي بِقُرَابِ الأَرْضِ خَطَايَا ثُمَّ لَقِيتَنِي لا تُشْرِكُ بِي شَيئاً لأَتَيْتُكَ بِقُرَابِهَا مَغْفِرَةً».

«አላህ:- <የአዳም ልጅ ሆይ! ምድርን የሚሞላ ሐጢአት ተሸክመህ ከኔ ዘንድ ብትመጣ በኔ ላይ ሌላ ኃይልን እስካላጋራህ ድረስ ምድርን የሚሞላ ምህረት ይዤ እጠብቅሐለሁ» ሲል አውጇ::>

## <u>ጠቃሚ ነጥቦች</u>

1. የአላህ እዝነትና ትሩፋት ስፋትና ጥልቀት::
2. የተውሒድ ምንዳ ከአላህ ዘንድ እጅግ የበዛ መሆኑ::
3. ተውሂድ በሽርክ እስካልተበከለ ድረስ ወንጀል ሁሉ የመማር ዕድል ይኖረዋል:
4. የአንቀፅ «አል-አንዓም :72» ትርጉም::
5. ዑባዳህ ካስተላለፉት የሐዲስ ዘገባ ውስጥ የሰፈሩት አምስት ጠቃሚ ነጥቦች::
6. ዑባዳህ ያስተላለፉትን ዘገባ ዑትባን ካስተላለፉትና ከዚያም በኋላ ከተወሰት ዘገባዎች ጋር በማጣመር የላኢላሃ ኢለላህን ትክክለኛ ትርጓሜ መረዳት ትችላለህ:: አንዳንድ የዋሆች ዑትባን ያስተላፉትን ዘገባ በመረዳቱ ረገድ የሚፈፅሙት የጎላ ስህተትም ግልጽ ይሆንልሃል::

7. በዑትባን ከተላለፈው ዘገባ ውስጥ የተጠቀሰው መስፈርት (ሸርጥ) ትኩረት ይሻል::

8. ነብያት የላኢላሃ ኢለላህን ጥቅምና ትሩፋት የሚያስታውሳቸው አካል ይሻሉ::

9. የላኢላሃ ኢለላህ ክብደት ተወስቷል:: ከፍጡራን ሁሉ ትልቃለች:: አብዛኛዎቹ በአፋቸው የሚሏት ወገኖች ግን አቅልለው ይመለከቷታል::

10. ምድሮችም፣ ሰማያትም ቁጥራቸው ሰባት እንደሆነ ተወስቷል::

11. ሰባቱ ሰማያት ነዋሪዎች እንዳሏቸው ተወስቷል::

12. የአላህን ባህሪያት (ሲፋት) ቁርአን ውስጥ በተጠቀሱበት መልኩ ያለምንም ተጨማሪ ትርጉም እንዳሉ መቀበል ግዴታ ነው::

13. አነስ (ረዐ) ያስተላለፉትን ዘገባ በሚገባ ከተረዳን ዑትባን ያስተላለፉት ሃዲስ መልዕክት ግልፅ ይሆንልናል:: የአላህን ውዴታ፣ ምንዳና ቀረቤታ በመሻት «ላ ኢላሃ ኢለላህ» ያለ ሰው ከእሳት ነፃ እንደሚወጣ ይገልፃል በዑትባን የተላለፈው ዘገባ:: በምላስ መናገሩ ብቻ በቂ አይደለም:: ሸርክን እርግፍ አድርጎ መተውንም ይጠይቃል::

14. ኢሣ (ዐሰ) እና ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ) የአላህ ባሪያዎች ናቸው::

15. ኢሣ (ዐሰ) «የአላህ ቃል» የሚል የማዕረግ ስም ተችሯቸዋል::

16. «የአላህ መንፈስ» ተብለዋልም::

17. በጀነትና በእሳት መኖር ማመን የሚያስገኘው የላቀ ትሩፋት::

18. «ፅድቅ ተግባሩ የቱን ያህል ኢምንት ቢሆንም» የሚለው መስፈርት ትኩረት ተችሮታል::

19. የሚዛን ምንነትና ባህሪ፣ እንዲሁም ተግባር::

20. ፊት የሚል የአላህ ባህሪ መወሳቱ::

# ምዕራፍ ሦስት
# ተውሒድን (ከብክለት) የጠበቀ ጀነትን ይገናፀፋል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ إِنَّ إِبْرَٰهِيمَ كَانَ أُمَّةً قَانِتًا لِّلَّهِ حَنِيفًا وَلَمْ يَكُ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴾

*«ኢብራሂም ለአላህ ታዛዥ፥ ወደ ቀጥተኛው ሃይማኖት ዘንባይ ህዝብ ነበር:: ከአጋሪዎች አልነበረም::» (አል-ነህል :120)*

﴿ وَٱلَّذِينَ هُم بِرَبِّهِمْ لَا يُشْرِكُونَ ﴾

*«እነዚያ እነሱ በጌታቸው የማያጋሩት፥» (አል-ሙእሚኑን: 59)*

ሁሴን ኢብን አብድረህማን ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«كُنْتُ عِنْدَ سَعِيدِ بن جُبَيْرٍ فَقَالَ: أَيُّكُمْ رَأى الكَوْكَبَ الذِي انْقَضَّ البَارِحَةَ؟ فَقُلْتُ أَنَا ثُمَّ قُلْتُ: أَمَا إِنِّي لَمْ أَكُنْ فِي صَلاةٍ ولكِنِّي لُدِغْتُ. قَالَ فَمَا صَنَعْتَ؟ قُلْتُ ارْتَقَيتُ: قَالَ فَمَا حَمَلَكَ عَلَى ذَلِكَ؟ قُلْتُ: حَديثٌ حَدَّثَنَاهُ الشَّعْبِيُّ قَالَ ما حَدَّثَكُم؟ قُلْتُ حَدَّثَنَا عَنْ بُرَيْدَةَ بن الحُصَيّبِ أَنَّهُ قالَ لاَ رُقْيَةَ إلاَّ مِنْ عَينٍ أو حُمَةٍ. قَالَ: وقَدْ أَحْسَنَ مَنِ انْتَهَى إلى ما سَمِعَ ولكِنْ حَدَّثَنَا ابنُ عَبَّاسٍ رضي الله عنه عَنِ النَّبيِّ ﷺ أَنَّهُ قَالَ: عُرِضَتْ عَلَيَّ الأُمَمُ فَرَأَيْتُ النَّبيَّ ومَعَهُ الرَّهْطُ والنَّبيَّ وَمَعَهُ الرَّجُلُ والرَّجُلانِ والنَّبيَّ ولَيْسَ مَعَهُ أَحَدٌ. إذْ رُفِعَ لي سَوَادٌ عَظيمٌ فظَنَنْتُ أَنَّهُمْ أُمَّتِي فَقِيلَ لِي هَذَا مُوسى وَقَوْمُه. فَنَظَرْتُ فَإذا سَوَادٌ عَظِيمٌ فَقِيلَ لي هذِهِ أُمَّتُكَ ومَعَهُمْ سَبْعُونَ ألفاً يَدْخُلونَ الجَنَّة بِغَيْرِ حِسَاب ولاَ عَذَاب. ثم نَهَضَ فَدَخَلَ مَنْزِلَهُ فَخَاضَ النَّاسُ فِي أُولَئِكَ فَقَالَ بَعْضُهُم فَلَعَلَّهُمُ الذِينَ صَحِبُوا

رَسُولَ اللهِ ﷺ وقَالَ بعْضهُمْ فَلعَلَّهُمُ الذِيْنَ وُلِدُوا فِي الإِسْلاَم فَلَمْ يُشْرِكُوا بِاللهِ شَيْئاً وَذَكَرُوا أَشْيَاءَ فَخَرَجَ عَلَيْهِم رَسُولُ اللهِ ﷺ فَأَخْبَرُوهُ فَقَالَ هُمُ الذِينَ لا يَسْتَرقُونَ ولاَ يَكْتَوونَ ولاَ يَتَطَيَّرونَ وعَلَى رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلونَ فَقَامَ عُكَّاشَةُ بنُ مِحْصَنٍ فقَالَ أُدْعُ اللهَ أَنْ يَجْعَلَنِي مِنْهُمْ قَالَ أَنْتَ مِنْهُمْ ثُمَّ قَامَ رَجُلٌ آخَرُ فَقَالَ أُدْعُ اللهَ أَنْ يَجْعَلَنِي مِنْهُمْ قَالَ سَبَقَكَ بِهَا عُكَّاشَةُ».

ከሰዒድ ኢብን ጁበይር ጋር ነበርኩ። «ያለፈውን ሌሊት ያደመቁ ከዋክብትን የተመለከተ ማን ነው?» ሲሉ ጠየቁ። «እኔ ተመልክቻቸዋለሁ» አልኩ። «ሶላት ላይ አልነበርኩም፤ ግና በመርዛም ነፍሳት ተነድፌ ነበር።» ስልም አከልኩ። «ምን አደረክ?» ጠየቁኝ። «ቱፍታን ተጠቀምኩ» አልኳቸው። «እንዲያ እንድታደርግ ያነሳሳህ ምንድን ነው?» አሉኝ። «ሸዕቢይ ያስተላለፉልን ሀዲስ ነው።» መለስኩላቸው። «ምንድን ነው ያስተላለፉላችሁ ሀዲስ?» ጠየቁኝ። «ቡረይድን በመጥቀስ፥ ለአይነ ጥላና በነፍሳት መነደፍ እንዲሁም ለትኩሳት ህመም እንጂ ለሌላ ቱፍታን መጠቀም አይፈቀድም፥ መባሉን ነግረውኛል።» ስል መለስኩ። «የደረሰውን ዕውቀት ወደ ተግባር ለመለወጥ ጥረት ያደረገ ሁሉ ሊመሰገን ይገባዋል። ግና ኢብን አባስ እንዳስተላለፉልን የአላህ መልዕክተኛ ተከታዩን ተናግረዋል፦ «ሕዝቦች ተገለፁልኝ፤ አንዱን ነቢይ ከጥቂት ተከታዮች ጋር፥ ሌላውን ነቢይ ከአንድ ወይም ሁለት ሰዎች ጋር ሌላኛውን ደግሞ አንድም ተከታይ የሌለው ሆኖ ብቻውን ተመለከትኩ። የኔ ተከታዮች እንደሆኑ ገመትኩ። «ይህ ሙሳና ተከታዮቹ ናቸው። ነገር ግን ወደ ሌላኛው አድማስ ተመልከት» ተባልኩ። በርካታ አባላትን ያቀፈ አንድ የሰዎች ስብስብ ተመለከትኩ። «እነኝህ ተከታዮችህ ናቸው። ከነርሱ መሀከል ያለምንም ጥያቄና ቅጣት ጀንነት የሚገቡ ሰዎች አሉ።» ተባልኩ።» ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ይህን እንደ ተናገሩ ተነስተው ወደ ቤታቸው ገቡ። ስለነዚያ ያለምንም ጥያቄና ቅጣት ጀንነት ስለሚገቡ ሰዎች ታዳሚው ይነጋገር ጀመር። ከፊሎቹ፦ «የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦች ሊሆኑ ይችላሉ» የሚል አስተያየት ሰጡ። ከፊሎቹ ደግሞ፦ «ምን አልባትም በዘመነ ኢስላም የተወለዱና በአላህ አንዳችንም ነገር ያላጋሩ»

ሊሆኑ እንደሚችሉ ገመቱ:: ሌሎች ግምቶችም ተሰነዘሩ:: በዚህ ወቅት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከነበሩበት ክፍል በመውጣት :- «ስለምን እየተነጋገራችሁ ነው?» ሲሉ ታዳሚዎቹን ጠየቁ:: የሚነጋገሩበትን ጉዳይ ነገሯቸው:: «እነዚያ (ያለምን ጥያቄና ቅጣት ጀንነት የሚገቡ ሰባ ሺህ ሰዎች) የማይደግሙና የማያስደግሙ፣ በገድ የማያምኑና በአላህ ብቻ የሚመኩ ናቸው::» አሉ:: ዑካሸህ ኢብን ሚህሰን:- «ከነርሱ ያደርገኝ ዘንድ አላህን ይማፀኑልኝ» አላቸው:: «አንተ ከነርሱ ነህ» አሉት:: ሌላ ሰው ቆመና:- «እኔንም ከነርሱ ያደርገኝ ዘንድ አላህን ይማፀኑልኝ» አላቸው:: «ዑካሸህ ቀድሞሃል» አሉት:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ሰዎች ካላቸው ተውሂድ ጥንካሬና ድክመት አንፃር የሚኖራቸው የተለያየ ደረጃ::

2. ተውሂድን ከሽርክ ብክለት ማፅዳት::

3. አላህ ኢብራሂምን፥ «ከአጋሪዎች አልነበረም» ሲል አወድሷቸዋል::

4. ታላላቅ የአላህ ወዳጆች «ከሽርክ የፀዱ» ተብለው መለኮታዊ እማኝነት ተችሯቸዋል::

5. «ሩቃ»ንና በገድ ማመንን መተው ተውሂድን ከብክለት የማዳን አካል ነው::

6. በአላህ መመካት (ተወኩል) ከሃዲሱ ውስጥ የተጠቀሱትን ውብ ባህሪያት ያካትታል::

7. የሶሀቦች ዕውቀት ጥልቀትና የግንዛቤ ብስለት በዘገባው ላይ ተንፀባርቋል:: የተጠቀሰውን የላቀ ደረጃ በተግባር እንጂ እንዲሁ እንደማያገኙት በሚገባ ተገንዝበዋል::

8. ሶሃባዎች ለፅድቅ ክንውን የነበራቸው የላቀ ጉጉት::

9. የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ኡምማ በጥራትም በብዛትም ከየትኛውም ነቢይ ኡምማ የተሻለ ነው::

10. የሙሣ ባልደረቦች የላቀ ደረጃ::

11. ነቢዩ(ሶ.ዐ.ወ) የተለያዩ ህዝቦች ሁኔታና እጣ ፈንታ ተገልጾላቸዋል::

12. እያንዳንዱ ኡማህ የሚቀሰቀሰው ከተላከለት ነቢይ ጋር ለየብቻ ነው::

13. ለነቢያት የተውሂድ ጥሪ አዎንታዊ ምላሽ የሰጡ ሰዎች ቁጥር አናሳነት::

14. ምንም ተከታይ ያላገኘ ነቢይ ብቻውን ይቀሰቀሳል፡፡

15. የዕውቀት የላቀ ጠቀሜታ፣ በቁጥር ብዛት አለመታለልና በቁጥር አናሳነትም አለመከፋት፡፡

16. ከዓይነ ጥላና በነፍሳት በመነደፍ ከሚፈጠር የህመም ስሜት ለመፈወስ «ሩቃ»ን መጠቀም ይፈቀዳል፡፡

17. ሰዒድ ኢብን ጁበ ÷ ያወቀውን በገቢር ለማዋል ጥረት ያደረገ ሊመሰገን እንደ ገባው በመግለፅ የተጠቀሰውን ሐዲስ አስተላለፉ፡፡ በሁለቱ ዘገባ፡ዎች መካከል ተቃርኖ አለመኖሩን በግልፅ አስቀመጡ፡፡ ይህም የሰለፎችን ዕውቀት ጥልቀትና የግንዛቤያቸውን ፅድቀት ያመለክታል፡፡

18. ሠለፎች አንድን ሰው የሌለውን መልካም ባህሪ ከማላበስና ከማወደስ የተቆጠቡ ነበሩ፡፡

19. «አንተ ከነሱው ነህ» በማለት ነቢዩ(ሶ.ዐ.ወ) ለዑካሻ መናገራቸው የነቢያዊ ትንቢታቸው አካል ነው፡፡

20. የዑካሻ የላቀ ደረጃ፡፡

21. ለበርካታ ትርጓሜዎች ክፍት የሆነን የአገላለፅ ስልት (መአሪድ) መጠቀም፡፡

22. የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ማራኪ ሰብዕና፡፡

# ምዕራፍ ስራት
# ሽርክን መጠንቀቅ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ﴾

*«አላህ በርሱ ማጋራትን በፍፁም አይምርም፤ ከዚህ ሌላ ያለውን ሀጢአት ለሚሻው ሰው ይምራል::» (አል-ኒሳእ:48)*

ነቢዩ ኢብራሂም (ዐ.ሰ.) እንዲህ ሲሉ አላህን መማፀናቸውን ቁርዓን ያስተምረናል:-

﴿ وَٱجْنُبْنِي وَبَنِيَّ أَن نَّعْبُدَ ٱلْأَصْنَامَ ﴾

*«እኔንም ልጆቼንም ጣኦታትን ከማምለክ ጠብቀን::» (ኢብራሂም:35)*

«أخوفُ ما أخافُ عليكمْ الشِّرْكُ الأصْغَرُ فَسُئِلَ عَنْهُ فقالَ: الرِّياءُ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶዐወ):- «ለናንተ በእጅጉ የምፈራላችሁ መለስተኛውን ሽርክ ነው::» ሲሉ ተናገሩ:: «መለስተኛው ሽርክ ምንድን ነው?» ተብለው ተጠየቁ:: «ለታይታና ለይስሙልኝ አንድን ተግባር መፈፀም (ሪያእ)» በማለት መለሱ::

ኢብኑ መስኡድ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«مَنْ مَاتَ وهُوَ يَدْعُو مِنْ دُونِ الله نِدًّا دَخَلَ النَّارَ».

«ከአላህ ውጭ ሌላን አካል በማምለክ ላይ እንዳለ የሞተ እሳት ገባ::» (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ሙስሊም ጃቢርን ጠቅሰው የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን መናገራቸውን ዘግበዋል :-

«مَنْ لَقِيَ الله لاَ يُشْرِكُ بِهِ شَيْئاً دَخَلَ الجَنَّةَ وَمَنْ لَقِيَه يُشْرِكُ بِه شَيْئاً دَخَلَ النَّارَ»

«አላህን በሱ ላይ አንዳች ኃይልን ሳያጋራ የተገናኘ ጀነት ገባ፤ በርሱ ላይ ሌላ ሀይልን አጋርቶ ሳይቶብት የተገናኘው ግን እሳት ገባ::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ሽርክን መጠንቀቅ ያሻል:: እጅግ አደገኛ ወንጀል ነው::

2. አንድን ተግባር የሰዎችን እይታ ለመሳብና ውዳሴያቸውን በመሻት መፈፀም (ሪያእ) ሽርክ ነው።

3. «ሪያእ» ከመለስተኛዎቹ ሽርኮች ይፈረጃል።

4. የአላህ አገልጋዮች ሊፈፅሟቸው ከሚችሉ ጥፋቶች ሁሉ አደገኛው «ሪያእ» ነው።

5. ጀነትና እሳት ሩቅ አይደሉም።

6. ሁለቱም በአንድ ሀዲስ ተቆራኝተው ቀርበዋል።

7. የሽርክ ተግባር እየፈፀመ ከአላህ ጋር የተገናኘ፥ የቱን ያህል አላህን አምላኪ ቢሆንም ከእሳት ቅጣት አይድንም።

8. ነቢ ኢብራሂም (ዐሰ) ለርሳቸውና ለልጆቻቸው አላህን የጠየቁት ነገር ከጣኦት አምልኮ እንዲጠብቃቸወ ነበር። ይህም የሽርክን አስከፊነት ይጠቁማል።

9. አብዛኛዎቹ ሰዎች የሚገኙበትን አስከፊ ሁኔታ ማጤናቸው፤

﴿ رَبِّ إِنَّهُنَّ أَضْلَلْنَ كَثِيرًا مِّنَ ٱلنَّاسِ ﴾

*«ጌታዬ ሆይ! እነርሱ (ጣኦታት) ከሰዎች ብዙዎችን አሳስተዋልና።» (ኢብራሂም :36)*

በሚለው ቁርአናዊ ቃል ውስጥ እንደተመለከተው።

10. በኻሪ ባሰፈሩት ዘገባ ውስጥ የላኢላሃ ኢለላህ ትርጓሜ ተብራርቷል።

11. ከሽርክ የፀዳ ሰው ያለው የላቀ ደረጃ።

# ምዕራፍ ስምንት
## ወደ «ላኢላሀ ኢለላህ» ጥሪ ማድረግ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ قُلْ هَٰذِهِۦ سَبِيلِىٓ أَدْعُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۚ عَلَىٰ بَصِيرَةٍ أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِى ۖ وَسُبْحَٰنَ ٱللَّهِ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴾

*«ይህች መንገዴ ናት፤ ወደ አላህ እጠራለው፤ እኔም የተከተለኝም ሰው በግልፅ ማስረጃ ላይ ነን:: ጥራት ለአላህ ይገባው:: እኔም ከአጋሪዎቹ አይደለሁም፥ በል» (ዩሱፍ:108)*

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ሙአዝን ወደ የመን በላኩበት ወቀት ተከታዩን መመሪያ ሰጥተውታል:-

«أنَّ رَسُولَ الله ﷺ لَمَا بَعَثَ مَعَاذاً إلى اليَمَنِ قَالَ لَهُ: إنَّكَ تَأتِي قَوْماً مِنْ أهْلِ الكِتَابِ فَلْيَكُنْ أوَّلَ مَا تَدْعُوهُم إلَيْهِ شَهَادَةُ أنْ لا إلـهَ إلاَّ الله.

«ከአህሉል ኪታብ የሆኑ ሰዎችን ታገኛለህ:: የመጀመሪያ ጥሪህ ላኢላሃ ኢለላህ ይሁን::»

« إلى أنْ يُوَحِّدُوا الله فَإنْ هُمْ أطَاعُوكَ لِذَلِكَ فَأعْلِمْهُمْ أنَّ الله افْتَرَضَ عَلَيْهِم خَمْسَ صَلَوَاتٍ فِي كُلِّ يَوْمٍ ولَيْلَةٍ. فَإنْ هُمْ أطَاعُوكَ لِذلِكَ فَأعْلِمهُمْ أنَّ الله افْتَرَض عَلَيْهِمْ صَدَقَةً تُؤخَذُ مِنْ أغْنِيَائِهِمْ فَتُرَدُّ عَلى فُقَرائِهِمْ فَإنْ هُمْ أطَاعُوكَ لِذلِكَ فَإيَّاكَ وكَرائِمَ أمْوَالِهِمْ واتَّقِ دَعْوَةَ المَظْلومِ فَإنَّهُ لَيْسَ بَيْنَهَا وبَيْنَ الله حِجَاب».

«አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ ጥሪ አቅርብላቸው (የሚል ሰፍሯል::) «ይህን ጥሪህን ከተቀበሉህ አላህ በቀን ውስጥ 5 ወቅት ሶላቶችን በግዳጅነት እንዳፀናባቸው አስተምራቸው:: ለዚህ ጥሪህ አዎንታዊ ምላሽ ከሰጡህ አላህ ከሀብታሞቻቸው ተይዛ ለድሆቻቸው የምትሰጥ ምፅዋት ግዴታ እንዳደረገባቸው አሳውቃቸው:: ይህንንም ከተቀበሉህ ከገንዘባቸው መልካሟን (በግዴታ ምፅዋትነት) እንዳትይዝ አደራ:: የተበደለን ሰው ዱዓ

ተጠንቀቅ። በርሷና በአላህ መካከል ምንም ዓይነት ግርዶሽ የለምና።»(ቡኻሪና ሙስሊም) ሳህል ኢብኑ ሰዒድ (ረዐ)

«أَنَّ رَسُولَ الله ﷺ قَالَ يَومَ خيبر: لأُعْطِيَنَّ الرَّايَةَ غَداً رَجُلاً يُحِبُّ الله ورَسُولَهُ ويُحِبُّهُ الله ورَسُولَهُ يَفْتَحِ الله عَلَى يَدَيْهِ فَبَاتَ النَّاسُ يَدوكُونَ لَيْلَتَهُمْ أَيُّهُمْ يُعْطَاهَا؟ فَلَمَّا أَصْبَحُوا غَدَوا عَلى رَسُولِ الله ﷺ كُلُّهُم يَرْجُو أَنْ يُعْطَاهَا. فَقَالَ أَيْنَ عَلِي بن أَبِي طالبٍ؟ فَقِيلَ هُوَ يَشْتَكِي عَيْنَيهِ فَأَرْسَلُوا إِلَيهِ فَأُتِي بِهِ فَبَصَقَ فِي عَيْنَيهِ ودَعَا لَهُ فَبَرَأَ كَأَنْ لَمْ يَكُنْ بِهِ وَجَعٌ. فأَعْطَاهُ الرَّايَةَ فَقالَ انْفُذْ عَلى رِسْلِكَ حتَّى تَنْزِلَ بِسَاحَتِهِم ثُمَّ ادْعُهُمْ إلى الإِسْلَامِ وأَخْبِرهُمْ بِمَا يَجِبُ عَلَيْهِم منْ حَقِّ الله تَعَالى فيهِ. فَوالله لأَنْ يَهْدِيَ الله بِكَ رَجُلاً واحِداً خَيرٌ لَكَ مِن حُمْرِ النَّعَم».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) የኸይበር ዕለት:- «ነገ ይህንን ሰንደቅ አላህንና መልዕክተኛውን ለሚወድና እነርሱም ለሚወዱት ሰው እሰጣለሁ። አላህ በርሱ አማካኝነት ድልን ያጎናፅፈናል።» ሲሉ ተናገሩ። ሰሃባዎች ፥ ሰንደቁን የሚረከበው ሰው ማን ይሆን? በሚለው ነጥብ ላይ ሲያስቡ፣ ሲያሰላስሉ፥ ሲወያዩ አደሩ። ሲነጋ ሁሉም ከአላህ መልዕክተኛ (ሶዐወ) ዘንድ ቀረቡ። እያንዳንዱ ሰው ሰንደቁ ለሱ እንደሚሰጥ ተስፋ ነበረው። «አሊይ ኢብን አቢ ጧሊብ የት አለ?» በማለት መልዕክተኛው ጠየቁ። «አይኖቹን ታሟል» ሲሉ ባልደረቦቻቸው መለሱላቸው። ላኩበት። እንዲመጣ ተደረገ። ነቢዩ (ሶዐወ) አይኑ ላይ ቱፍታ በማድረግ አላህን ተማፀኑለት። ፍፁም የሆነ ፈውስ አገኘ። ሰንደቁን አስከረቡት። እንዲህ አሉትም:- «ከመስካቸው ላይ እስክትደርስ ወደ ፊት ቀጥል። ከዚያ ስትደርስ ወደ ኢስላም ጥራቸው፤ ግዴታ ስለሚሆንባቸው የአላህ መብት ንገራቸው። አላህ በአንተ ሰበብ አንድን ሰው ወደ ቅን ጎዳና መምራቱ ላንተ ከቀይ ግመል ይበልጥ ዋጋ አለው።»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ወደ አላህ ጥሪ ማድረግ መልዕክተኛው (ሶዐወ) የተከተሉት ጎዳና ነው።

2. ቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ) የላቀ ትኩረት ሊቸረው ይገባል:: አብዛኛው ሰው ወደ ሀቅ ጥሪ ማድረግ ቢችልም «ኢኽላስ» ይጎድለዋል:: የግል ስሜቱንና ፍላጎቱን ለማስፈፀም ሲማስን ይስተዋላል::

3. ግልፅ ማስረጃ እጅግ አስፈላጊና ግዴታም እንደሆነ ተወስቷል::

4. የአላህን ክብር ከማጉደፍ መቆጠብ ከተውሂድ አዎንታዊ ተፅእኖዎች አንዱ ነው::

5. አላህን መሳደብና ክብሩን ማጉደፍ ከሽርክ አስከፊ ተፅዕኖዎች አንዱ ነው::

6. ሙስሊሞችን ከሙሽሪኮች ማራቅ ጠቀሜታ እንዳለው ዘገባው ያሳያል:: ከነሱ እንዳይፈረጁ:: የሽርክን ተግባር ባይፈፅሙ እንኳ ::

7. ተውሂድ ከምንም በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ የላቀ ግዳጅ ነው::

8. ወደ ኢስላም ጥሪ የሚያደርግ ሰው መጀመር የሚገባው በተውሂድ እንደሆነ ተመልክቷል::

9. «አላህን በብቸኝነት ሊያመልኩ» የሚለው ሀረግ የላኢላሃ ኢለላህን አስኳል ትርጓሜ ጨብጧል::

10. አንድ ሰው የእምነቱን ትክክለኛ ባህሪ ባይረዳ ወይም ተረድቶ በገቢር ባያውለው እንኳ «አህሉል ኪታብ» ሊሰኝ ይችላል::

11. ትምህርት ደረጃ በደረጃ መሰጠት እንዳለበት ዘገባው ያመለክታል::

12. እያንዳንዱ የኢስላም ትምህርት እንደ የክብደቱና አስፈላጊነቱ በየደረጃው ትኩረት ይቸረዋል::

13. ዘካ የሚሰጣቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ዘገባው ውስጥ ተወስተዋል::

14. አንድ መምህር ለተማሪዎቹ አሻሚ የሆኑ ሀሳቦችን የማብራራት ኃላፊነት አለበት::

15. ዘካ ሰብሳቢ ከዘካ ሰጪው ንብረቶች እጅግ ውድ ዋጋ ያላቸውን መርጦ መቀበሉ አግባብ አይደለም::

16. የተበዳይን ዱዓ መጠንቀቅና መፍራት ያሻል::

17. የተበደለ ሰው ዱዓ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት አለው::

18. የነቢያት ፈርጥ በሆኑት ነቢይ በሙሐመድ (ሶዐወ) እና ባልደረቦቻቸው ላይ የደረሰው ረሀብ፣ ጥማት፣ ስቃይ... የተውሂዳቸውን ጥንካሬ ያመለክታል::

19. «ሰንደቁን እሰጥሃለሁ» የሚለው አረፍተ ነገር ከነቢያት ምልክቶች አንዱ ነው።

20. ከአይኑ ላይ ቱፍታ በማድረግ እንዲፈወስ ማድረጋቸውም እንዲሁ ከነብይነታቸው ምልክቶች አንዱ ነው።

21. የአሊይ (ረዐ) ታላቅነት።

22. የሶሃቦች የላቀ ደረጃ። ሌሊቱን በሙሉ ሲያስቡና ሲያሰላስሉ አደሩ። የድሉ ብስራት እውን ሆኖ ለማየት በመጓጓት።

23. በቀደር ማመን። ሰንደቁን መቀበል የከጀሉ ሁሉ ሳያገኙት ሀሳቡ ያልነበራቸው አሊይ እንዲረከቡት ተደርጓል።

24. «ወደ ፊት ቀጥል» በማለት ነቢዩ (ሰዐወ) ለአሊይ የሰጡት ትዕዛዝ የነበራቸውን ከፍተኛ ዲሲፕሊን ያሳያል።

25. ከውጊያ በፊት ወደ ኢስላም ጥሪ ማድረግ ይቀድማል።

26. ወደ ኢስላም ጥሪ ቀርቦላቸው አሻፈረን ያሉ ወገኖችን መዋጋት ይፈቀዳል።

27. ዳዕዋ ከፍተኛ ጥበብን (ሒክማ) ይጠይቃል። «ግዴታ የሚሆንባቸውን ነገር አስተምራቸው።» የሚለው ነቢያዊ ቃል ይህንኑ ያመለክታል።

28. አላህ በባሮቹ ላይ ያለው መብት።

29. አንድ ሰው በሱ አማካኝነት ቅንን መንገድ የያዘለት «ዳዒ» የሚያገኘው የላቀ ትሩፋት።

30. ለአንድ ነገር ብይን በሚሰጡበት ወቅት መማል እንደሚፈቀድ።

# ምዕራፍ ስድስት
## የተውሂድና የላኢላሀ ኢለላህ ትርጓሜ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ أُولَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ يَبۡتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ ٱلۡوَسِيلَةَ أَيُّهُمۡ أَقۡرَبُ وَيَرۡجُونَ رَحۡمَتَهُۥ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُۥٓۚ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحۡذُورٗا﴾

*«እነዚያ እነሱ የሚገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን ሥራ ይፈልጋሉ፤ እዝነቱንም ይከጅላሉ፤ ቅጣቱንም ይፈራሉ፤ የጌታህ ቅጣት የሚፈራ ነውና::» (አል-ኢስራእ: 57)*

﴿ وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦٓ إِنَّنِي بَرَآءٞ مِّمَّا تَعۡبُدُونَ ○ إِلَّا ٱلَّذِي فَطَرَنِي فَإِنَّهُۥ سَيَهۡدِينِ○ وَجَعَلَهَا كَلِمَةَۢ بَاقِيَةٗ فِي عَقِبِهِۦ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ﴾

*«ኢብራሂም ለአባቱና ለህዝባቹ ባለ ጊዜ አስታውስ:: እኔ ከምትገዙት ሁሉ ንፁህ ነኝ:: ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር አልገዛም:: በእርግጥ ይመራኛልና:: በዝርዮቹም ዘንድ ይመለሱ ዘንድ በአምላክ ማመንን ቀሪ ቃል አደረጋት::» (አልዙኹሩፍ:26-28)*

﴿ ٱتَّخَذُوٓاْ أَحۡبَارَهُمۡ وَرُهۡبَٰنَهُمۡ أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِ﴾

*«ሊቃውንቶቻቸውንና መነኩሳቶቻቸውን፤ የማርያምን ልጅ ኢሣ አልመሲህንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ::»(አል-ተውባህ :81)*

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادٗا يُحِبُّونَهُمۡ كَحُبِّ ٱللَّهِۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَشَدُّ حُبّٗا لِّلَّهِۗ﴾

*«ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን (ጣኦታትን) አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አሉ:: እነዚያ ያመኑት ለአላህ የበረታ ፍቅር አላቸው::»(አል-በቀረህ:165)*

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን መናገራቸውን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዋል:-

«مَنْ قَالَ لا إلـهَ إلاَّ الله وكَفرَ بِمَا يُعْبَدُ مِنْ دُونِ الله حَرُمَ مَالُهُ ودَمُهُ وحِسَابُهُ عَلى الله».

«ላኢላሃ ኢለላህ ያለና ከአላህ ውጭ በሚመለኩ ኃይላት የካደ ገንዘቡም ደሙም እርም ሆነ። ከዚያ በኋላ የሰውዬውን ምስክርነት እውነተኛነት የመፈተሹ ኃላፊነት ለአላህ የተተወ ነው።»

## ጠቃሚ ነጥቦች

ባለፉት ርዕሶች ሦስት አበይት ቁም ነገሮች ተዳሰዋል። ከሁሉም አብይ ሊሰኝ የሚበቃው የሸሃዳዎች ትርጓሜ ነው። በማያሻማ ሁኔታ ተብራርቷል። ከአል ኢስራእ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሰው አንቀፅ ደጋግ ሰዎችን የሚያመልኩ ሙሽሪኮችን ስህተትና ተግባራቸውም ከትልቁ ሺርክ የሚፈረጅ መሆኑን በግልፅ አስቀምጧል። ከአልተውባህ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰው አንቀፅ ደግሞ አህለል ኪታቦች ሊቃውንቶችንና መነኩሳቶቻቸውን አማልክት አድርገው መያዛቸውን ገልፆ አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ እንጂ በዚህ እንዳልታዘዙ ያብራራል። ሊቃውንቶችን ማምለክ ማለት አላህን በመወንጀል ሲያዙ አሜን ብሎ መቀበል እንጂ ለእነርሱ «ኢባዳ» ማድረግ አይደለም። የአንቀፁ ትክክለኛ ትርጓሜ ይኸው ነው። ነቢዩ ኢብራሂም፦

﴿ إِنَّنِي بَرَآءٌ مِّمَّا تَعْبُدُونَ ۝ إِلَّا ٱلَّذِى فَطَرَنِى ﴾

*«ከምትገዙት ነገር ሁሉ። ንፁህ ነኝ። ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር»*

በማለት ከአላህ ውጭ ሌላን ኃይል እንደማያመልኩ መግለፃቸው ተወስቷል። ይህ አይነቱ «በራእ» (ራስን ከሽርክ ተግባራትና ከሙሽሪኮች መገንጠል) የላኢላሃ ኢላላህ ትርጓሜ አካል እንደሆነ አላህ ሲገልፅ፦

﴿ وَجَعَلَهَا كَلِمَةًۢ بَاقِيَةً فِى عَقِبِهِۦ لَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ﴾

*«በዝርዮቹም ውስጥ ይመለሱ ዘንድ (በአንድ አምላክ ማመንን) ቀሪ ቃል አደረጋት» ብሏል።*

አልበቀራህ ምዕራፍ ላይ የሰፈረው አንቀፅ፦

﴿ وَمَا هُم بِخَٰرِجِينَ مِنَ ٱلنَّارِ ﴾

*«እነርሱ ከእሳት ወጭዎች አይደሉም።»*

የሚል መለኮታዊ ዛቻ ስለተሰነዘረባቸው ከሃዲያን ያወሳል። እነዚህ ከሃዲያን ጣኦቶቻቸውን አላህን እንደሚወዱ አድርገው ይወዳሉ። አላህን በጥልቅ እንደሚያፈቅሩ አንቀፁ ይጠቁማል። ግና

ከሙስሊሞች ወገን አልፈረጃቸውም:: ጣኦቶቻቸውን ከአላህ ይበልጥ የሚያፈቅሩትንስ በሙስሊምነት እንቀበላለን? ጣኦቶቻቸውን እንጅ አላህን የማያፈቅሩትንስ?

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ቃልም ተጠቃሽ ነው:: «ላኢላሃ ኢለላህ ያለና ከአላህ ሌላ ያሉ ተመላኪ ኃይላትን የካደ ገንዘቡም ደሙም የተጠበቀ ነው:: የምስክርነቱን እውነተኛነት የመፈተሹ ኃላፊነት የአላህ ነው» ብለዋል:: ላኢላሃ ኢለላህን በቃል መናገሩ ብቻ ደምንና ገንዘብን የተጠበቀ አያደርግም:: ትርጉሟን በጥልቅ መረዳትና ከልብ መቀበል ያሻል:: ከአላህ ውጭ ሌላ ኃይላትን አለማምለክም:: ከዘገባው ላይ በግልፅ እንደሰፈረው:: ከአላህ ሌላ ባሉ ኃይላትም መካድ ያስፈልጋል:: አንድ ሰው በዚህ ላይ ቅንጣት ጥርጣሬ ካለበት (ካመነታ) ገንዘቡም ደሙም ጥብቅ አይሆኑም::

እጅግ የተብራራና በግልፅ የተቀመጠ ነጥብ ነው:: ከፍተኛ ትኩረት ይሻል::

# ምዕራፍ ሰባት
## ጉዳትን ለመከላከል ወይም ለማስቀረት ቀለበትን ማጥለቅ፣ ክርን ማንጠልጠል ወዘተ ከሺርክ ይፈረጃል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ قُلْ أَفَرَءَيْتُم مَّا تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ إِنْ أَرَادَنِىَ ٱللَّهُ بِضُرٍّ هَلْ هُنَّ كَـٰشِفَـٰتُ ضُرِّهِۦٓ أَوْ أَرَادَنِى بِرَحْمَةٍ هَلْ هُنَّ مُمْسِكَـٰتُ رَحْمَتِهِۦ ۚ قُلْ حَسْبِىَ ٱللَّهُ ۖ عَلَيْهِ يَتَوَكَّلُ ٱلْمُتَوَكِّلُونَ ﴾

*«ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣኦታትን አያችሁን? አላህ በጉዳት ቢፈልገኝ እነሱ ጉዳቱን ገላጮች ናቸውን? ወይስ በችሮታው ቢፈቅደኝ እነርሱ ችሮታውን አጋጆች ናቸውን? በላቸው አላህ በቂየ ነው፤ በርሱ ላይ ተመኪዎች ይመካሉ::» (አል-ዙመር :38)*

ኡምራን ኢብን ሁሰይን (ረዐ) እንዳስተላለፉት:-

«أَنَّ النَّبِيَّ ﷺ رَأى رَجُلاً فِي يَدِهِ حَلْقَةٌ مِنْ صُفْرٍ فَقَالَ ﷺ ما هذِهِ؟ قَالَ من الوَاهِنَةِ فَقَال: أَنْزِعهَا فَإِنَّهَا لا تَزِيْدُكَ إلاَّ وَهْناً فَإِنَّكَ لَوْ مُتَّ وَهِي عَلَيكَ ما أَفْلَحْتَ أَبداً».

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የመዳብ ቀለበት ያጠለቀ አንድ ሰው ተመለከቱ:: «ይህ ምንድን ነው» አሉት:: «የእርጅናን ድካም ለመቋቋም ነው ያጠለቅኩት» አላቸው:: «አውልቀው፤ ከድካም ውጭ የሚያክልልህ ነገር የለም:: ከእጅህ ላይ እንዳለ ሞተህ ቢሆን ኖሮ ከዘላለማዊ እሳት አትድንም ነበር» አሉት:: (አህመድ ብዙም ጠንካራ ባልሆነ ሰነድ ዘግበውታል)

አህመድ ኡቅበት ኢብን አሚርን ጠቅሰው «መርፉዕ» በሆነ ሰነድ እንደዘገቡት የአላህ ምልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል:-

«مَنْ تَعَلَّقَ تَمِيمةً فَلاَ أَتَمَّ الله لَهُ. ومَنْ تَعَلَّقَ وَدَعَةً فَلا وَدَعَ الله له».

«ተማኢም (ሂርዝ) ያንጠለጠለ አላህ (ጉዳዩን) አይሙላለት:: ወዳአ ያንጠለጠለ አላህ ስክነትን አይለግሰው::»

በሌላ ዘገባ ደግሞ:-

«مَنْ تَعَلَّقَ تَمِيْمَةً فَقَدْ أَشْرَكَ».

«ሂርዝ ያንጠለጠለ የሽርክ ተግባር ፈፀመ» መባሉ ተወስቷል::

ኢብን ሃቲም ሁዘይፋን ጠቅሰው እንዳስተላለፉት:-

«أَنَّهُ رَأَى رَجُلاً فِي يَدِهِ خَيْطٌ مِنَ الحُمَّى فَقَطَعَه وتَلا قَوْلَهُ ﴿وَمَا يُؤْمِن أَكْثَرُهُم بالله إلاَّ وَهُمْ مُشْرِكُونَ﴾.

ለትኩሳት መፈወሻ በሚል ከእጁ ላይ ክር ያንጠለጠለ አንድ ሰው ተመለከቱ:: ክሩን በጠሱበት:: ከዚያም:- «አብዛኛ ዎቻቸው እነርሱ አጋሪዎች ሆነው እንጅ በአላህ አያምኑም» (የሱፍ: 106) የሚል ቁርአናዊ ቃል አነበቡ::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ከላይ ለተጠቀሱት አላማዎች ቀለበትን ማጥለቅ፣ ክርን ማንጠልጠል ወዘተ የከበደ የሃጢአት ድርጊት ነው::

2. ሶሃቢዩ ቀለበቱን እንዳንጠለጠለ ቢሞት ኖሮ ለዘላለማዊ የእሳት ቅጣት እንደሚዳረግ መገለፁ :- «መለስተኛው ሺርክ ከትልቁ ሽርክ ይበልጥ አጥፊ ነው» የሚለውን የሶሃባዎች አባባል ትክክለኛነት ያረጋግጣል::

3. በእንዲህ ዓይነት መሠረታዊ ጉዳዮች ላይ አለማወቅ ምክንያት ሊሆን አይችልም::

4. ቀለበቱ ላሰበው አላማ አይጠቅመውም:: ይልቁንም ይጎዳዋል:: «ከድክመት ውጭ የሚያክልልህ ነገር የለም» የሚለው ነቢያዊ ቃል ይህንኑ ያመለክታል::

5. እንዲህ አይነቱን ተግባር የሚፈፅምን ሰው ኃይልና ቁጣ በተቀላቀለበት አኳኋን ከጥፋቱ ማረም ተገቢ ነው::

6. ከአላህ ውጭ ባለ ሌላ ኃይል የተመካ አላህ ለዚያ ኃይል እንደሚተወው በሀዲስ ተገልጿል::

7. ሂርዝ ማንጠልጠል የሽርክ ተግባር መፈፀም ነው::

8. ለህመም (ትኩሳት/ንዳድ) ክርን ማንጠልጠልም ሽርክ ነው::

9. ሁዘይፋህ የተጠቀሰውን የቁርአን አንቀፅ ማንበባቸው ሰሃቦች ለትልቁ ሽርክ የተጠቀሱ አንቀፆችን ለመለስተኛው ሽርክም እንደሚያውሉ ያመለክታል:: ኢብን አባስም ከአልበቀራህ ምዕራፍ ውስጥ አንድ አንቀፅ በመጥቀስ ይህንኑ ስልት ተጠቅመዋል::

10. ለሰው አይን (ለአይነ ጥላ) «ወዳዕ» ማንጠልጠል የሽርክ ተግባር ነው::

11. ሂርዝ ላንጠለጠለ ሰው አላህ ጉዳዩን እንዳይሞላለት፥ ወዳእ ላንጠለጠለ ሰው ደግሞ አላህ ስክነትን እንዳይለግሰው ነቢዩ (ሶዐወ) ዱዓእ አድርገዋል::

# ምዕራፍ ስምንት
# ስለመጠበቂያ (ሩቃ) እና ተማኢም (ሂርዝ) የተነገሩ የሀዲስ ዘገባዎች

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት አቡበክር አል አንሷሪ (ረዐ) ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«أَنَّهُ كَانَ مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ فِي بَعْضِ أَسْفَارِهِ فَأَرْسَلَ رَسُولاً أَنْ لاَ يَبْقَيَنَّ فِي رَقَبَةِ بَعِيرٍ قِلاَدةٌ مِن وَتَرٍ أَوْ قِلاَدَةٌ إِلاَّ قُطِعَتْ».

በአንድ ጉዞ ላይ ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ነበርኩ:: «ከከብቶች አንገት ላይ የተንጠለጠሉ ክሮችን ወይም ዶቃዎችን አንድም ሳታስቀር በጥስ» የሚል መልዕክት አስይዘው መልዕክተኛ ላኩ::

የአላህ መልዐክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት ኢብን መስዑድ (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«إِنَّ الرُّقَى والتَّمَائِمَ والتِّوَلَةَ شِرْكٌ».

«ሩቃ፣ ሂርዝና ቲወላ ሽርክ ናቸው::» (አህመድና አቡዳውድ)

ተማኢም (ሂ.ርዝ) ከዓይነ ጥላ ለመጠበቅ ከልጆች አንገት ላይ የሚንጠለጠል ነው:: «የቁርአን አንቀጾች የተጻፉበት ከሆነ ይፈቀዳል::» ይላሉ ከሠለፎች ከፊሎቹ:: ሌሎቹ ደግሞ- ኢብን መስዐድን ጨምሮ - መንገድ መክፈቱን አልወደዱትም:: ሐራም እንደሆነ ይገልጻሉ::

«አዛኢም» በመባልም ይታወቃል ሩቃ:: ሽርክ ያልሆነ እንዳለው የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ):- «ለአይነ ጥላና ለህመም (ትኩሳት/ንዳድ) ይፈቀዳል» ሲሉ ገልፀዋል::

«ቲወላህ» መስተፋቅር ነው:: የባልና ሚስትን ፍቅር ይጨምራል ተብሎ ይታመናል- በአድራጊዎች ዘንድ::

አብደላህ ኢብን ኡሰይም መርፋዕ በሆነ ሰነድ እንዳስተላለፉት:-

«مَنْ تَعَلَّقَ شَيْئاً وُكِلَ إِلَيْهِ».

«አንዳች ነገር ያንጠለጠለ ለዛ ነገር ይተዋል» መባሉ ተወስቷል::(አህመድና ቲርሚዚ)

ሩወይፋዕ ተከታዩን ማስተላለፋቸውን አህመድ ዘግበዋል:: የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«يَا رُوَيْفِعُ! لَعَلَّ الحَيَاةَ سَتَطُولُ بِكَ فَأَخْبِرِ النَّاسَ أَنَّ مَنْ عَقَدَ لِحْيَتَهُ أو تَقَلَّدَ وَتَراً أَوِ اسْتَنْجَى بِرَجِيعِ دَابَّةٍ أَوْ عَظْمٍ فَإِنَّ مُحَمَّداً بَرِيءٌ مِنْهُ».

«ሩወይፋዕ ሆይ! ምን አልባትም ረዥም ዕድሜ ልትኖር ትችላለህ:: ፂሙን የቋጠረ፣ ክር ያንጠለጠለ፣ በእንስሳት ፍግ ወይም አጥንት ኢስቲንጃ ያደረገ ሙሐመድ ከርሱ የፀዱ መሆናቸውን ለሰዎች ንገር» አሉኝ::

ሰዒድ ኢብኑ ጁበይር እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«مَنْ قَطَعَ تَمِيمَةً مِنْ إنْسَانٍ كَانَ كَعَدْلِ رَقَبَةٍ».

«ከአንድ ሰው (አንገት) ላይ ሂርዝን የበጠሰ ባሪያን ነፃ ከለቀቀ ቁጥር ነው::»

ኢብራሂምን በመጥቀስ ወኪዕ እንዳስተላለፉት ሶሃቦች ሂርዝን የቁርአን አናቀፅ የተከተበበትም ይሁን ሌላ አጥብቀው ይጠሉ ነበር::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የሩቃ (መጠበቂያ) እና የተማኢም (ሂርዝ) ትርጓሜ::

2. የቲወላህ ትርጓሜ::

3. ሁሉም ሽርክ ናቸው፤ ያለምንም ልዩነት::

4. ለአይነ ጥላና ለህመም (ትኩሳት/ንዳድ) በቁርአን «ሩቃ» መጠቀም ሽርክ አይደለም::

5. ሂርዝ የቁርአን አንቀፆች የተከተቡበት ከሆነ ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም በሚለው ነጥብ ላይ ኡለሞች ተወዛግበዋል::

6. ለአይነ ጥላ በሚል ከከብቶች አንገት ላይ ክርን ማንጠልጠል ሽርክ ነው::

7. ከከብቱ ወይም ከራሱ አንገት ላይ ክርን ላንጠለጠለ የተሰነዘረ አስደንጋጭ ዛቻ::

8. ከአንድ ሰው አንገት ላይ ሂርዝን የበጠሰ የሚያገኘው የላቀ ምንዳ::

9. የኢብራሂም ንግግር የተጠቀሰውን የኡለሞች ውዝግብ የሚቃረን አይደለም:: የአብደላህን ባልደረቦች አቋም ብቻ የሚያንፀባርቅ ነው::

# ምዕራፍ ዘጠኝ

## በዛፍ፣ በድንጋይና መሰል ግዑዛን መባረክ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿أَفَرَءَيۡتُمُ ٱللَّٰتَ وَٱلۡعُزَّىٰ ۝ وَمَنَوٰةَ ٱلثَّالِثَةَ ٱلۡأُخۡرَىٰٓ﴾

*«አልላትና አልኡዛን አያችሁን? ሦስተኛውንም አነስተኛዋን መናትም!» (አል-ነጅም: 19-20)*

አቡዋቂድ አለይስ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«خَرَجْنَا مَعَ رَسُولِ اللهِ ﷺ إِلَى حُنَيْنٍ وَنَحْنُ حُدَثَاءُ عَهْدٍ بِكُفْرٍ ولِلْمُشْرِكِينَ سِدْرَةٌ يَعْكُفُونَ عِنْدَهَا ويَنُوطُونَ بِهَا أَسْلِحَتَهُمْ يُقَالُ لَهَا ذَاتُ أَنْوَاطٍ فَمَرَرْنَا بِسِدْرَةٍ فَقُلْنَا يَا رَسُولَ اللهِ! اجْعَلْ لَنَا ذَاتَ أَنْوَاطٍ كَمَا لَهُمْ ذَاتَ أَنْوَاطٍ فَقَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ اللهُ أَكْبَرُ إِنَّهَا السَّنَنُ قُلْتُمْ والذِي نَفْسِي بِيَدِهِ كَمَا قَالَتْ بَنُو إِسْرائِيلَ لِمُوسَى ﴿اجْعَلْ لَنَا إِلٰهاً كَمَا لَهُمْ آلِهَةٌ قَالَ إِنَّكُمْ قَوْمٌ تَجْهَلُونَ﴾ لَتَرْكَبُنَّ سُنَنَ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ.

ከአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር ለሁነይን ዘመቻ ተንቀሳቀስን:: ኢስላምን ከተቀበልን ብዙም አልቆየንም:: ሙሽሪኮች አንዲት ዛፍ ነበረቻቸው:: ከአጠገቧ ይቀመጣሉ:: ሰይፋቸውንም ያንጠለጥሉባታል:: «ዛት አንዋጥ» የሚል ስያሜ ተሰጥቷታል:: በዚያች ዛፍ አጠገብ አለፍን:: «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ+ለኛም እንደነሱ ዛቱአንዋጥ ያድርጉልን» በማለት ጠየቅናቸው:: «አላሁ አክበር! ይህ የሌሎች ህዝቦች ፈለግ ነው:: ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ:: የጠየቃችሁት በኒ ኢስራኤል ለሙሣ:- «ሙሣ ሆይ! ለነርሱ አማልክት እንዳሏቸው ለኛም አምላክ አድርግልን» (አል-አዕራፍ: 37) በማለት ያቀረቡት አይነት ጥያቄ ነው:: ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ፈለግ ትከተላላችሁ» አሉ:: (ቲርሚዚ ዘግበውታል ፤ ሶሂህ ብለውታልም::)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አልነጅም 19-20» ትርጉም::

2. ሶሀቦች ለነቢዩ (ሶ.0.ወ) ያቀረቡትን ጥያቄ እውነተኛ ምንነት መረዳት::

3. ሶሃቦች ጥያቄውን አቀረቡ እንጂ አልፈፀሙትም::

4. በዚህ ተግባር ወደ አላህ መቃረብን ነበር የፈለጉት:: ይወደዋል በሚል ፅኑ እምነት::

5. ሶሃቦች ይህንን መገንዘብ ከተሳናቸው ሌሎቹ እንዲህ አይነት ነገሮችን አለመረዳታቸው የሚጠበቅ ነው::

6. ሶሃቦች ከሌሎች በላቀ ሁኔታ አያሌ የመልካም ሥራ ምንዳ ክምችት፣ ከአላህ ዘንድም የምህረት ቃል ኪዳን አላቸው::

7. ነቢዩ (ሶ.0.ወ) በዚህ ነጥብ ላይ ምንም ዓይነት ይቅርታ አላደረጉላቸውም፤እንዲህ በማለት ነበር ተቃውሟቸውን የገለፁት:- «አላሁ አክበር! ይህ የሌሎች ህዝቦች ፈለግ ነው:: ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን የጥፋት ጎዳና ትከተላላችሁ::»

8. ጥያቄአቸውን በኒ ኢስራኤሎች «አምላክ አድርግልን» በማለት ለሙሳ ካቀረቡት ጥያቄ ጋር ማመሳሰላቸው አትኩሮት ሊሰጠው የሚገባ እጅግ ጠቃሚ ነጥብ ነው::

9. ይህ ሁሉ ከላኢላሃ ኢለላህ ትርጓሜ ውስጥ ተካቷል:: ለሶሃቦች በጉልህ ባይታያቸውም::

10. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.0.ወ) የሰጡትን ብይን በመሃላ አፅድቀዋል:: ጠቃሚ ለሆነ ነገር ካልሆነ በቀር አይምሉም ነበር::

11. ሽርክ ትልቁና አነስተኛው ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይችላል:: ምክንያቱም ሶሃቦች በዚህ ጥያቄአቸው ከኢስላም ውጭ አልተዳረጉም::

12. «እኛ ኢስላምን ከተቀበልን ቅርብ ጊዜአችን ነው» ማለታቸው ሌሎች ቀደም ብለው ኢስላምን የተቀበሉት ይህን ነገር እንደሚያውቁት ያመለክታል::-

13. አስደናቂ ነገር ሲገጥም «ተክቢራ» ማድረግ::

14. ለባሰ ጥፋት የሚዳርግን ትንሽ ቀዳዳ አለመክፈት::

15. ከጃሂሊያ ሰዎች ጋር መመሳሰል የተከለከለ ነው::

16. ትምህርት በሚሰጡበት ጊዜ ቁጣን መቀላቀል አስፈላጊ የሚሆንበት አጋጣሚ አለ::

17. «ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች ፈለግ ነው» የሚለው ሃረግ ስለሰው ልጆች የዕድገት እርከኖች አጠቃላይ መርህ ግንዛቤን ያስጨብጣል::

18. ይህ ከነቢያዊ ምልክቶች አንዱ ነው። የተነበዩት በገቢር ውሎ ተገኙ። ህዝበ- ሙስሊም ያለፉ ህዝቦችን ፈለግ ተከተለ።

19. አላህ ቁርአን ውስጥ የሁዳዎችንና ክርስቲያኖችን ያወገዘበት ነገር እኛንም ይመለከታል።

20. የኢባዳ ምንጭ መለኮታዊ ትዕዛዝ እንደሆነ አህለል ኪታብ በማገባ ይረዳለ።፡

21. የአህለል ኪታብ ጎዳና እንደ ሙሽሪኮች ጎዳና የተወገዘ ነው።

22. ከአንድ ባጢል (መጥፎ) እምነት፣ አመለካከት፣ ልምድና ባህል ተላቆ ወደ ኢስላም የመጣ ልቦናው ውስጥ የዚያ እምነት፣ ባህል ወይም አመለካከት ቅሪት በቀላሉ ላይፋቅለት ይችላል። ሶሃቦች ከዚህ ዘገባ ላይ «ኢስላምን የተቀበልነው በቅርቡ ነው» ማለታቸው ይህንኑ ያመለክታል።

# ምዕራፍ አስር
# ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት ለለማረድ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ قُلْ إِنَّ صَلَاتِي وَنُسُكِي وَمَحْيَايَ وَمَمَاتِي لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ۝ لَا شَرِيكَ لَهُۥ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلْمُسْلِمِينَ ﴾

*«ስግደቴም፣ መገዛቴም፣ ህይወቴም ሞቴም ለአለማት ጌታ ለአላህ ነው፥ በል:: ለርሱ ተጋሪ የለውም:: በዚህም በማጥራት ታዘዝኩ:: እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ነኝ (በል)::» (አል-አንዓም : 162-163)*

﴿ فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَٱنْحَرْ ﴾

*«ለጌታህ ስገድ፤ (በስሙ) ሰዋም::» (አል-ከውሰር :2)*

ዓሊ (ረዐ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«حَدَّثَنِي رَسُولُ الله ﷺ بِأَرْبَعِ كَلِمَاتٍ: لَعَنَ الله مَنْ ذَبَحَ لِغَيْرِ الله. لَعَنَ الله مَنْ لَعَنَ وَالِدَيْهِ. لَعَنَ الله مَنْ أَوَى مُحْدِثاً. لَعَنَ الله مَنْ غَيَّرَ مَنَارَ الأَرْضِ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዮቹን አራት ጠቃሚ ቁም ነገሮች ነግረውኛል:-

ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት የሚያርድን አላህ ረግሞታል:: ወላጆቹን የረገመ አላህ ረግሞታል:: ሸሪዓዊ የቅጣት ብይን የተወሰነበትን ሰው ያስጠጋንም አላህ ረግሞታል:: የመሬት ይዞታ ምልክቱን የቀየረም አላህ ረግሞታል::

ጧሪቅ ኢብን ሸሃብ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ):-

«دَخَلَ الجَنَّةَ رَجُلٌ فِي ذُبَابٍ وَدَخَلَ النَّارَ رَجُلٌ فِي ذُبَابٍ. قَالُوا وَكَيْفَ ذَلِكَ يَا رَسُولَ الله ﷺ قَالَ مَرَّ رَجُلانِ عَلى قَوْمٍ لَهُمْ صَنَمٌ لا يُجَاوِزُهُ أَحَدٌ حَتَّى يُقَرِّبَ لَهُ شَيْئاً فَقَالُوا لأَحَدِهِمَا قَرِّبْ قَالَ لَيْسَ عِنْدِي شَيْءٌ أُقَرِّبُ قَالُوا لَهُ قَرِّب وَلَوْ ذُبَاباً. فَقَرَّب ذُبَاباً فَخَلُّوا سَبِيلَهُ فَدَخَلَ النَّارَ. وَقَالُوا للآخَرِ قَرِّب. فَقَالَ مَا كُنْتُ

لأُقَرِّبَ لأَحَدٍ شَيْئاً دُوْنَ الله عزَّ وجَلَّ فَضَرَبُوا عُنُقَهُ فَدَخَلَ الجَنَّةَ»

«አንድ ሰው በዝንብ ምክንያት ጀነትን ተጎናፅፏል:: አንድ ሌላ ሰው ደግሞ በዝንብ ምክንያት ለእሳት ተዳርጓል» በማለት ተናገሩ:: «ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ?» በማለት ባልደረቦቻቸው ጠየቋቸው:: «ነገሩ እንዲህ ነው

ሁለት ሰዎች በአንድ ክልል ያልፉሉ:: ነዋሪዎቹ አንድ ጣኦት አላቸው:: በዚህ ክልል ያለፈ ማንም ሰው ለዚያ ጣኦት አንዳች ነገር ሳያቀርብ እንዲያልፍ አይፈቀድለትም:: ከሁለቱ መንገደኞች ለአንደኛው:- «ለጣኦታችን መስዋዕት አቅርብ» ሲሉ ጠየቁት:: «መስዋዕት የማቀርበው ነገር የለኝም::» አላቸው:: «ዝንብም ቢሆን ማቅረብ ትችላለህ» አሉት:: የዝንብ መስዋዕት አቀረበ:: እንዲያልፍ ተፈቀደለት:: በዚች ሰበብ ለእሳት ተዳረገ:: ሌላኛውንም እንዲሁ «መስዋዕት አቅርብ» አሉት:: « ልዑልና ኃያል ከሆነው አላህ ውጭ ለማንም መስዋዕት አላቀረብም» በማለት መለሰላቸው:: አንገቱን መተው ገደሉት:: ጀነትን ተጎናፀፈ::» (አህመድ ዘግበውታል)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀጽ «አል አንዓም 162-163» ትርጉም

2. የአንቀጽ «አል ከውሰር 2» ትርጉም::

3. ከተጠቀሰው የሐዲስ ዘገባ ላይ አላህ መርገምት ከሚያወርድባቸው ሦስት ሰዎች በቅድሚያ የተወሳው ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት የሚያርደው ነው::

4. ወላጆቹን የተራገመ ሰው የአላህ እርግማን ይወርድ በታል:: የሌሎችን ወላጆች በመርገም ለወላጆቹ መረገም ምክንያት የሆነም ከመርገምቱ አያመልጥም::

5. የአላህ ቅጣት ለተወሰነበት ሰው መጠጊያ የሆነም የአላህ እርግማን ይወርድበታል::

6. የመሬት ይዞታን ምልክት መቀየር፣ ማለትም በርሱና በጎረቤቱ መካከል ያለውን ድንበር ማፋለስም ለአላህ እርግማን ይዳርጋል::

7. ወንጀለኞችን በአጠቃላይ መራገም ይፈቀዳል:: አንዱን ወንጀለኛ ለይቶ መራገም ግን ይፈቀዳል ወይስ አይፈቀድም? በሚለው ነጥብ ላይ የዑለማዎች ውዝግብ አለ::

8. እጅግ ጠቃሚ ታሪክ ተወስቷል- የዝንቧ ታሪክ::

9. ሰውዬው በአንዲት ዝንብ ሰበብ ለእሳት መዳረጉ:: አስቦበት አልነበረም:: ከጥቃታቸው ለመዳን ነበር የፈፀመው::

10. በሙእሚኖች ልቦና ውስጥ ሽርክ የተሰጠው ክብደት፡፡ አንዲት ዝንብ መስዋዕት በማቅረብ ፍላጎታቸውን ከማሟላት ሞትን መረጠ፡፡

11. በዚህች በጥፋቱ ለእሳት የተዳረገው ሙስሊም ነው፡፡ ካፊር ቢሆን ኖሮ ለእሳት የመብቃቱን ሰበብ ሲገልፁ፡- «በአንዲት ዝንብ ሰበብ ለእሳት ተዳረገ» ባላሉ ነበር፡፡

12. ከላይ የተወሳው ዘገባ ተከታዩን ሶሒሕ የሐዲስ ዘገባ ያጠናክራል፡- «ጀነት እና እሳት ከናንተ ለአንዳችሁ በጣም ቅርብ ናቸው፡፡»

13. ውስጣዊ እምነት እጅግ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው፡፡ ጣኦት አምላኪ ሙሽሪኮች እንኳ ይህን እውነታ በሚገባ ይረዱታል፡፡

## ምዕራፍ አሥራ አንድ
## ከአላህ ውጭ ላሉ ኀይላት መስዋዕት በሚቀርብበት ቦታ ለአላህ መስዋዕት አይቀርብም

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ لَا تَقُمْ فِيهِ أَبَدًا لَّمَسْجِدٌ أُسِّسَ عَلَى ٱلتَّقْوَىٰ مِنْ أَوَّلِ يَوْمٍ أَحَقُّ أَن تَقُومَ فِيهِ فِيهِ رِجَالٌ يُحِبُّونَ أَن يَتَطَهَّرُوا۟ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلْمُطَّهِّرِينَ ﴾

*«በርሱ ውስጥ በፍፁም አትስገድ፤ ከመጀመሪያ ቀን ይዞ በአላህ ፍራቻ ላይ የተመሠረተው (የቁባ) መስጊድ በውስጡ ልትሰግድበት ይልቅ የተገባው ነው፤ በሱ ውስጥ መጥራራትን የሚወዱ ወንዶች አልሉ፤ አላህም ተጥራሪዎችን ይወዳል::» (አል-ተውባህ: 108)*

ሳቢት ኢብን ዷሂክ እንዳስተላለፉት:-

«نَذَرَ رَجُلٌ أنْ يَنْحَرَ إبِلاً بِبُوانَةَ فَسَألَ النَّبِيَّ ﷺ فقالَ: هَلْ كَانَ فيهَا وَثَنٌ منْ أوثَانِ الجَاهِلِيَّةِ يُعْبَدُ؟ قَالُوا لا. قَالَ؛ فَهَلْ كَانَ فيهَا عِيدٌ مِنْ أعْيَادِهِمْ؟ قَالوا لا. فَقَال رَسُولُ الله ﷺ أَوْفِ بِنَذْرِكَ فإنَّهُ لاَ وَفَاءَ لِنَذْرٍ فِي مَعْصِيَةِ الله. ولاَ فِيمَا لاَ يَمْلِكُ ابنُ آدمَ».

አንድ ሰው «ቡዋነህ» ከተባለ ሥፍራ ላይ ግመል ለማረድ ስለት (ነዝር) ገባ:: «ከቦታው የሚመለክ የጃሂልያ ጣኦት ነበረን?» ሲሉ መልዕክተኛው ጠየቁ:: «አልነበረም» አሏቸው:: «ከበአላቶቻቸው አንዱ ከዚያ ቦታ ላይ ይፈፀም ነበረን?» ጠየቁ:: «በፍፁም» መለሱላቸው:: «ስለትህን አድርስ:: አላህን በመወንጀል ወይም በማይቻል ነገር ስለት አይሞላም» አሉ:: (አቡዳውድ ዘግበውታል)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል-ተውባህ 108» ትርጉም::

2. ወንጀል ሃጢአቱ የተፈፀመበትን አካባቢ ይበክላል:: ፅድቅ ተግባር ደግሞ በአካባቢው ላይ አዎንታዊ ተፅእኖ ያሳድራል::

3. ያልተብራራን ነጥብ ግልፅና የተብራራ በሆነው ነጥብ መመዘን::

4. ሸሪአዊ ብይን የሚሰጥ ግለሰብ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ዝርዝር ሁኔታዎችን ማጣራትና ማጥናት ይችላል::

5. ለእቀባ የሚያበቁ ምክንያቶች እስከሌሉ ድረስ ለስለት (ነዝር) የተለየን ቦት መምረጥ ይፈቀዳል::

6. ከአንድ ቦታ ላይ የሚመለክ የጃሂሊያ ጣኦት ካለ ወይም ከነበረ ያን ቦታ ለስለት መምረጥ የተከለከለ ነው::

7. ከጃሂሊያ በአላት አንዱ የሚከበርበት ከሆነም እንዲሁ ይከለከላል::

8. በእንዲህ ዓይነት ቦታዎች ላይ ሊፈፀም የታሰበ ስለት ውድቅ ነው:: ወንጀል በመሆኑ::

9. ሆነ ብለን እንኳ ባይሆን ከሙሽሪኮች ጋር በበአላቶቻቸው መመሳሰል የተከለከለ ነው::

10. ወንጀል በሆነ ነገር ላይ ስለት የለም::

11. ከአቅም በላይ በሆነ ነገርም ስለት የለም::

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት
## ከአላህ ውጭ ላለ አካል መሳል ሽርክ ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿يُوفُونَ بِٱلنَّذْرِ وَيَخَافُونَ يَوْمًا كَانَ شَرُّهُۥ مُسْتَطِيرًا﴾

*«(ዛሬ) በስለታቸው ይሞላሉ፣ መከራው ተሰራጭ የሆነንም ቀን ይፈራሉ::»(አል-ደሪሀር:7)*

﴿وَمَآ أَنفَقْتُم مِّن نَّفَقَةٍ أَوْ نَذَرْتُم مِّن نَّذْرٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُهُۥ﴾

*«ከምፅዋትም ማንኛውም የለገሳችሁትን፣ ወይም በስለት የተሳላችሁትን አላህ ያውቀዋል::» (አል-በቀራህ: 270)*

አዒሻ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) :-

«مَنْ نَذَرَ أَنْ يُطِيعَ الله فَلْيُطِعْهُ. ومَنْ نَذَرَ أَنْ يَعْصِيَ الله فَلاَ يَعْصِه».

«አላህን ሊያመልክ ስለት ያደረገ ስለቱን ይሙላ:: አላህን ለመወንጀል ስለት ያደረገ ስለቱን አይፈፅም» ብለዋል:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. ስለትን መሙላት ግዴታ ነው::

2. አምልኮ መሆኑ የታወቀን አንድ ነገር ከአላህ ውጭ ላሉ ሃይላት መስጠት ሽርክ ይሆናል::

3. ወንጀል የሆነን ስለት መሙላት አይፈቀድም::

# ምዕራፍ አሥራ ሦስት
# ከአላህ ውጭ ያሉ ኀይላትን ጥበቃ መሻት ሽርክ ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَأَنَّهُۥ كَانَ رِجَالٌ مِّنَ ٱلْإِنسِ يَعُوذُونَ بِرِجَالٍ مِّنَ ٱلْجِنِّ فَزَادُوهُمْ رَهَقًا ﴾

*«እነሆ ከሰዎች የሆኑ ወንዶች በጋኔን ወንዶች ይጠበቁ ነበር፤ ኩራትንም ጨመሩቻቸው::» (አል-ጂን: 6)*

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት ኸውላት ቢንት ሐኪም (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«مَنْ نَزَلَ مَنْزِلاً فَقَالَ: أَعُوذُ بِكَلِمَاتِ اللهِ التَّامَّاتِ مِنْ شَرِّ مَا خَلَقَ لَمْ يَضُرَّهُ شَيءٌ حَتَّى يَرْحَلَ مِنْ مَنْزِلِهِ ذَلِكَ».

«ወደ አንድ ቤት ሲገባ:- «ምሉዕ በሆነው የአላህ ቃል ከፍጡራን ሁሉ ክፋት እጠብቃለሁ» ያለ ቤቱን እስኪለቅ ድረስ የሚጎዳው ነገር አያገኘውም::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አልጂን 6» ትርጉም::

2. ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላትን ጥበቃ መሻት (ኢስቲጋሳ) ሽርክ ነው::

3. የአላህ ቃል ያልተፈጠረ ነው ለማለት ኡለሞች ይህንን ዘገባ እንደዋቢ ያቀርባሉ:: የፍጡራንን ጥበቃ መሻት ሽርክ በመሆኑ::

4. ይህ ዱዓ አጭር ቢሆንም እጅግ የላቀ ፋይዳ አለው::

5. አንድ ነገር ዱንያዊ ጥቅም የሚያስገኝ ወይም ከጉዳት የሚጠበቅ መሆኑ ብቻ ሽርክ ላለመሆኑ በአስረጅነት ሊቀርብ አይችልም::

# ምዕራፍ አሥራ አራት

## ከአላህ ሌላ ያሉ ኋይላትን መንፈሳዊ እገዛ መሻት (ኢስቲጋሳ) ወይም እነርሱን መማፀን (ዱዓእ) ሽርክ ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَلَا تَدْعُ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكَ وَلَا يَضُرُّكَ فَإِن فَعَلْتَ فَإِنَّكَ إِذًا مِّنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ○ وَإِن يَمْسَسْكَ ٱللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَ وَإِن يُرِدْكَ بِخَيْرٍ فَلَا رَآدَّ لِفَضْلِهِۦ يُصِيبُ بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ وَهُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴾

*«ከአላህ በቀር የማይጠቅምንና የማይጎዳን አትገዛ፤ ብትሰራም አንተ ያን ጊዜ ከበደለኞች ትሆናለህ (ተብያለሁ በላቸው::) አላህም ጉዳትን ቢያደርስብህ ከርሱ ሌላ ለርሱ ገላጭ የለውም:: በጉንም ነገር ቢሻል ለችሮታው መላሽ የለም፤ ከባሮቹ የሚሻውን ይለይበታል፤ እርሱም መሓሪ አዛኝ ነው::» (ዩኑስ:106)*

﴿ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَا يَمْلِكُونَ لَكُمْ رِزْقًا فَٱبْتَغُوا۟ عِندَ ٱللَّهِ ٱلرِّزْقَ وَٱعْبُدُوهُ وَٱشْكُرُوا۟ لَهُۥٓ إِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴾

*«እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዙዋቸው ለናንተ ሲሳይን ሊሰጧችሁ አይችሉም፤ ስለዚህ ሲሳይን ከአላህ ብቻ ፈልጉ፤ ተገዙትም፤ ለርሱም አመስግኑ፤ ወደርሱ ትመለሳላችሁ::» (አል-አንከቡት:17)*

﴿ وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ وَهُمْ عَن دُعَآئِهِمْ غَٰفِلُونَ ○ وَإِذَا حُشِرَ ٱلنَّاسُ كَانُوا۟ لَهُمْ أَعْدَآءً وَكَانُوا۟ بِعِبَادَتِهِمْ كَٰفِرِينَ ﴾

*«እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስም ለርሱ የማይመልስለትን ጣኦት ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማን ነው? እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው::» (አል-አሕቃፍ: 5)*

﴿ أَمَّن يُجِيبُ ٱلْمُضْطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكْشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجْعَلُكُمْ خُلَفَآءَ ٱلْأَرْضِ أَءِلَٰهٌ مَّعَ ٱللَّهِ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ ﴾

*«ወይም ያ ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል፤ መከራንም የሚያስወግድ፤ በምድር ላይ ምትኮች የሚያደርጋቸው፤ ከአላህ ሌላ አምላክ አለን? ጥቂትም አትገሰፁም?»(አል-ነምል፡ 62)*

ጠበራኒ እንዳስተላለፉት:-

«أنَّهُ كَانَ فِي زَمَنِ النَّبِيِّ ﷺ مُنَافِقٌ يُؤْذِي الْمُؤْمِنِينَ فَقَالَ بَعْضُهُم: قُومُوا بِنَا نَسْتَغِيثُ بِرَسُولِ الله ﷺ مِنْ هذَا الْمُنَافِقِ فَقَالَ النَّبِيُّ ﷺ إِنَّهُ لاَ يُسْتَغَاثُ بِي وإِنَّمَا يُسْتَغَاثُ بالله».

በአላህ መልዕክተኛ ዘመን ሙእሚኖችን የሚያውክ አንድ ሙናፊቅ ነበር:: «ተነሱ፤ ከዚህ ሙናፊቅ ተንኮል ይገላግሉን ዘንድ የአላህን መልዕክተኛ እገዛ እንጠይቅ» አሉ ከሙእሚኖች ከፊሎቹ:: «እኔን እገዛ መጠየቅ አይፈቀድም:: እገዛ የሚጠየቀው አላህ ብቻ ነው::» አሉ መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ)::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ለተወሰነ ተግባር ብቻ የሚያገለግሉ ዱዓዎችን የአላህን ጥበቃ መማፀንን ከሚገልፁ አጠቃላይ ዱዓዎች ጋር መደመር ለተለየ ዓላማ የሚውሰውን አጠቃላይ ግልጋሎት ካለው ላይ ማከል ነው::

2. የአንቀፅ «ዩኑስ 106» ትርጉም::

3. «ኢስቲጋሳ» ትልቅ ሽርክ (ሽርኩል አክበር) ነው::

4. የሰው ልጆች ሁሉ ፈርጥ የሆኑት ነብይ እንኳ ሰዎችን ለማርካት ሲሉ ይህንን ዘግናኝ ጥፋት ቢፈፅሙ ከበደለኞች እንደሚፈረጁ ተገልጿል::

5. የአንቀፅ «አልአንአም 17» ትርጉም::

6. ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላትን መንፈሳዊ እገዛ (ኢስቲጋሳ) መጠየቅ ኩፍር ከመሆኑም ባሻገር በዚህች ዓለምም ቅንጣት ፋይዳ የለውም::

7. የአንቀፅ «አል አንከቡት 17» ትርጉም::

8. ጀነት የሚጠየቀው አላህን ብቻ እንደሆነ ሁሉ «ሪዝቅ» (ሲሳይን) መጠየቅ የሚፈቀደውም እሱን ብቻ ነው::

9. የአንቀፅ «አልአህቃፍ 5» ትርጉም::

10. ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላትን ከሚጠራ (ከሚያመልክ) ሰው ይበልጥ የዘቀጠ እንደሌለ ተመልክቷል::

11. ከአላህ ውጭ የሚጥጠሩ ኃይላት የጠሪዎችን ጥሪ የሚያደምጡ አይደሉም:: መጠራታቸውንም አያውቁም::

12. ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላትን መጥራት አምልኮ ነው። የሚጥጠሩ አካላት ጠሪዎችን እስከመጨረሻው እንዲጠሉና እንዲርቁ ምክንያት የሆናቸውም ይኸው ነው።

13. ጥሪ ፥ የሚጥጠሩ አካላትን ማምለክ ነው።

14. ድርጊቱ ከሽርክ ተፈርጇል።

15. ከሰው ሁሉ ይበልጥ የዘቀጠ (የጠመመ) እንዲሆን ምክንያት የሆነው ከአላህ ውጭ ያሉ አካላትን መጥራቱ ነው።

16. የአንቀፅ «አል ነምል 62» ትርጉም፣

17. ጣኦት አምላክያን በችግር ጊዜ ደራሽ አላህ ብቻ እንደሆነ በሚገባ ይረዳሉ። ይቀበሉታልም። ለዚህም ነው መከራ ሲያገኛቸው፣ ችግር ሲገጥማቸው አላህን ብቻ የሚጠሩት፤ የርሱን እገዛ ብቻ የሚሹት። ይህ እጅግ የሚያስደንቅ ነገር ነው።

18. የአላህ መልዕክተኛ በተውሂድ ላይ የነበራቸው ፅኑና ጥንቁቅ አቋም።

# ምዕራፍ አሥራ አምስት
## (ፍጡራን ሲመለኩ አይገባም)

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ أَيُشْرِكُونَ مَا لَا يَخْلُقُ شَيْئًا وَهُمْ يُخْلَقُونَ ۝ وَلَا يَسْتَطِيعُونَ لَهُمْ نَصْرًا وَلَا أَنفُسَهُمْ يَنصُرُونَ ﴾

*«ምንም የማይፈጥሩትንና እነርሱም የሚፈጠሩትን በአላህ ላይ ያጋራሉን? ለነርሱም መርዳት የማይችሉትን? ነፍሶቻቸውንም የማይረዱትን?» (አል-አዕራፍ:191)*

﴿ وَالَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِهِ مَا يَمْلِكُونَ مِن قِطْمِيرٍ ۝ إِن تَدْعُوهُمْ لَا يَسْمَعُوا دُعَاءَكُمْ وَلَوْ سَمِعُوا مَا اسْتَجَابُوا لَكُمْ وَيَوْمَ الْقِيَامَةِ يَكْفُرُونَ بِشِرْكِكُمْ وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثْلُ خَبِيرٍ ﴾

*«እነዚያ ከርሱ ውጭ የምትገዟቸው የተምር ፍሬ ሽፋን እንኳ አይኖራቸውም:: ብትጠሯቸው ጥሪያቸውን አይሰሙም፤ ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም፤ በትንሳኤ ቀን (እነርሱም በአላህ) ማጋራታችሁን ይክዳሉ፤ እንደ ውስጠ አዋቂው ማንም አይነግርህም::»(ፋጢር :13)*

በሰሒሕ የሐዲስ ዘገባ እንደተመለከተው:-

«شُجَّ النَّبِيُّ ﷺ يَوْمَ أُحُدٍ وكُسِرَتْ رَبَاعِيَتُهُ، فَقَالَ كَيْفَ يُفْلِحُ قَوْمٌ شَجُّوا نَبِيَّهُمْ فَنَزَلَتْ: ﴿لَيْسَ لَكَ مِنَ الأَمْرِ شَيْءٌ﴾

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የኡሁድ ዕለት የመፈንከት አደጋ ደረሰባቸው:: ጥርሳቸው ተሰበረ:: «ነብያቸው የመፈንከት አደጋ የደረሰበት ህዝቦች እንዴት ለድል ይበቃሉ አሉ::» ይሄኔ አላህ:- «ላንተ ከነገሩ ምንም የለህም» (አል ዒምራን: 128) የሚለውን ቁርአናዊ ቃል አወረደ::

በሌላ ሶሒሕ ዘገባ እንደተወሳው ኢብን ዑመር (ረዐ) ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«أنَّه سَمع رسول الله ﷺ يقول إذا رَفَعَ رأسه من الركوع في الركعةِ الأخيرةِ من الفجرِ: اللهُمَّ العَنْ فُلاناً وفُلاناً بَعْدَ مَا يَقُولُ سَمِعَ الله لِمَنْ حَمِدَه ربَّنا ولَكَ الحَمْدُ فأنْزَلَ الله: ﴿لَيْسَ لَكَ مِنَ الأَمْرِ شَيْءٌ﴾»

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከፈጅር የመጨረሻው ረከዓ ከሩኩዕ ሲነሱ:- «ሰሚዐላሁ ሊመን ሐሚደህ ረበና ለከል ሐምድ» ካሉ በኋላ:- «አላህ ሆይ! በእገሌ፣ በእገሌ ላይ መርግምትህን አውርድ» በማለት ዱዓ ሲያደረጉ አድምጫለሁ:: አላህ:- «ላንተ ከነገሩ ምንም የለህም» የሚለውን የቁርአን አንቀፅ አወረደ::

በሌላ ዘገባ እንደተወሳው ደግሞ መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ):-

«يَدْعُو عَلَى صَفْوانَ بن أُمَيَّةَ وَسهَيْل بن عَمرٍو والحَارِثَ بن هِشَام فَنَزَلَتْ: ﴿لَيْسَ لَكَ مِنَ الأمْرِ شَيءٌ﴾.

በሱፍያን አብን ኡመየህ፣ በሱሃይል ኢብን ዑመርና በሐሪሥ ኢብን ሐሽም ላይ ዱዓ ያደርጉ ነበር:: አላህም:- «ላንተ ከነገሩ ምንም የለህም» የሚል የቁርአን አንቀፅ አወረደ::

በሰሒሕ ዘገባ እንደተላለፈው አቡሁረይራ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

«قامَ رَسُولُ الله ﷺ حِينَ أُنْزِلَ عَلَيهِ: ﴿وَأَنذِرْ عَشِيرَتَكَ ٱلْأَقْرَبِينَ﴾ فَقَالَ يَا مَعْشَرَ قُرَيْشٍ أَوْ كَلِمَةً نَحْوَهَا: اشْتَرُوا أَنْفُسَكُم لا أُغْنِي عَنْكُمْ مِنَ الله شَيئاً. يَا عَبَّاسَ بنَ عَبدِ المُطَّلِبِ! لا أُغْنِي عَنْكَ مِنَ الله شَيئاً. يَا صَفِيَّة عَمَّةَ رَسُولِ الله لا أُغْنِي عَنْكِ مِنَ الله شَيئاً. ويا فَاطِمَةَ بِنْتَ مُحَمَّدٍ سَلِينِي مِنْ مَالِي مَا شِئْتِ لا أُغْنِي عَنْكِ مِنَ الله شيئاً».

«የቅርብ ዘመዶችህን አስጠንቅቅ» የሚለው የቁርአን አንቀፅ የወረደ እለት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) «ህዝበ- ቁረይሽ ሆይ! ነፍሶቻችሁን ከጥፋት አድኑ! ከአላህ ዘንድ ቅንጣት የምፈይዳችሁ ነገር የለም:: አባሲ ኢብን አብዱል ሙጦልብ ሆይ! ከአላህ ዘንድ የምፈይድህ ነገር የለም:: አክስቴ ሶፍያ ሆይ! ከአላህ ዘንድ ቅንጣት የምፈይድሽ ነገር የለም:: የሙሐመድ ልጅ ፋጡማ ሆይ! ከገንዘቤ ያሻሽን ጠይቂኝ:: ከአላህ ዘንድ ግን ቅንጣት የምፈይድሽ ነገር የለም::» የሚል የአዋጅ ቃል አሰሙ::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አልአዕራፍ 191» እና «የአንቀፅ ፋጢር 13» ትርጉም::

2. የኡሁድ ዘመቻ ታሪክ ቅንጫቢ::

3. የነቢያት ፈርጥ የሆኑት ነብይ ያደርጉት የነበረው ዱአ:: ከበስተጀርባቸው የነበሩ ታላላቅ ሶሃቦች ሶላት ውስጥ ቆመው «አሚን» በማለት ዱአቸውን ይቀበሉ ነበር::

4. ዱዓ ይደረግባቸው የነበሩ ሰዎች ካፊሮች ናቸው::

5. እነኚህ ሰዎች አብዛኛዎቹ ካፊሮች የማይፈፅሙትን ወንጀል ፈፅመዋል:: ነቢዩን ፈንክተዋል:: የግድያ ሙከራዎችን አድርገውባቸዋል:: የቅርብ ዘመዶቻቸው የሆኑ ታላላቅ ሶሃቦችን ሙት አካል በመቆራረጥ ጭራቃዊ ድርጊት ፈፅመዋል::

6. አላህ ይህን በማስመልከት:- «ላንተ ከነገሩ ምንም የለህም» የሚል ቁርአናዊ ቃል አወረደ::

7. «ወይ ተውበት ያደርጋሉ፤ አሊያም ይቀጣቸዋል::»

በሚል ነበር አላህ አንቀፁን ያሳረገው:: ተውበት ያደረጉት ምህረት ተለግሷቸዋል::

8. አንዳች ችግር ሲገጥም «ቁኑት» ማድረግ በሸሪአው የተደነገገ ነው::

9. ዱዓ የሚደረግባቸውን ግለሰቦችና የወላጆቻቸውንም ስም ሶላት ውስጥ መጥቀስ ይፈቀዳል::

10. «ቁኑት» ላይ አንድን ግለሰብ ለይቶና በስም ጠርቶ መርገም ይፈቀዳል::

11. «የቅርብ ዘመዶችህን አስጠንቅቅ»

የሚለው የቁርአን አንቀፅ በወረደበት ወቅት የተከሰተው የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ውሎ::

12. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ለሩቅም ለቅርብ ዘመዶቻቸውም:- «ከአላህ ዘንድ ቅንጣት አልፈይዳችሁም» ሲሉ ማወጃቸው ተወስቷል::

«የሙሐመድ ልጅ ፋጡማ ሆይ! ከአላህ ዘንድ ቅንጣት አልፈይድሽም» በማለት እቅጩን ተናግረዋል:: እጅግ ታማኙና የነቢያት ሁሉ አለቃ የሆኑት ነቢይ (ሶ.ዐ.ወ) ለአለማት እንስቶች ፈርጥ ለፋጡማ (ረዐ) ይህንን መናገራቸውን በአሁኑ ሰዓት አንዳንድ የዋሆች ከሚፈፅሙት ተግባር ጋር ስናገናዝብ ተውሂድ ምን ያህል ችላ እንደተባለና ኢስላም ምን ያህል እንግዳ እንደሆነ እንረዳለን::

# ምዕራፍ አሥራ ስድስት
## መለኮታዊ መልዕክት

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿حَتَّىٰٓ إِذَا فُزِّعَ عَن قُلُوبِهِمْ قَالُوا۟ مَاذَا قَالَ رَبُّكُمْ ۖ قَالُوا۟ ٱلْحَقَّ ۖ وَهُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْكَبِيرُ﴾

*«ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤ በተገለጠ ጊዜ (ተማላጆቹ) ጌታችሁ ምን አለ? ይላሉ፤(አማላጆቹ) እውነትን አለ፤ እርሱም ከፍተኛውና ታላቁ ጌታ ነው ተ ይላሉ::» (ሰበዕ: 23)*

ቡኻሪ አቡሁረይራን (ረዐ) ጠቅሰው እንደዘገቡት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ተናግረዋል :-

«إذَا قَضَى الله الأمْرَ فِي السَّماءِ ضربَتِ الملائِكَةُ بِأجْنِحَتِهَا خُضْعاناً لِقَوْلِهِ كأنَّهُ سِلْسِلَةٌ عَلى صَفْوانٍ يَنْفُذُهُمْ ذَلِكَ حتَّى إذَا فُزِّعَ عَنْ قُلُوبِهِمْ قَالُوا مَاذَا قَالَ رَبُّكُمُ قَالوا الحَقَّ وهُوَ العَليُّ الكَبِيرُ فَيَسْمَعُهَا مُسترِقُ السَّمْعِ. ومُسْتَرِقُ السَّمْعِ هكَذَا بَعْضُهُ فَوْقَ بَعْضٍ. وصَفَهُ سُفْيَانُ بِكَفِّهِ فَحَرَّفَهَا وَبَدَّدَ بَيْنَ أصَابِعِهِ فَيَسْمَعُ الكَلِمَةَ فَيُلْقِيهَا إلى مَنْ تَحتَه ثُمَّ يُلْقِيهَا الآخَرُ إلى مَنْ تَحْتَه حتَّى يُلْقِيهَا عَلى لِسَانِ السَّاحِرِ أو الكَاهِنِ فَرُبَّمَا أدْرَكَهُ الشِّهابُ قَبْلَ أنْ يُلْقِيهَا. ورُبَّما ألْقَاهَا قَبْلَ أنْ يُدركهُ فَيَكْذِبُ مَعَهَا مائَةَ كَذْبَةٍ فَيُقَالُ ألَيْسَ قَدْ قَالَ لَنَا يَوْمَ كَذَا وكَذَا كَذَا وكَذَا فَيصدَّقُ بِتِلْكَ الكَلِمَةِ التي سُمِعَتْ مِنَ السَّماءِ»

«አላህ አንድ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ወቅት መላኢኮች በታዛዥነት ክንፋቸውን ይመታሉ:: ውሳኔውንም በፀጋ ይቀበላሉ:: ድንጋጤው ሲለቃቸው:- «ጌታችሁ ምን አለ?» በማለት ይጠይቃሉ:: «እውነትን ተናግሯል፤ ልዕልናው ታላቅ ነው::» የሚል ምላሽ ያገኛሉ:: ሸይጧን ውይይታቸውን ያዳምጥና ለበታቹ ያቀብለዋል:: ያኛው ለሚቀጥለው እያለ በመጨረሻ ጠንቋዩ ዘንድ ይደርሳል:: ሸይጧኑ ወሬውን ከማቀበሉ በፊት ተወርዋሪ ኮከብ አግኝቶ ሊመታው ወይም ሊስተውና ወሬውን ሊያቀብል ይችላል፡፡ ጠንቋዩ መቶ ውሸቶችን ጨማምሮባቸው ያወራል:: «አንድ ቀን እንዲህ እንዲህ በማለት ነግሮን ነበር:: ያለው አልሆነምን?»

ይባላል:: ሸሽማይ ባደመጣት አንዲት ንግግር ሰበብ ከሰዎች ዘንድ ተቀባይነትን ያገኛል::

ነዋስ ኢብን ሰምአን እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል :-

«إذَا أرادَ الله تَعَالى أنْ يُوحِيَ بالأمْرِ تكَلَّمَ بالوَحْيِ أَخَذَتِ السَّمواتُ مِنهُ رَجْفَةً أوْ قَالَ رَعْدَةً خَوفاً مِنَ الله تعالى. فَإذَا سَمِعَ ذَلِكَ أهْلُ السَّمواتِ صُعِقُوا وخَرُّوا لله سُجَّداً فَيَكونُ أوَّلَ مَنْ يَرْفَعُ رأسَهُ جِبريلُ فَيُكَلِّمُهُ الله مِنْ وَحْيِهِ بمَا أرَادَ. ثُمَّ يَمُرُّ جِبريْلُ عَلَى المَلائِكَةِ كُلَّمَا مَرَّ بِسَماءٍ سَألَهُ مَلائِكَتُهَا مَاذا قَالَ رَبُّنَا يَا جِبْرِيلُ، فَيَقُولُ جبريلُ: قَالَ الحَقَّ وهُوَ العَلِيُّ الكَبيرُ. فَيَقُولونَ كُلُّهُمْ مِثْلَ مَا قَالَ جِبْرِيلُ. فَيَنْتَهِي جِبريلُ بالوَحْيِ إلى حَيْثُ أَمَرَهُ الله تعالى»

«አላህ አንድን መልዕክት ማስተላለፍ በሚፈልግበት ወቅት ያንን ወህይ (ራዕይ) ይናገራል:: ሰማያት አላህን ከመፍራት የተነሳ ይርዳሉ:: የሰማየሰማያት ነዋሪዎችም ይህንን ሲያደምጡ ይንቀጠቀጣሉ:: ለአላህ ሱጁድ ይወርዳሉም:: በመጀመሪያ ራሱን ከሱጁድ የሚያነሳው ጅብሪል ነው:: አላህ ከወህዩ የሚሻውን ይነግረዋል:: ከዚያም ጀብሪል በመላኢኮች መሀከል ያልፋል:: በሰማያት ባለፈ ቁጥር «ጅብሪል ሆይ! ጌታችን ምን አለ?» በማለት መላኢኮች ይጠይቁታል:: «እውነትን ተናገረ:: እጅግ የተላቀና ልዑል አምላክ ነው» ይላቸዋል:: ሁሉም ጀብሪል የተናገረውን ያስተጋባሉ:: ጅብሪል ወህዩን ይዞ ከተፈለገው ቦታ ይደርሳል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «ሰበእ 23» ትርጉም

2. ሽርክን፣ በተለይም ከደጋግ ሰዎች ጋር ተያያዥነት ያለው ከሆነ፣ በማጋለጡ ረገድ ይህ አንቀፅ ጠንካራ ዋቢ ነው:: የሽርክን ስረመሠረት ከልቦና ላይ አውጥቶ የሚጥል ኃይል አለው፣ ተብሎለታል::

3. «እውነትን አለ፤ እርሱም ከፍተኛው ታላቁ ጌታ ነው» የሚለው ቁርአናዊ ቃል ትርጉም::

4. መላኢኮች ስለዚህ ቃል የመጠየቃቸው ሰበብ::

5. ጅብሪል ከጠየቁት በኋላ «እንዲህ፣ እንዲህ አለ» የሚል ምላሽ ይሰጣቸዋል::

6. መጀመሪያ ከሱጁድ ራሱን የሚያቀናው ጀብሪል እንደሆነ ተወስቷል::

7. ለሚጠይቁት የሰማየ ሰማያት ነዋሪዎች ሁሉ ምላሽ ይሰጣል::

8. ሁሉም የሰማየ ሰማያት ነዋሪዎች በፍርሃት ይርዳሉ::

9. ሰማያት በአላህ ንግግር መንቀጥቀጣቸው ተወስቷል::

10. ለሚፈለገው አካል ወህይ የማድረሱ ተግባር የሚፈፀመው በጀብሪል አማካይነት ነው::

11. ሸይጧኖች ከሰማይ ወሬ ይቀዳሉ::

12. ሸይጧኖች እርስ በርስ እንዴት እንደሚደራረቡ::

13. ከዋክብት በወሬ ለቃሚ ሰይጣናት ላይ እንደሚወረወሩ::

14. አንዳንድ ጊዜ ሸይጧኖች ወሬ ከማቀበላቸው በፊት የከዋክብት ጥቃት ይደርስባቸዋል:: አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ከአደጋው አምልጠው ለጅንና ለሰው ወዳጆቻቸው የለቃቀሙትን ወሬ ያቀብላሉ::

15. ጠንቋይ አንዳንድ ጊዜ እውነትን ሊናገር እንደሚችል::

16. ከአንዲት እውነት ጋር መቶ እብለቶችን እንደሚቀላቅል::

17. እብለቱ በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት የሚያገኘው ከሰማይ በደረሰችው አንዲት እውነት ሳቢያ ነው::

18. የሰዎች ነፍሶች ከንቱ ነገሮችን (ባጢልን) ለመቀበል ያላቸው ዝግጁነት:: ለአንዷ እውነት ትኩረት ሲቸሩ መቶ ሀሰቶችን ግን አያስተውሉም::

19. ሰዎች ከጠንቋይ የሰሟትን አንዲት እውነት እርስ በርስ እየተቀባበሉ ያደንቃሉ:: ያችን እውነት ለጠንቋዩ ትክክለኛነት እንደዋቢ ይጠቀሙባታል::

20. የአላህን ባህሪያት ማወቅ::

21. የፍጡራን በአላህ ፍርሃት መራድና መርገፍገፍ::

22. መላኢኮች ለአላህ ሱጁድ እንደሚወርዱ::

# ምዕራፍ አሥራ ሰባት
## ምልጃ(ሸፋዐ)

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَأَنذِرْ بِهِ ٱلَّذِينَ يَخَافُونَ أَن يُحْشَرُوٓا۟ إِلَىٰ رَبِّهِمْ ۙ لَيْسَ لَهُم مِّن دُونِهِۦ وَلِىٌّ وَلَا شَفِيعٌ لَّعَلَّهُمْ يَتَّقُونَ﴾

*«እነዚያን ከርሱ ሌላ ረዳትና አማላጅ የሌላቸው ሲሆኑ ወደ ጌታቸው መሰብሰብን የሚፈሩትን ይጠነቀቁ ዘንድ በርሱ (በቁርአን) አስፈራራ::» (አል-አንዓም:51)*

﴿ قُل لِّلَّهِ ٱلشَّفَـٰعَةُ جَمِيعًا ﴾

*«ምልጃ ሁሉም የአላህ ብቻ ነው»(አል-ዙመር :44)*

﴿ مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذْنِهِۦ ﴾

*«ያ ከእርሱ ዘንድ በፍቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማን ነው?» (አል-በቀራህ:255)*

﴿ ۞ وَكَم مِّن مَّلَكٍ فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ لَا تُغْنِى شَفَـٰعَتُهُمْ شَيْـًٔا إِلَّا مِنۢ بَعْدِ أَن يَأْذَنَ ٱللَّهُ لِمَن يَشَآءُ وَيَرْضَىٰٓ ﴾

*«በሰማያት ውስጥ ካሉ መላዕክትም ብዙዎቹ ሊማለዱት ለሚሻውና ለሚወደው ሰው ከፈቀደ በኋላ እንጂ ምልጃቸው ምንም አይጠቅምም::» (አል- ነጅም :26)*

﴿ قُلِ ٱدْعُوا۟ ٱلَّذِينَ زَعَمْتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ ۖ لَا يَمْلِكُونَ مِثْقَالَ ذَرَّةٍ فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَلَا فِى ٱلْأَرْضِ وَمَا لَهُمْ فِيهِمَا مِن شِرْكٍ وَمَا لَهُۥ مِنْهُم مِّن ظَهِيرٍ ○ وَلَا تَنفَعُ ٱلشَّفَـٰعَةُ عِندَهُۥٓ إِلَّا لِمَنْ أَذِنَ لَهُۥ ﴾

*«እነዚያን ከአላህ ሌላ አማልክት ብላችሁ የምትጠሯቸውን ጥሩ! በሰማያትም በምድርም ውስጥ የብናኝ ክብደት ያክል ምንም አይችሉም:: ለነርሱ በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም:: ከነርሱም ለርሱ ምንም አጋዥ የለውም፥ በላቸው:: ምልጃ እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ ከርሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም::» (ሰበዕ: 22-23)*

አቡል አባስ እንደሚሉት ሙሽሪኮች ከአላህ ውጭ ያሉ ኃይላት ይፈፅሟቸዋል በሚል ተስፋ ያደረጉባቸውን ነገሮች ሁሉ ከርሱ ሌላ ያሉ አካላት ሊፈፅሟቸው አቅሙ እንደሌላቸው በግልፅ

ሰፍሯል:: ከአላህ ውጭ ኃይልና ችሎታ ያለው አካል የለም:: ረዳትም የለውም:: ምልጃ ብቻ ነበር በዚህ መልኩ ሳይብራራ የቀረው:: እርሱንም በፈቃዱ ብቻ እንደማይከናወን:-

﴿وَلَا يَشْفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ٱرْتَضَىٰ﴾

*«ለወደደው ሰው እንጂ ለሌላ አያማልድም»*

በማለት አብራርቷል:: ሙሽሪኮች ተገቢያቸው እንደሆነች ተስፋ ያደረጓት ሸፈአ (ምልጃ) የቂያማ ቀን ትነፈጋቸዋለች:: ቁርዓን እንደማትፈቅድላቸው ገልጿል::

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንደተናገሩት:-

«أنَّهُ يَأتِي فَيَسْجُدُ لِرَبِّهِ ويَحْمَدُهُ لاَ يَبْدَأُ بالشَّفَاعَةِ أوَّلاً ثُمَّ يُقَالُ لَهُ: ارْفَعْ رَأْسَكَ وَقُلْ يُسْمَعُ وَسَلْ تُعْطَ واشْفَعْ تُشَفَّعْ».

የቂያማ እለት ሸፈአ ከመጠየቃቸው በፊት ለአላህ ሱጁድ ይወርዳሉ:: ያመሰግኑታልም:: «ራስህን ከሱጁድ አንሳ:: ተናገር፤ተሰሚነት ይኖርሃል:: ጠይቅ ፤ ትሰጣለህ:: ምልጃ ተማፀን፤ ይፈቀድልሃል» ይባላሉ::

አቡሁረይራ:-

«مَنْ أسْعَدُ النَّاس بشَفَاعَتِكَ يَا رَسُولَ الله؟ قَالَ مَنْ قالَ لاَ إلـهَ إلاَّ الله خَالِصاً مِنْ قَلْبِهِ».

«የእርስዎን ሸፈአ ለማግኘት የታደለ ሰው እንዴት አይነቱ ነው?» በማለት ጠየቋቸው:: «ከልቡ በፍፁም ቅንነትና ታማኝነት (ኢኽላስ) ላኢላሃ ኢለላህን ያለ::» በማለት መለሱ::

በአላህ ፈቃድ በተውሂድ (ኢኽላስ) ላይ የፀኑት ብቻ ናቸው የነብዩን ምልጃ የሚያገኙት:: ሙሽሪኮች ፈፅሞ ለዚህ ዕድል አይበቁም::

በአጭሩ ለማስቀመጥ ያህል ሸፈአን የሚፈቅደው አላህ ብቻ ሲሆን የሚፈቅደውም ለተውሂድ ሰዎች ብቻ ነው:: ሊያልቀውና የተከበረን ደረጃ ሊያጎናፅፈው ይታደል ዘንድ በፈቀደለት ግለሰብ ዱዓ አማካይነት::

ቁርአን ተቀባይነት እንደሌለው የገለፀው ሽርክ የተቀላቀለበትን ትድግና(ሸፈአ) ነው:: ለዚህም ነው በሌሎች አናቅፅ ላይ በአላህ ፈቃድ ተፈፃሚነት የሚኖረው ሸፈአ እንዳለ

ያስቀመጠው:: ለእንዲህ አይነቱ ሸፋአ የታደሉት የተውሂድና የኢኽላስ ባለሀብቶች ብቻ እንደሆኑ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተናግረዋል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ከላይ የተጠቀሱ የቁርአን አንቀፆች ትርጓሜ::
2. ተቀባይነት እንደሌለው የተገለፀው የሸፋአ አይነት::
3. ተቀባይነቱ የፀደቀለት የሸፋአ ዓይነት::
4. ታላቁ የትድግና ክንውን (ሸፋአተልኩብራ) «መቃመል መሕሙድ» ላይ እንደሚፈፀም::
5. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በሸፋአ እንደማይጀምሩ፤ መጀመሪያ ሱጁድ ይወርዳሉ:: ሲፈቀድላቸው ሸፋአን ይጠይቃሉ::
6. ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ትድግና የታደለ የሰው አይነት::
7. በአላህ ላይ ያሻረኩ ሰዎች ይህን ታላቅ እድል አያገኙም::
8. የሸፋአ ምንነትና ባህሪ::

# ምዕራፍ ሰሥራ ስምንት
# አላህ የሚፈልገውን ሰው ወደቀጥተኛ መንገድ ይመራል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿إِنَّكَ لَا تَهْدِي مَنْ أَحْبَبْتَ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَهْدِي مَن يَشَآءُ وَهُوَ أَعْلَمُ بِٱلْمُهْتَدِينَ﴾

*«አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም:: ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል:: እርሱም ቅኖቹን አዋቂ ነው::» (አል-ቀሰስ:56)*

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት መሰየብ አባታቸውን ዋቢ በማድረግ ተከታዩን ዘገባ አስተላልፈዋል:-

«قَالَ لَمَّا حَضَرَتْ أَبَا طَالِبٍ الوَفَاةُ جَاءَهُ رَسُولُ الله ﷺ وعِنْدَهُ عَبْدُ الله بنُ أُمَيَّةَ وأَبُو جَهْلٍ فقَالَ لَهُ يَا عَمِّ! قُلْ لا إلـهَ إلاَّ الله كَلِمَةً أُحاجُّ لَكَ بِهَا عِنْدَ الله، فَقَالا لَهُ أَتَرْغَبُ عَنْ مِلَّةِ عَبْدِ المُطَّلِبِ؟ فَأَعَادَ عَلَيْهِ النَّبِيُّ ﷺ فَأَعَادَا فَكَانَ آخِرُ مَا قَالَ، هُوَ عَلى مِلَّةِ عَبْدِ المُطَّلِبِ وأَبَى أَنْ يَقُولَ لا إلـهَ إلاَّ الله. فَقَالَ النَّبِيُّ ﷺ لأَسْتَغْفِرَنَّ لَكَ مَا لَمْ أُنْهَ عَنْكَ. فأنْزَلَ الله عزَّ وجلَّ: ﴿مَا كَانَ للنَّبِيِّ والذِينَ آمَنُوا أَنْ يَسْتَغْفِرُوا للمُشْرِكِينَ ولَوْ كَانُوا أُولِي قُرْبَى﴾. وأنزلَ الله في أبي طَالِبٍ: ﴿إِنَّكَ لا تَهْدِي مَنْ أَحْبَبْتَ ولكِنَّ الله يَهْدِي مَنْ يَشَاءُ وَهُوَ أَعْلَمُ بِالمُهتَدِينَ﴾.

አቡ ጧሊብ ከሞት አፋፍ ላይ በነበሩበት ወቅት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከርሳቸው ዘንድ መጡ:: አብደላህ ኢብን አቢ ኡመያህና አቡጀህል ከአቡ ጧሊብ ጋር ነበሩ:: «አጎቴ ሆይ! ላኢላሃ ኢለላህ በል፣ ከአላህ ዘንድ በአስረጅነት የማቀርብልህ ቃል ናት::» ሲሉ መልዕክተኛው አቡጧሊብን ጠየቋቸው:: «ከአብዱል ሙጦሊብ መንገድ ታፈነግጣለህን?» አሉ አቡጀህልና አብደላህ ኢብን ኡመያህ:: ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) በድጋሚ ተማፀኗቸው:: ሁለቱም ግለሰቦች ያሉትን ደገሙ:: አቡ ጧሊብ በመጨረሻ በአብዱል ሙጠሊብ መንገድ መፅናተቸውን ተናገሩ:: ላኢላሃ ኢላላህ በማለት

ፈቃደኛ አልሆኑም:: «እስክከለከል ድረስ ከአላህ ዘንድ ምህረትን እማፀንልሃለሁ» አሉ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ):: አላህም:- «ለነቢዩና ለነዚያ ላመኑት ለአጋሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች ቢሆኑም እንኳ እነሱ ከሃዲዎች የእሳት ጓዶች መሆናቸው ከተገለፀላቸው በኋላ ምህረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም::» (አልተውባህ 113) የሚል የቁርአን አንቀፅ አወረደ:: አቡጧሊብን አስመልክቶም :- «አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም፤ ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል:: እርሱም ቅኖቹን አዋቂ ነው»(አል-ቀሶስ:26) የሚል መለኮታዊ ቃል አወረደ:.

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አልቀሰስ 26» ትርጉም::

2. የአንቀፅ «አልተውባህ 113» ትርጉም::

3. የላ ኢላሃ ኢለላህ ትክክለኛ ትርጓሜ ተገልጿል:: ኡለማዕ የሚባሉ ክፍሎች ይህንን ነጥብ በተዛባ መልኩ ሲረዱት ይስተዋላሉ:: እጅግ ከፍተኛ ትኩረት ሊቸረው ይገባል::

4. ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) አቡጧሊብን «ላ ኢላሃ ኢለላህ በል» እያሉ በሚማፀኑበት ወቅት አቡጀህልና ባልደረቦቹ የዚህችን ቃል ትክክለኛ ምንነትና ትርጓሜ ይረዱ ነበር:: የኢስላምን መሠረተ አስመልክቶ ከአቡ ጀህል ያነሰ እውቀት ያለው ሰው እጅግ አሳፋሪ ከሆነ የድንቁርና ዝቅጠት ውስጥ ነው::

5. ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ኢስላምን በማድረሱ ረገድ የነበራቸው ብርታትና አጎታቸው ኢስላምን እንዲቀበሉ የነበራቸው ጉጉት::

6. አብዱል ሙጦሊብና አያት ቅድመ አያቶቻቸው ኢስላም ውስጥ እንደነበሩ ይነገራል:: ሀሰት መሆኑን ከዚህ ዘገባ እንረዳለን::

7. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ለአጎታቸው አብዱል ሙጦሊብ ከአላህ ዘንድ ምህረትን ይማፀኑ ነበር:: ተቀባይነት አላገኙም:: ምህረት እንዳይለምኑ እቀባ ተደርጎባቸዋል::

8. መጥፎ ጓደኛ በሰዎች ላይ የሚያደርስው አስከፊ ጉዳት::

9. ለመሪዎችና ለቅድመ አያቶች ከተገቢው በላይ ክብር መቸር የሚያስከትለው ጥፋት::

10. ጃሂሊያው በዋቢነት የሚያቀርበው የመሪዎችንና የአያቶችን እምነትና ተግባር ነው::

11. የአንድ ተግባር ጠቀሜታ መቋጫው ላይ መሆኑን ከተጠቀሰው ዘገባ እንረዳለን:: አብዱል መጦሊብ በመጨረሻው የህይወት እስትንፋሳቸውም እንኳ «ላኢላሃ ኢለላህ» ቢሉ ኖሮ ከእሳት ነፃ ይወጡ ነበር::

12. ይህ «ሹብሐ» ትክክለኛውን እምነት በሳቱ ሰዎች ልቦና ውስጥ የተቸረው ትልቅ ቦታ ትኩረትን ይስባል። አጥብቀው የተከራከሩበት ነጥብ ይህችው ብቻ እንደሆነች ታሪክ ያመለክታል። መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) አፅንኦት ሰጥተው በተደጋጋሚ ለማብራራት ሞክረዋል። ታላቅና ግልፅ በመሆኗ ነው ሊዘሏት ያልፈለጉት።

## ምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ

## ለሰው ልጆች ክህደትና ዲናቸውን መተው ምክንያቱ ለደጋግ ሰዎች ያላቸው የተጋነነ አመለካከት ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ لَا تَغۡلُواْ فِي دِينِكُمۡ وَلَا تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ إِلَّا ٱلۡحَقَّۚ﴾

*«እናንተ የመፅሐፍ ሰዎች ሆይ! በሀይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ፤ በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ» (አል ኒሳዕ:171)*

﴿وَقَالُواْ لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمۡ وَلَا تَذَرُنَّ وَدّٗا وَلَا سُوَاعٗا وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ وَنَسۡرٗا﴾

*«የውቅንም፣ ነስርንም አትተው» (ኑህ :23)*

የሚለውን የቁርአን አንቀፅ ኢብን ዓባስ ሲያብራሩ :-

«هَذِهِ أَسْمَاءُ رِجَالٍ صَالِحِينَ مِنْ قَوْمِ نُوحٍ فَلَمَّا هَلَكُوا أَوْحَى الشَّيْطَانُ إِلى قَوْمِهِمْ أَنْ انْصِبُوا إِلَى مَجَالِسِهِمُ الَّتِي كَانُوا يَجْلِسُونَ فِيهَا أَنْصَاباً وسَمُّوهَا بِأَسْمَائِهِمْ فَفَعَلُوا وَلَمْ تُعْبَدْ حتَّى إِذَا هَلَكَ أُولَئِكَ وَنَسِيَ العِلْمُ عُبِدَتْ»

«እነኚህ በአንቀፁ ላይ የተጠቀሱ ስሞች ከኑህ ህዝቦች ውስጥ የደጋግ ሰዎች መጠሪያዎች ነበሩ:: ሁሉም ለህልፈት ሲበቁ ሸይጣን ለህብረተሰባቸው ይቀመጡበት ከነበረው ሥፍራ ላይ ሀውልቶች ትከሉ እና በየስሞቻቸው ሰይሟቸው የሚል ሪዕይ አስተላለፈ:: ያላቸውን ፈፀሙ:: ግን ሀውልቶችን አላመለኩም:: ይህን ያደረገው ትውልድ አለፈ:: እውቀት ጠፋ:: ቀስ በቀስ ለመመለክ በቁ::»

ኢብኑል ቀይም እንደሚሉት እነኚህ ደጋግ ሰዎች ሲሞቱ ህብረተሰቡ ከመቃብራቸው ላይ ተቀመጠ:: ሀውልቶችን ገነባም:: ጊዜ እየረዘመ ሲሄደ ለመታሰቢያነት የታነፁ ሀውልቶች ለመመለክ በቁ::

ዑመር (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ):-

«لا تُطْرُونِي كمَا أطْرَتِ النَّصَارَى ابنَ مَرْيَمَ. إنَّمَا أنَا عَبْدٌ فَقُولُوا عَبْدُ الله ورَسُولُه».

«ክርስቲያኖች የማርያምን ልጅ ኢሳን ከተገቢው በላይ እንዳላቁት፥ የኔንም ክብር ከሚገባው በላይ ከፍ አታድርጉ:: እኔ የአላህ ባሪያ ነኝ የአላህ መልዕክተኛና ባሪያ ብቻ በሉኝ::» ብለዋል:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

እንዲህም ሲሉ ተደምጠዋል:-

«إيَّاكُمْ والغُلُوَّ فإنَّمَا أهْلَكَ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمُ الغُلُوّ».

«ፅንፈኝነትን አደራ ተጠንቀቁ:: ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ለጥፋት የዳረገው ፅንፈኝነት ነው::»

ሙስሊም ኢብኑ መስኡድን ጠቅሰው እንደዘገቡት አላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) :-

« هَلكَ المُتنطعون» قالها ثلاثاً.

«ፅንፈኞች ለጥፋት ተዳረጉ»

በማለት ሦስት ጊዜ ደጋግመው ተናግረዋል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ይህንንና ተከታዮቹን ሁለት ምዕራፎች በአንክሮ ያስተዋለ ኢስላም ከሰዎች ልቦና ውስጥ ምን ያህል እንደተፋቀ ይረዳል:: የአላህንም የሰዎችን ቀልብ የመቀያየር ችሎታ ያስተውላል::

2. ምድር ላይ የተከሰተው የመጀመሪያ ሽርክ ከደጋግ ሰዎች ጋር በተያያዘ መልኩ እንደሆነ ተወስቷል::

3. ነቢያት ከአላህ የተላኩ መሆናቸው እየታወቀ ያስተማሩት ዲን የተቀየረበት የመጀመሪያ ምክንያት::

4. ቢድአ ከሰው ልጆች ጋር የሚጋጭና ሸሪዓዊ መሠረትም የሌለው ከመሆኑ ጋር ሰፊ ተቀባይነትን ማግኘቱ::

5. የዚህ ሁሉ ምክንያት እውነትን ከሀሰት መለየት አለመቻሉ ነው:: መጀመሪያ ደጋግ ሰዎችን ከልክ በላይ ማፍቀር ተከሰተ:: በመቀጠልም አዋቂ የሚባሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ይበጃል በሚል በጎ ስሜትና በንፁህ ንያ ተነሳስተው የከወኑት ተግባር፥ ቀጣዩ ትውልድ የነርሱን በጎ አላማ ባለመረዳት ጥንስሳቸውን ለጥፋት አዋለው::

6. የአንቀፅ «ኑህ፥ 23» ትርጉም::

7. የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ:: ሀቅን ላለመቀበል ያንገራግራል:: ባጢልን ግን በሙሉ ልብ ያስተናግዳል::

8. «ቢድአ ለኩፍር ይዳርጋል» የሚለው የሰለፎች አባባል ጠንካራ መሠረት አለው::

9. ሽይጧን የቢድአን የመጨረሻ ውጤት በጥልቅ ይረዳል:: ቢድአ የቱን ያህል በንፁህ ስሜትና መልካም «ንያ» ቢወጠንም መጨረሻው አስከፊ ነው::

10. ፅንፈኝነትን የሚያወግዝ አጠቃላይ መርህ ተሰጥቷል:: ፅንፈኝነት የሚያስከትለውን አስከፊ ውጤት መረዳት ያሻል::

11. ለፅድቅ ክንውን እንኳ ቢሆን ቀብር ላይ ለረዥም ጊዜ መቆየት ጥፋት ሊያስከትል ይችላል::

12. ሀውልት ማነፅ የተከለከለ ነው:: እንዲወገድ የመደረጉ ጥበብ ግልፅ ነው::

13. የተጠቀሰውን ታሪክ ማወቅና ዘወትር ማስታወስ ጠቃሚ ነው::

14. እጅግ የሚገርመውና የሚደንቀው ሰዎች ይህን ታሪክ ከቁርአን ተፍሲርና ከሐዲስ ኪታቦች ላይ ዘወትር እያነበቡና ትርጉሙንም በሚገባ እየተረዱ የኑህን ሕዝቦች የጥፋት ተግባር እንደ ፅድቅ የዒባዳ ክንውን መቁጠራቸው ነው:: አላህና መልዕክተኛው የከለከሉት ግልፅ ኩፍርን ብቻ ነው ብለው ማሰባቸው ደግሞ ከዚህ በላይ ያስገርማል:: አላህ ልቦናቸውን ከእውነት ጋርዶታል::

15. እነርሱ የከጀሉት ሽፈአን እንጅ ሌላን እንዳልሆነ ግልፅ ነው::

16. የመጀመሪያ ሀውልቶችን የተከሉ ክፍሎች ያን ሲያደርጉ ምንም ዓይነት አላማ አልነበራቸውም ብለው ማሰባቸው::

17. «ክርስቲያኖች የማርያምን ልጅ ክብር አለቅጥ እንዳጎኑት እናንተም የኔን ክብር ከተገቢው በላይ አታዝልቁት» በማለት መልዕክተኛው የሰጡት ትምህርት እጅግ ከፍተኛ ቁም ነገርን አዝሏል:: የአላህ ሶላትና ሰላም ይስፈንባቸው:: መልዕክታቸውን በሚገባ አድርሰዋል::

18. ፅንፈኞች ለጥፋት እንደሚዳረጉ በመግለፅ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጥሩ ምክር ለግሰውናል::

19. የኑህ ህዝቦች ሀውልቶችን ማምለክ የጀመሩት እውቀት ሲጠፋ፥ መሐይምነት ሲስፋፋ ነበር:: ይህ የዕውቀትን ጠቀሜታና የመሐይምነትን አስከፊነት በጉልህ ያሳያል::

20. «ኢልም» እንዲከስም ምክንያቱ የዑለሞች ማለቅ ነው::

# ምዕራፍ ሃያ

## የአንድን ደግ ሰው መቃብር ማምለክ ይቅርና ከዚያ ሰው ቀብር ላይ አላህን ማምለክ እንኳ በጥብቅ ተወግዟል

በሰሂሐል ቡኻሪ እንደተዘገበው አዒሻ (ረዐ) ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«أنَّ أمَّ سَلَمَةَ ذَكَرَتْ لِرَسُولِ الله ﷺ كَنِيسَةً رأَتهَا بأرْضِ الحَبَشَةِ ومَا فِيهَا مِنَ الصُّوَرِ. فَقالَ أولئِكَ إذَا مَاتَ فِيهِمُ الرَّجُلُ الصَّالِحُ أو العَبْدُ الصَّالِحُ بَنَوْا عَلى قَبْرِهِ مَسْجِداً وصَوَّرُوا فيْهِ تِلْكَ الصُّوَرَ أولئِكَ شِرَارُ الخَلْقِ عِنْدَ الله. فهؤلاءِ جَمَعُوا بَيْنَ فِتْنَتَيْنِ فِتنَةَ القُبُورِ وفِتْنَةَ التَّماثِيلِ»

ኡሙሰለማህ ሀበሻ መሬት ላይ ስላየችው አንድ ቤተክርስቲያን፣ በውስጡ ስላሉ ሀውልቶችና ስዕላ ስዕሎች ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) አጫወተቻቸው:: «እነርሱ ከአላህ ዘንድ በጣም የተጠሉ ህዝቦች ናቸው:: አንድ ደግ ሰው ወይም መልካም የአላህ ባሪያ በሚሞትበት ወቅት ከመቃብሩ ላይ መስጊድ ይገነባሉ፥ ከውስጡም ሀውልቶችን ያቆማሉ፤ ስዕላስዕሎችን ይስላሉ:: እነኚህ ሰዎች በመካነ መቃብሩ ውስጥ ሁለት አይነት የከበዱ ጥፋቶችን ፈፅመዋል፤ቀብር ላይ ማምለክና ስዕላስዕሎችን መሳል::»

ቡኻሪና ሙስሊም አዒሻን ጠቅሰው እንደዘገቡት:-

«لمَّا نُزِلَ برَسُولِ الله ﷺ طَفِقَ يَطْرَحُ خَميصَةً لَهُ عَلى وَجْهه فَإذَا اغتَمَّ بِهَا كَشَفَهَا فقَالَ وهُوَ كذلِكَ لَعَنَةُ الله عَلى اليَهُودِ والنَّصارَى اتَّخَذُوا قُبُورَ أنْبِيائِهِمْ مَسَاجِدَ يُحَذِّرُ مَا صَنَعُوا ولوْلا ذلِكَ أُبْرِزَ قَبْرُهُ غَيْرَ أنَّهُ خَشِيَ أنْ يُتَّخَذَ مَسْجِداً».

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ጣእረ ሞት ላይ በነበሩበት ወቅት ፊታቸውን በጥቁር ጨርቅ ሸፈኑ፤ መተንፈስ እስኪሳናቸው ድረስ:: ከዚያም ጨርቁን ከፊታቸው ላይ በማስወገድ :-

«የሁዳዎችና ክርስቲያኖች የአላህ መርገምት ይውረድባቸው። የነቢያቶቻቸውን መቃብሮች መስጊድ አድርገው ያዙ። የነሱን ፈለግ አትከተሉ» በማለት ተናገሩ። ይህ እቀባ ባይኖር ኖሮ ቀብራቸው ከሌሎች ለየት እንዲል ባማረ ሁኔታ ይታነፅ ነበር። ግና ሰዎች ቤተአምልኮ እንዳያደርጉት ሰጉ።

ጁንደብ ኢብን አብደላህ ተከታዩን ሐዲስ ማስተላለፋቸውን ሙስሊም ዘግበዋል:-

«سَمِعتُ النَّبيَّ ﷺ قَبْلَ أَنْ يَمُوتَ بِخَمْسٍ وهُوَ يَقُولُ إِنِّي أَبرَأُ إِلَى اللهِ أَنْ يَكُونَ لِي مِنْكُمْ خَليلٌ، فَإِنَّ اللهَ قَدِ اتَّخَذَنِي خَليلاً ولَوْ كُنْتُ مُتَّخِذاً مِنْ أُمَّتِي خَليلاً لاتَّخَذْتُ أَبَا بَكْرٍ خَليلاً. أَلا وإِنَّ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ كَانُوا يَتَّخِذُونَ مِنْ قُبُورِ أَنْبِيائِهِمْ مَسَاجِدَ أَلا فَلاَ تَتَّخِذُوا القُبُورَ مَسَاجِدَ فَإِنِّي أَنْهَاكُمْ عَنْ ذلِكَ».

ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ከመሞታቸው አምስት ቀናት ቀደም ብለው ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ:- «ከመካከላችሁ አንድንም ሰው ኸሊል (የልብ ወዳጅ) እንዳማልይዝ በአላህ ስም አውጃለሁ። አላህ ኢብራሂምን ኸሊሉ እንዳደረጋቸው እኔንም አድርጎኛል። ከተከታዮቼ መካከል ኸሊል መያዝ የምችል ቢሆን ኖሮ አቡበክርን ነበር ኸሊል የማደርገው። አዋጅ! ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦች የነቢያቶቻቸውን መካነ መቃብሮች መስጊድ አድርገው ይይዙ ነበር። የቀብር ቦታዎችን መስጊድ አድርጋችሁ አትያዙ። በጥብቅ ከልክያችኋለሁ።»

በህይወታቸው የመጨረሻ ሰዓትም ይህንኑ እቀባ አስተላልፈዋል። ድርጊቱን የሚፅሙትን ተራግመዋል። ከቀብር ቦታዎች ላይ መስገድም - ግንብ ባይገነባም- ከዚሁ እቀባ ውስጥ ይካተትል። «መስጊድ እንዳይደረግ ሰጉ» የሚለው አገላለፅ ይህንኑ ያመለክታል። ሶሃቦች (ረዐ) ከነብዩ ቀብር ዙሪያ ግንብ ለመገንባት ፈቃደኛ አልሆኑም። ማንኛውም ለሰላት ብቻ የታቀደ ሥፍራ እንደ መስጊድ ይቆጠራል። ከዚህም አልፎ ማንኛውም ሶላት የሚሰገድበት ቦታ ሁሉ- የአላህ መልዕክተኛ እንደተናገሩት- መስጊድ ሊባል ይችላል:-

«جُعِلَتْ لِيَ الأَرْضُ مَسْجِداً وَطَهُوراً».

«ምድር መስጊድና ጦሑር ተደርጋልኛለች።»

አህመድ ኢብን መስኡድን (ረዐ) ጠቅሰው መርፋዕ በሆነ ሰነድ እንደዘገቡት:-

«إِنَّ مِنْ شِرَارِ النَّاسِ مَنْ تُدْرِكُهُمُ السَّاعَةُ وهُمْ أَحْيَاءٌ والذِينَ يَتَّخِذُونَ القُبُورَ مَسَاجِدَ».

«ከሰዎች ሁሉ ከአላህ ዘንድ እጅግ የተጠሉት በህይወት እያሉ ቂያማ የሚደርስባቸውና የቀብር ቦታዎችን መስጊድ አድርገው የሚይዙ ናቸው::»

በማለት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) መናገራቸው ተወስቷል:: (አቡ ሃቲም ሶሂህ በሆነ ጥራዛቸው ውስጥ አስፍረውታል)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከመካነ መቃብር ላይ በንፁህ «ንያ» ተነሳስቶም ቢሆን አላህ የሚመለክበትን መስጊድ ስለገነባ ሰው የተናገሩት እውነታ::

2. ስዕላስዕሎች በጥብቅ የተወገዙ መሆናቸው::

3. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ይህን ነጥብ ከፍተኛ ትኩረት ችረውታል:: በመጀመሪያ በማያሻማ ሁኔታ አብራሩላቸው:: ከመሞታቸው አምስት ቀናት ቀደም ብሎም አወሱት:: ከሞት አፋፍ ላይ እያሉም አልዘነጉትም:: ቀብራቸው ላይ መስጊድ እንዳይገነባ በጥብቅ አስጠንቅቀዋል::

4. ከመሞታቸው በፊት መቃብራቸው ላይ ይህ የጥፋት ድርጊት እንዳይፈፀም መከልከላቸው::

5. ይህ ድርጊት የሁዳዎችና ክርስቲያኖች በነቢያቶቻቸው መቃብሮች ላይ የሚፈፅሙት ነው::

6. በዚህ አድራጎታቸው ነቢያዊ መርገምት ወርዶባቸዋል::

7. የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ፍላጐት በርሳቸው ቀብር ላይም ይህንን ድርጊት እንዳንፈፅም እኛን ማስጠንቀቅ ነበር::

8. የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ቀብር ከሌሎች ጎልቶ እንዲታይ ያለመደረጉ ጥበብ::

9. መካነ መቃብርን መስጊድ አድርጎ የመያዝ ትርጉም::

10. ይህን ድርጊት የሚፈፅሙ ወገኖችን በህይወት እያሉ ቂያማ ከሚደርስባቸው ሰዎች አጣምረው አወሱ:: ለሽርክ የሚያበቁ ሰበቦችን ከመጨረሻ ውጤታቸው ጋር ገለፁ::

11. ከመሞታቸው አምስት ቀናት ቀደም ብለው ባስደመጡት ንግግር ይህንኑ አውስተዋል:: ከቢድአ ሰዎች ሁሉ ይበልጥ አስከፊ የሆኑትን ሁለት አንጃዎች ከንቱነት ይህ ዘገባ

ያጋልጣል፤የራፊዷንና የጀህምዮችን አተያይ ብክለት። አንዳንድ ኡለሞች እነኝህ አንጃዎች ከ72ቱ የዚህ ኡማ ክፍሎች ውጭ ያደርጓቸዋል። በራፊዷ ጀማሪነት ነው ሽርክና የቀብር አምልኮ በሙስሊሞች ህይወት ውስጥ የሰረፀው። እነሱ ናቸው ቀብር ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ግንብ ያነፁት።

12. በመልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የደረሰው የጣዕረ ሞት ሁኔታ።

13. መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) የታላላቅ ሰብዕናዎችን ባልደረባነት የማግኘት እድል ገጥሟቸዋል።

14. ይህ ባልደረባነት ከፍቅር የላቀ ደረጃ ነው።

15. አቡበክር አልሲዲቅ ከሶሃቦች ሁሉ የላቀ ደረጃ ያላቸው እንደሆኑ ተመልክቷል።

16. ይህም የረሱል (ሰ.ዐ.ወ) ኸሊፋ የመሆን ብቃታቸውን አመልካች ነው።

## ምዕራፍ ሃያ አንድ
## በደጋግ ሰዎች ያለን ፅንፈኛ አመለካከት መቃብሮቻቸውን ወደ ሚመለኩ ጣኦታት ይለውጣቸዋል

ማሊክ «ሙወጦእ» ላይ እንዳሰፈሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«اللهُمَّ لاَ تَجْعَلْ قَبْرِي وَثَناً يُعْبَدُ اشْتَدَّ غَضَبُ الله على قَوْمٍ اتَّخَذُوا قُبُورَ أَنْبِيائِهِمْ مَسَاجِدَ».

«አላህ ሆይ! መቃብሬን የሚመለክ ጣኦት አታድርግብኝ፤ የነብያቶቻቸውን መቃብሮች ጣኦት አድርገው በያዙ ህዝቦች ላይ የአላህ ቁጣ በረታ::» ሲሉ ተናግረዋል::

ኢብን ጀሪር ሱፍያንን ጠቅሰው እንደዘገቡት ሙጃሂድ:-

﴿أَفَرَءَيْتُمُ ٱللَّٰتَ وَٱلْعُزَّىٰ﴾

«አል ላትንና አል ዑዛን አያችሁን?»
የሚለውን ቁርአናዊ ቃል ሲያብራሩ:-

«كَانَ يَلُتُّ لَهُمُ السَّوِيقَ فَمَاتَ فَعَكَفُوا عَلى قَبْرِهِ».

«እርሱ (የተጠቀሱት ጣኦታት በስማቸው ከተሰየሙባቸው ሰዎች አንዱ) ሐጅ ለሚያደርጉ ሰዎች ምግብ ያዘጋጅ ነበር:: ሞተ:: ሰዎች መቃብሩ ላይ ለረዥም ጊዜ ተቀመጡ::»

ኢብን ዓባስም:- «ለሐጃጆች ምግብ ያዘጋጅ ነበር» ማለታቸውን አቡል ጀውዛእ አስተላልፈዋል:: ኢብን ዓባስ እንዲህ ብለዋል:-

«لَعَنَ رَسُولُ الله ﷺ زَائِرَاتِ القُبُورِ والمُتَّخِذِينَ عَلَيهَا المَسَاجِدَ والسُّرُجَ».

«የአላህ መልዕክተኛ ﷺ መቃብር የሚጎበኙ እንስቶችን፣ መቃብርን መስጊድ አድርገው የሚይዙትንና መቃብር ላይ መብራት የሚያበሩትን ተራግመዋል::» (አስሐበ ሱነን)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. የጣኦት ትርጉም::

2. የአምልኮ (ዒባዳ) ትርጉም፡፡

3. የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ይከሰታል ብለው ከሚፈሩት ነገር ብቻ ነው የአላህን ጥበቃ ይጠይቁ የነበሩት፡፡

4. የነቢያትን መቃብሮች መስጊድ አድርጎ መያዝን ከዚሁ መፈረጃቸው፡፡

5. አላህ ይህ ድርጊት በጣሙን እንደሚያስቆጣው ተወስቷል፡፡

6. ትልቋ ጣኦት «ላት» የምትመለከበት የዒዳ አይነትና ባህሪ፡፡

7. የደግ ሰው ቀብር እንደነበረች ተገልጿል፡፡

8. የጣኦቷ ስያሜ ከዚያ መቃብር ከተቀበረው ሰው ስም የተወሰደ ነው፡፡

10. ቀብር ላይ መብራት የሚያበሩ ሰዎች መረገማቸው፡፡

# ምዕራፍ ሃያ ሁለት

## ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተውሒድን ከብክለት ተከላክለዋል፤ ለሽርክ የሚያበቁ መንገዶችን ሁሉ ዘግተዋል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿لَقَدْ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مِّنْ أَنفُسِكُمْ عَزِيزٌ عَلَيْهِ مَا عَنِتُّمْ حَرِيصٌ عَلَيْكُم بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ۝ فَإِن تَوَلَّوْا فَقُلْ حَسْبِىَ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَهُوَ رَبُّ ٱلْعَرْشِ ٱلْعَظِيمِ﴾

*«ከጎሳችሁ የሆነ፣ ችግራችሁ በርሱ ላይ ፅኑ የሆነ፣ በናንተ እምነት ላይ የሚጓጓ፣ ለምእመናን ሩኅሩህና አዛኝ የሆነ መልዕክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ:: ቢያፈገፍጉም አላህ በቂዬ ነው፤ ከርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ በርሱ ተመካሁ፤ እርሱም የታላቁ ዓርሽ ጌታ ነው፣ በል» (አል-ተውባህ: 128-130)*

አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«لا تَجْعَلُوا بُيُوتَكُمْ قُبُوراً ولا تَجْعَلوا قَبْرِي عِيداً وصَلُّوا عَلَيَّ فَإِنَّ صَلاتَكُمْ تَبْلُغُنِي حَيْثُ كُنتُمْ».

«ቤቶቻችሁን መካነ መቃብር አታድርጓቸው፤ መቃብሬንም የባዕል (ዒድ) ማዕከል አታድርጉት፤ በኔ ላይ ሰለዋት አውርዱ፤ ይደርሰኛል::»

አቡዳወድ ሐሰን በሆነ ሰነድ ሐሰን ኢብን አሊን ዋቢ አድርገው እንደዘገቡት :-

«أنَّه رَأى رَجُلاً يَجيءُ إلى فُرْجَةٍ كَانَتْ عِنْدَ قَبْرِ النَّبيِّ ﷺ فَيَدْخُلُ فِيهَا فَيَدْعُو. فَنَهاهُ وقَالَ ألاَ أُحَدِّثُكُم حَديثاً سَمِعْتُه مِنْ أبي عَن جَدِّي عَن رَسُولِ الله ﷺ قَالَ: لا تَتَّخِذُوا قَبْري عِيداً ولا بُيُوتَكُمْ قُبُوراً وصَلُّوا عَلَيَّ فَإنَّ تَسْليمَكُمْ يَبْلُغُني أينَ كُنْتُمْ».

ከነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) መቃብር ዘንድ በነበረች አንዲት ክፍተት በኩል ሾልኮ የሚገባና ዱአ የሚያደርግ አንድ ሰው ተመለከቱ:: ከለከሉት:: እንዲህም አሉትም :- «አባቴ አያቴን ዋቢ አድርገው ሲያስተላልፉ ያደመጥኩትን ተከታዩን የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ቃል አልነገርኳችሁምን? «መቃብሬን የበዓል ቦታ አታድርጉት::

ቤታችሁንም መቃብር አድርጋችሁ አትያዙ:: ሰላምታችሁም የትም ሆናችሁ ብትልኩልኝ ይደርሰኛል::» ብለዋል::» (ሙኽታር ከተሰኘው ጥራዛቸው ውስጥ አስፍረውታል::)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ተውባህ 128-129» ትርጉም::

2. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዮቻቸውን ከተጠቀሰው አደጋ ማራቃቸው::

3. ለተከታዮቻቸው እምነት ያላቸው ጉጉት፤ ምን ያህል እንደሚያዝኑላቸውና እንደሚራሩላቸው::

4. መቃብራቸውን መጎብኘት ፅድቅ ክንውን ከመሆኑ ጋር በተለየ መልኩ እንዲጎበኝ ግን አልፈቀዱም::

5. መቃብራቸውን በብዛት መጎብኘትን ከልክለዋል::

6. ሱንና ሶላቶች ከቤት ውስጥ እንዲሰገዱ ግፊት አድርገዋል::

7. ከመካነ መቃብር ላይ ሶላት እንደማይሰገድ በዘመነ ሶሃባ በግልፅ ይታወቅ ነበር::

8. የትም ቦታ ሆኖ ለነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የሚደረግ ዱዓና የሚላክ ሰላምታ እንደሚደርሳቸው ተገልጿል::

9. የሚደረግላቸው ዱዓና ሰላምታ በመቃብር ዓለም ውስጥ ሆነውም ይደርሳቸዋል::

# ምዕራፍ ሃያ ሦስት

# ከዚህ «ኡምማ» ከፊሉ ጣዖት እስከማምለክ ይዘቀጣል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ نَصِيبًا مِّنَ ٱلْكِتَـٰبِ يُؤْمِنُونَ بِٱلْجِبْتِ وَٱلطَّـٰغُوتِ وَيَقُولُونَ لِلَّذِينَ كَفَرُوا۟ هَـٰٓؤُلَآءِ أَهْدَىٰ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ سَبِيلًا ﴾

*«ወደነዚያ ከመፅሐፉ እድልን ወደ ተሰጡት አላየህምን? በድግመትና በጣኦት ያምናሉ:: ለነዚያ ለካዱት እናንተ በመንገድ (በሃይማኖት) ከነዚያ ከተመሩት ይበልጥ የቀናችሁ ናችሁ ይላሉ::» (አል-ኒሳእ: 51)*

﴿ قُلْ هَلْ أُنَبِّئُكُم بِشَرٍّ مِّن ذَٰلِكَ مَثُوبَةً عِندَ ٱللَّهِ ۚ مَن لَّعَنَهُ ٱللَّهُ وَغَضِبَ عَلَيْهِ وَجَعَلَ مِنْهُمُ ٱلْقِرَدَةَ وَٱلْخَنَازِيرَ وَعَبَدَ ٱلطَّـٰغُوتَ ۚ ﴾

*«አላህ ዘንድ ቅጣቱ ከዚህ የከፋ ነገር ልንገራችሁን በላቸው፤ እርሱም አላህ የረገመው ሰው፣ በርሱም ላይ የተቆጣበት፣ ከነርሱም ዝንጀሮዎችንና ከርከሮዎችን ያደረገው፣ ጣኦትንም የተገዛው ሰው፣ ሃይማኖት ነው::» (አል-ማኢዳህ: 60)*

﴿ قَالَ ٱلَّذِينَ غَلَبُوا۟ عَلَىٰٓ أَمْرِهِمْ لَنَتَّخِذَنَّ عَلَيْهِم مَّسْجِدًا ﴾

*«እነዚያ በነገራቸው ላይ ያሸነፉ (ምእመናን) በነርሱ ላይ መስጊድን እንሰራለን አሉ::»(አል-ከህፍ:21)*

*አቡ ሰዒድ አል ኹድሪ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) :-*

«لَتَتَّبِعُنَّ سُنَنَ مَنْ كَانَ قَبْلَكُمْ حَذْوَ القُذَّةِ بالقُذَّةِ حتَّى لَوْ دَخَلُوا جُحْرَ ضَبٍّ لَدَخَلْتُموهُ. قَالُوا: يَا رَسُولَ اللهِ! اليَهُودُ والنَّصارى؟ قَالَ: فَمَنْ؟»

«ከናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ፈለግ እርምጃ በርምጃ ትከተላላችሁ:: ኣከድብ ጉድጓድ ውስጥ ቢገቡ እንኳ ትገባላችሁ፥ በማለት ተናገሩ»:: «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! የሁዳዎችንና

ክርስቲያኖችን ነው የምንከተለው?» ጠየቋቸው- (ሶሃቦች):: «ታዲያ ሌላ ማንን ሊሆን ይችላል?» ሲሉ መለሱ:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

ሙስሊም አቡ ሁረይራን (ረዐ) ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«أنّ الله زَوى لِيَ الأرْضَ فَرَأَيْتُ مَشَارِقَهَا ومَغَارِبَهَا وإنَّ أُمَّتِي سَيَبْلُغُ مُلْكُهَا مَا زُوِيَ لي مِنها: وأُعْطِيتُ الكَنْزَينِ: الأحْمَرَ والأبْيَضَ وإنِّي سَأَلْتُ رَبِّي لأُمَّتِي أنْ لا يُهلِكَهَا بِسَنَةٍ بِعَامَّةٍ وأنْ لا يُسَلِّطَ عَلَيْهِمْ عَدُوًّا مِنْ سِوى أنْفُسِهِم فَيَستَبيحُ بَيْضَتَهُم وإنَّ رَبِّي قَالَ: يَا مُحَمَّد! إذَا قَضَيْتُ قَضَاءً فإنَّهُ لا يُرَدُّ وإنِّي أعْطَيتُكَ لأُمَّتِكَ أنْ لا أهْلِكَهُمْ بِسَنَةٍ عامَّةٍ. وأنْ لا أُسَلِّطَ عَليهِمْ عَدُوًّا مِنْ سِوى أنْفُسِهِمْ فَيَستَبيحُ بَيْضَتَهُم ولَو اجْتَمَعَ عَليهِمْ بِأقْطَارِهَا. حتَّى يَكُونَ بعْضُهُم يُهْلِكُ بَعْضاً ويُسبِي بَعْضُهُم بَعضاً».

«አላህ ምድርን አቀረበልኝ:: ምስራቁንም፣ ምዕራቡንም ተመለከትኩ:: ወደ ፊት ተከታዮቼ የተመለከትኩትን ሁሉ ይቆጣጠራሉ:: ሁለት ድልቦች ተሰጡኝ፤ ቀይና ነጭ፤ የሮማ እና የፐርሺያን ኢምፓየሮች:: ተከታዮቼን በድርቅ እንዳያጠፋ፣ በበላይነት የሚቆጣጠራቸውና አመራሩን የሚነጥቃቸው ከራሳቸው ውጭ የሆነ ጠላት እንዳያጠቃቸው ፈጣሪዬን ተማፀንኩ::

«ሙሐመድ ሆይ! የእኔ ውሳኔ አንድ ጊዜ ከተላለፈ አይታጠፍም:: ተከታዮችህን በድርቅ ላላጠፋና ከነርሱ ውጭ የሆነ ጠላት እንዲያጠቃቸው ፈቃዴ ላይሆን ቃል እገባልሃለሁ:: የዓለም ህዝብ ሊያጠፋቸው ቢረባረብ እንኳ ሊያሸንፋቸው እንደማይችል ወስኛለሁ:: ግና ተከታዮችህ ከፊሉ ከፊሉን ያጠቃል:: በበላይነትም ይገዛል» ተባልኩ:: (አል በርቃኒ ዘግበውታል)

እንዲህ ሲሉም አክለዋል:-

«وإنَّمَا أخَافُ عَلى أُمَّتِي الأئمَّةَ المُضِلِّينَ وإذَا وَقَعَ عَليهِمُ السَّيفُ لَمْ يُرْفَعُ إلى يَوم القيامَةِ ولا تَقُومَ السَّاعَةُ حتَّى يَلحَقَ حيٌّ مِنْ أُمَّتي بالمُشْرِكينَ. وحتَّى تَعبُدُ فِئَامٌ مِنْ أُمَّتي الأوْثَانَ. وإنَّه سيَكُون في أُمَّتي كَذَّابونَ ثَلاثُونَ كُلُّهُم يَزْعَمُ أنَّهُ نَبيٌّ وأنَا

خَاتَمُ النَّبِيِّينَ لا نَبِيَّ بَعْدِي، ولا تَزَالُ طَائِفَةٌ مِنْ أُمَّتِي عَلى الحَقِّ مَنْصُورةٌ لا يَضُرُّهُمْ مَنْ خَذَلَهُم حتَّى يَأْتِي أمْرُ الله تَبَارَكَ وتَعالَى».

«ለተከታዮቼ እጅግ የምፈራላቸው ወደ ተሳሳተ ጎዳና የሚመሩ መሪዎችን ነው:: ደም መፋሰስ ላይ ከወደቁ፣ እስከ ዕለተ ቂያማ ደም መፋሰሳቸው አይቆምም:: ከተከታዮቼ ከፊሎች የሙሽሪኮችን ፈለግ ሳይከተሉና ጣኦት ሳያመልኩ ቂያማ አይከሰትም:: ሰላሳ ሐሳዊ ነብያትም ከመካከላቸው ይነሳሉ:: እኔ የነብያት መቋጫ ነኝ:: ከኔ በኋላ ነብይ የለም:: ግና ከተከታዮቼ የተወሰነ ክፍል በሐቅ ላይ እንደሆነ በድል አድራጊነት እስከመጨረሻው ይዘልቃል:: የሌሎች ከጎኑ አለመሰለፍ ቅንጣት አይጎዳውም:: ልዑልና ሐያል የሆነው አላህ (ለታሪክ ሂደት) ውሳኔውን እስኪያስተላልፍ ድረስ::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ኒሳእ 51» ትርጉም::
2. የአንቀፅ «አል ማኢዳህ 60» ትርጉም::
3. የአንቀፅ «አል ካህፍ 21» ትርጉም::
4. በድግምትና በጣኦት ማመን ትርጉሙ ተገልጿል:: እጅግ ጠቃሚ ነጥብ ነው:: በልቦና ማመን ነው ወይስ ሐጢአት መሆኑን ከልብ ከመቀበል ጋር በወንጀሉ የተዘፈቁ ግለሰቦችን ድርጊት አለመቃወም?
5. ክህደታቸው በግልፅ የሚታወቅ ካፊሮች ከሙእሚኖች በተሻለ ፍኖት ላይ ናቸው መባሉ::
6. የዚህን ኡምማ እጣ ፈንታ አስመልክቶ አቡ ሰዒድ ባስተላለፉት ዘገባ የተወሳው እውነታ የሚከሰትበት አጋጣሚ እውን እንደሚሆን::
7. በዚሁ ኡምማ ውስጥ ጣኦት አምልኮ እንደሚከሰት መልዕክተኛው (ሰ.ዐ.ወ) ግልፅ አድርገዋል::
8. እንደ ሙኽታር ዓይነት ነብይ ነን የሚሉ ግለሰቦች ከዚህ ኡምማ መሐል እንደሚነሱ ተወስቷል:: እጅግ የሚያስደንቅ ነው:: ሙኽታር ቃለ-ተውሂድን ይናገራል:: የዚህ ኡምማ አካል መሆኑንም ከመግለፅ በዝና አያውቅም:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እውነተኛ የአላህ መልዕክተኛ፣ ቁርአንም የአላህ ቃል መሆናቸውን ይቀበላል:: ሙሐመድ የነቢያት መቋጫ መሆናቸው በማያሻማ

ሁኔታ ቁርአን ላይ ሰፍሯል:: ይህ ሁሉ እንደረፋድ ፀሐይ ቁልጭ ያለ እውነታ እያለ የሙኽታርን የ «ነብይ ነኝና ተከተሉኝ» ጥሪ ሰዎች አምነው ተቀበሉ:: በሶሃቦች የመጨረሻ ዘመን ነበር ሙኽታር የተነሳው::በርካታ ሰዎች ተከትለውታል::

9. ሐቅ እንደበፊቱ ሙሉ በሙሉ እንደማይወገድና ከሐቅ ጋር የወገነ አካል ከኡምማው ውስጥ ምንጊዜም እንደማይጠፉ ከተጠቀሰው የሀዲስ ዘገባ ውስጥ ብስራት ተነግሯል::

10. እነኝህ የሐቅ ጠበቆች ቁጥራቸው ጥቂት ቢሆንም ከጎናቸው ያልተሰለፈ ወይም እነርሱን ተቃርኖ የተንቀሳቀሰ ሁሉ ቅንጣት አይጎዳቸውም:: ይህ ታላቅ ተአምር ነው::

11. ይህ ሁኔታ እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ይቀጥላል::

12. ከዘገባው ውስጥ የተጠቀሱ ታላላቅ ተአምራት :-

- ምድርን ምስራቁንም፣ ምዕራቡንም እንዳቀረበላቸውና ትርጉሙንም ተናግረዋል:: ያሉት እውን መሆኑን አረጋግጠናል:: ይህ ኡምማ ከሰሜንና ደቡብ ይልቅ በጣም የተስፋፋ በምስራቅና ምዕራብ ነው::
- ሁለት ታላላቅ ድልቦች እንደተሰጧቸው ተናግረዋል::
- ለኡመታቸው ሁለት ነገሮችን አላህን ተማፅነው ጥያቄያቸው ተቀባይነትን አግኝቷል::
- ሦስተኛውን ግን መከልከላቸውን ገልፀዋል::
- የደም መፋሰስ እንደሚከሰትና እስከ ዕለተ ቂያማ እንደማይበርድ አውስተዋል::
- ነብይ ነን የሚሉ ግለሰቦችና ኡማውን በክህደት ጎዳና የሚመሩ መሪዎች ከኡምማው ውስጥ እንደሚወጡም ተናግረዋል::

እነኝህ ሁሉ ትንቢቶች በጊዜው የማይታመኑ ቢመስሉም ተፈጻሚነትን አግኝተዋል::

13. በዚህ ኡምማ ላይ በተለየ ሁኔታ እጅግ የፈሩት ስህተት ውስጥ ያሉ መሪዎችን ነበር::

14. የጣኦት አምልኮ ትርጉም አፅንኦት ተሰጥቶታል::

# ምዕራፍ ሃያ ሰራት
## ድግምት

አላህ እንዲህ ብሏል :-

﴿وَلَقَدْ عَلِمُوا۟ لَمَنِ ٱشْتَرَىٰهُ مَا لَهُۥ فِى ٱلْـَٔاخِرَةِ مِنْ خَلَـٰقٍ﴾

*«የገዛውም ሰው ለርሱ በመጨረሻይቱ ሀገር ምንም ዕድል የሌለው መሆኑን በእርግጥ አወቁ፤» (አል-በቀራህ:102)*

﴿يُؤْمِنُونَ بِٱلْجِبْتِ وَٱلطَّـٰغُوتِ﴾

*«በድግምትና በጣኦት ያምናሉ::» (አል ኒሳእ: 51)*

ዑመር (ረዐ) «ጁብት»ን ድግምት፣ ጣኦትን ደግሞ ሽይጧን ብለውታል:: ጃቢር ደግሞ:- «ጣኦት በየቦታው የሚገኙና ሽይጧን ወህይ የሚያወርድላቸው ጠንቋዮች ናቸው::» ብለዋል::

አቡ ሁረይራ (ረዐ) ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«اجْتَنِبُوا السَّبْعَ الموبقَاتِ. قَالُوا يَا رَسُولَ الله! ومَا هُنَّ؟ قَالَ الشِّرْكُ بِالله. والسِّحْرُ. وقَتْلُ النَّفْسِ التِي حَرَّمَ الله إلاَّ بالحَقِّ. وأَكْلُ الرِّبَا، وأَكْلُ مَالَ اليَتِيمِ، والتَّوَلِّي يَوْمَ الزَّحْفِ، وَقَذْفِ المُحْصَنَاتِ الغَافِلاَتِ المُؤْمِنَاتِ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) :- «ከሰባት አጥፊ ወንጀሎች ታቀቡ» በማለት ተናገሩ:: «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነርሱ እነማን ናቸው?» ሲሉ ሶሃቦች ጠየቋቸው:: «በአላህ ላይ ማሻረክ፣ ድግምት፣ ያለ አግባብ አላህ እርም ያደረገውን የሰዎችን ነፍስ ማጥፋት፣ አራጣ፣ የሙት ልጅን ገንዘብ መብላት፣ ከተፋፋመ ውጊያ ላይ ወደ ኋላ ማፈግፈግና የንፁህን ሙስሊም ሴቶችን ስም በዝሙት ማጉደፍ» ሲሉ መለሱ::

ጁንዳብ «መርፉዕ» በሆነ «ሰነድ» እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«حَدُّ السَّاحِرِ ضَرْبُهُ بالسَّيْفِ».

«የድግምተኛ መቀጮ አንገቱን በሾተል መቀላት ነው::» ብለዋል:: (ቲርሚዚ ዘግበውታል)

ቡኻሪ እንደዘገቡት በጅለት ኢብን ዐብደህ ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«كَتَبَ عمر بن الخطاب رضي الله عنه: أنِ اقْتُلُوا كُلَّ سَاحِرٍ وسَاحِرَةٍ قَالَ فَقَتَلْنَا ثَلَاثَ سَوَاحِرَ».

ዑመር ኢብንል ኸጧብ:- «ድግምተኛን ሁሉ ግደሉ» የሚል ትዕዛዝ አስተላለፉ:: እናም ሦስት ድግምተኞችን ገደልን::

ሐፍሷ (ረዐ) በርሷ ላይ ድግምት ያደረገችባትን ሴት እንድትገድል መታዘዟና መግደሏ ተዘግቧል:: ጁንደብም ተመሳሳይ ድርጊት መፈፀማቸው ተወስቷል:: ሌሎች ሦስት የመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ባልደረቦችም ድግምተኛን እንደገደሉ አህመድ ዘግበዋል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል በቀራህ 102» ትርጉም
2. የአንቀፅ «አል ኒሳእ 51» ትርጉም::
3. የጁብት እና የጣኡት ትርጉም፥ እንዲሁም በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት::
4. ጣኡት ከጅንም ከሰውም ሊሆን ይችላል::
5. በጥብቅ የተከለከሉ ሰባት አጥፊ ወንጀሎች ተዘክረዋል::
6. ድግምተኛ ከኢስላም ውጭ ነው::
7. ለተውበት ጊዜ አይሰጠውም፤ ወዲያውኑ ይገደላል::
8. በዑመር (ረዐ) ዘመነ ኺላፋ በሙስሊሞች መካከል ድግምተኛ ይኖር ነበር:: ከዚያ በኋላ ባሉ ዘመናት መገኘቱ ብዙም የሚያስገርም አይሆንም::

# ምዕራፍ ሃያ ስምስት
## የድግምት ዓይነቶች

ኢብን ቀቢሰህ አባታቸውን ዋቢ አድርገው እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

«إنَّ العِيَافَةَ والطَّرْقَ والطِّيَرَةَ مِنَ الجِبْتِ».

«ዒያፉ፣ ጦርቅ እና ገድ የድግምት ዓይነቶች ናቸው::»

ዓውፍ እንዳሉት «ዒያፉ» በበራሪ አዕዋፋት የሚፈፀም የድግምት ዓይነት ሲሆን:- «ጦርቅ» ከምድር ላይ በማስመር የሚፈፀም ነው:: ሐሰን ጁብትን :- «የሰይጣንን ድምፅ ማድመጥ» ሲሉ ገልፀውታል:: (አቡዳውድ፣ ነሲእይና ኢብን ሒባን)

ኢብን ዓባስ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ):-

«مَنِ اقْتَبَسَ شُعْبَةً مِنَ النُّجُوم فَقَدِ اقْتَبَسَ شُعْبَةً مِنَ السِّحْرِ زَادَ مَا زَادَ»

«ስለ ኮከብ ቆጠራ ጥቂት ያወቀ ከድግምት እውቀት ተቃምሷል:: እውቀቱ በጨመረ ቁጥር የደጋሚነት ችሎታውም ይጨምራል» ብለዋል:: (አህመድ ዘግበውታል)

ነሳኢ አቡሀረይራን በመጥቀስ ባሰፈሩት ዘገባ ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«مَنْ عَقَدَ عُقْدَةً ثُمَّ نَفَثَ فيهَا فَقَدْ سَحَرَ، ومَنْ سَحَر فَقَدْ أشْرَكَ، ومَنْ تَعَلَّقَ شَيْئاً وُكِلَ إليهِ».

«ክር ቋጥሮ ከዚያ ላይ የነፋ ድግምት ፈፅሟል:: ድግምት የፈፀመ ደግሞ በአላህ አሻርኳል:: በአንዳች ነገር የተመካ ሁሉ- ነገሩ ለዚያ ነገር ይተተዋል::» ብለዋል::

ኢብን መስዑድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) :-

ألاَ هَلْ أنَبِّئُكُم مَا العَضْهُ؟ هيَ النَّميمَةُ القَالَةُ بَيْنَ النَّاسِ».

«አድሃ ምን እንደሆነ ልንገራችሁን? ነገር ማሳበቅ ነው፤ በሰዎች መካከል አለመግባባቶችን የሚፈጥሩ ወሬዎችን ማሰራጨት::» ብለዋል:: (ሙስሊም ዘግበውታል)

ቡኻሪና ሙስሊም ኢብን ዑመርን ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.0.ወ):-

«إِنَّ مِنَ البَيَانِ لَسِحْراً».

«ማራኪ የአገላለፅ ስልት ድግምት አለው» ብለዋል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ዒያፋ፣ ጡሩቅ እና ገድ (ጢየረህ) የድግምት ዓይነቶች ናቸው::

2. የዒያፋ እና የጡሩቅ ትርጉመ ተወስቷል::

3. የኮከብ ቆጠራ ዕውቀት የድግምት ክፍል ነው::

4. ክር ቋጥሮ መተንፈስ (ዑቀድ) ድግምት ነው::

5. ነገር እያሳበቁ ሰዎችን ማጣላትም የድግምት አካል ነው::

6. ማራኪ የአገላለፅ ስልት ከድግምት ይፈረጃል::

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት
## ጠንቋዮችና መሰሎቻቸው

ሙስሊም ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ባልተቤቶች አንዷን በመጥቀስ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን መናገራቸውን ዘግበዋል:-

«مَنْ أتَى عَرَّافاً فَسَألَهُ عَنْ شَيءٍ فَصَدَّقَهُ بِمَا يَقُولُ لَمْ تُقْبَلُ لَهُ صلاةُ أربَعِينَ يَوماً».

«ጠንቋይ ዘንድ ሄዶ አንዳች ነገር የጠየቀና ጠንቋዩ የተናገረውን አምኖ የተቀበለ ሶላቱ ለአርባ ቀናት ያህል ተቀባይነት የለውም::»

አቡ ሁረይራ (ረዐ) እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«مَنْ أتَى كاهِناً فَصَدَّقَهُ بِمَا يَقُولُ فَقَدْ كَفَر بِمَا أُنْزِلَ عَلى مُحَمَّدٍ ﷺ».

«ጠንቋይ ዘንድ የሄደና ጠንቋዩ የሚለውን አምኖ የተቀበለ በሙሐመድ ላይ የወረደውን መልዕክት ክዷል» ብለዋል::

አራቱ የሐዲስ አውታሮችና ሐኪም እንደዘገቡት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«مَنْ أتَى عَرَّافاً أوْ كَاهِناً فَصَدَّقَهُ بِمَا يَقُولُ فَقَدْ كَفَر بِمَا أُنْزِلَ عَلى مُحَمَّدٍ ﷺ».

«ከጠንቋይ ወይም ድግምተኛ ዘንድ በመሄድ የሚናገሩትን አምኖ የተቀበለ በሙሐመድ ላይ በተወረደው (መልዕክት) ክዷል::» ብለዋል::

አቡ የዕላእ «መውቁፍ» በሆነ ሰነድ ኢብን መስዑድን ጠቅሰው ተመሳሳይ ዘገባ አስፍረዋል::

ኢምራን ኢብን ሁሰይን «መርፉዕ» በሆነ ሰነድ እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ በማለት ተናግረዋል:-

«لَيسَ مِنَّا مَنْ تَطَيَّرَ أوْ تُطيِّرَ لَهُ أو تكَهَّنَ أو تُكُهِّنَ لَهُ، أو سَحَرَ أو سُحِرَ لَهُ، ومَنْ أتَى كَاهِناً فَصَدَّقَهُ بِمَا يَقُولُ فَقَدْ كَفَر بِمَا أُنْزِلَ عَلى مُحَمَّدٍ ﷺ».

«በገድ የተነበየ ወይም ያስተነበየ፣ የጠነቆለ ወይም ያስጠነቆለ፣ ድግምት የፈፀመ ወይም ያስፈፀመ፣ ጠንቋይ ዘንድ በመሄድ ጠንቋዩ የሚለውን አምኖ የተቀበለ በሙሐመድ ላይ የተወረደውን (መልዕክት) ክዷል።» (በዛር «ጀይድ» በሆነ ሰነድ ዘግበውታል)

ጦበራኒም «አውሰጥ» ከተሰኘው ጥራዛቸው ውስጥ «ሐሰን» በሆነ «ሰነድ» ኢብን ዓባስን በመጥቀስ «የሄደ» ከሚለው ውጭ ተመሳሳይ ዘገባ አስፍረዋል።

በገዊይ እንደሚሉት «ዓራፍ» የጠፉ ዕቃዎችና ከብቶች የሚገኙበትን ቦታና መሰል እውነታዎችን የጠፋበት ሰው የሚሰጠውን መረጃ በመንተራስ አውቃለሁ የሚል ነው። «ካሂን» በሚል ስያሜም ይታወቃል። «ካሂን» ወደፊት ስለሚከሰቱ ሚስጥራዊ ነገሮች የሚናገር ነው። ከልብ ውስጥ የተደበቁ ነገሮችን የሚናገር ነውም ተብሏል።

አቡል ዓባስ ኢብን ተይሚየህ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«ዓራፍ ለጠንቋይ፣ ለኮከብ ቆጣሪ፣ በጠጠር ለሚጠነቁልና ለሌሎችም በዚህ መንግድ የነገሮችን እውነታ እናውቃለን ለሚሉ ወገኖች የተሰጠ ስያሜ ነው።»

ኢብን ዓባስ ስነ ከዋክብትን የሚያጠኑ ሰዎችንና ኮከብ ቆጣሪዎችን አስመልክተው ሲናገሩ:- «እንዲህ ዓይነቱን ድርጊት የሚፈፅም ሰው ከአላህ ዘንድ መልካም ዕድል ይጠብቀዋል ብዬ አላምንም» ብለዋል።

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. በቁርአን ማመን ጠንቋይ የሚናገረውን አምኖ ከመቀበል ጋር ተጣምሮ ሊገኝ ፈፅሞ አይችልም።
2. ጥንቆላ ኩፍር ነው፣ ከኢስላም መውጣት።
3. ጠንቋይ ዘንድ የሄደ።
4. በገድ የጠነቆለ።
5. ድግምት ያስደረገ።
6. ሥነ ከዋክብት (አስትሮሎጂ) የተማረ።
7. በ«ካሂን» እና በ«ዓራፍ» መካከል ያለው ልዩነት።

# ምዕራፍ ሃያ ሰባት
## ድግምትን ስለመሻር (ኑሽረህ)

ጃቢር (ረዐ) እንዳስተላለፉት:-

«أَنَّ رَسولَ الله ﷺ سُئِلَ عَنِ النُّشْرَةِ؟ فَقَالَ هِيَ مِنْ عَمَلِ الشَّيْطَانِ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ስለ «ኑሽረህ» ተጠይቀው ሲመልሱ:- «የሰይጣን ተግባር ነው» ብለዋል::

አህመድም ስለዚሁ ጉዳይ ተጠይቀው :- «ኢብን መስዑድ ይህንን ሁሉ ይጠሉ ነበር» የሚል ምላሽ ሰጥተዋል:: ቡኻሪ እንደዘገቡት ቀታዳህ ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

ኢብን ሙሰየብን:- «አንድ ሰው ድግምት ቢፈፀምበት ወይም የወሲብ ስሜቱ ቢሞት ከበሽታው ለመፈወስ ኑሽረህን መጠቀም ይችላል ወይስ ሌላ የፈውስ መንገድ ይጠቀም?» ስል ጠየቅኳቸው:: «ለበጎ ተግባር እስከዋለ ድረስ ይፈቀዳል:: መልዕክተኛው የከለከሉት ጠቃሚ የሆነውን አይደለም»አሉኝ::

ሐሰን:- «ድግምት ሊፈታ የሚችለው በደጋሚ ብቻ ነው» ብለዋል:: ኢብንል ቀይም እንደጻፉት:- «ድግምትን መሻር «ኑሹራ» ይባላል:: ሁለት የኑሹራ ዓይነቶች አሉ:-

ሀ. ድግምትን በድግምት መሻር:: ይህ የተከለከለ ነው:: የሐሰን ንግግር የሚያመለክተው ይህንን ነው:: ኑሹራ አድራጊውም፣ የሚደረግለትም ሰው ከሸይጧን ጋር የሚፈልገውን በመፈፀም መግባባት አለባቸው:: ከዚያ በኋላ የድግምት ቋጠሮውን ይፈታላቸዋል::

ለ. ሁለተኛው የ«ኑሽራ» ስልት የቁርአን አንቀፆችን በማንበብ፣ መድሐኒቶችን በመጠቀምና የተፈቀዱ ዱዓዎችን በማድረግ «ሩቃ» መጠቀም ሲሆን፥ ይህ የተፈቀደ ነው::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. «ኑሽራህ» መሻር የተከለከለ ነው::
2. የተፈቀዱና ያልተፈቀዱ የ«ኑሽራ» ዓይነቶች::

# ምዕራፍ ሃያ ስምንት
## በገድ ማመን (ተጠዩር)

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿أَلَآ إِنَّمَا طَٰٓئِرُهُمْ عِندَ ٱللَّهِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ﴾

*«ንቁ! ገደቢስነታቸው ከአላህ ዘንድ ብቻ ነው፤ግን አብዛኞዎቻቸው አያውቁም» (አል-አዕራፍ:131)*

﴿قَالُوا۟ طَٰٓئِرُكُم مَّعَكُمْ ۚ أَئِن ذُكِّرْتُم ۚ بَلْ أَنتُمْ قَوْمٌ مُّسْرِفُونَ﴾

*«ገደ ቢስነታችሁ ከናንተው ጋር ነው፤ ብትገሰፁ ትስታላችሁን? በውነቱ እናንተ ወሰን አላፊዎች ናችሁ፣ አሏቸው» (ያሲን:131)*

አቡ ሁረይራ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ):-

«لاَ عَدْوَى، ولاَ طِيرَةَ، ولاَ هَامَةَ ولاَ صَفَرَ».

«ዐድዋ፣ ጢየረህ (ገድ)፣ ሐማህም ሆነ ሰፈር የተከለከሉ ናቸው::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

ሙስሊም:-

«ولا نَوْءَ ولا غُولَ».

«ነውእም፥ ጉወልም የለም፤»

የሚል አክለዋል::

ቡኻሪና ሙስሊም አነስን ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ):-

«لاَ عَدْوى ولاَ طِيرَةَ ويُعْجِبُنِي الفَأْلُ. قَالُوا ومَا الفَأْلُ؟ قَالَ الكَلِمَةُ الطَّيِّبَةُ».

«ዐድዋም ሆነ ጢየረህ (ገድ) የተፈቀዱ አይደሉም:: ፈዕል (ተስፈኝነት) ግን ያስደስተኛል» በማለት ተናገሩ:: «ፈዕል ምንድን ነው?» የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው:: «መልካም ንግግር» ሲሉ መለሱ::

ዑቅበት ኢብን ዓሚር ተከታዩን ማስተላለፋቸውን አቡዳውድ ሶሒሕ በሆነ ሰነድ ዘግበዋል:-

«ذُكِرَتِ الطِّيرَةُ عِنْدَ رَسُولَ الله ﷺ فَقَالَ أحْسَنُهَا الفَأْلُ، ولا تَرُدُّ مُسْلِماً فَإذَا رَأى أحَدُكُمْ مَا يَكْرَهُ فَلْيَقُلْ: اللهُمَّ لا يَأتِي بالحَسَنَاتِ إلاَّ أنْتَ ولاَ يَدْفَعُ السَّيِّئَاتِ إلاَّ أنْتَ ولاَ حَوْلَ ولاَ قُوَّةَ إلاَّ بِكَ».

ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ስለ ገድ (ጢየረህ) ተነሳ:: «ከሁሉም የተሻለው ፈዕል (ተስፈኝነት) ነው:: ሙስሊምን አትመልሱ:: ከናንተ አንዳችሁ የሚጠላው ሁኔታ ሲገጥመው፥ አላህ ሆይ ! ከአንተ ውጭ መልካም ነገር እንዲከሰት የሚያደርግ፣ ክፉ ነገርንም የሚመልስ የለም:: ብልሃትም፣ ሃይልም የለም፤ በአንተ ቢሆን እንጅ ፥ ይበል» አሉ::

ኢብን መስዑድ መርፋዕ በሆነ ሰነድ እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«الطِّيَرَةُ شِرْكٌ الطِّيرَةُ شِرْكٌ ومَا مِنَّا إلاَّ . . . . . . ولكنَّ الله يُذهِبُه بالتَّوكُّل»

«በገድ ማመን ሽርክ» ነው:: ሲሉ ተደምጠዋል:: ኢብን መሰዑድም:- «ለኛ እንግዳ ነው:: ቢከሰት እንኳ አላህ በተውኩል ያስወግደዋል » ብለዋል:: (አቡ ዳውድና ቲርሚዚ)

አህመድ እንደዘገቡት በኢንብ ዑመር ከተላለፈ አንድ ዘገባ ውስጥ የሚከተለው ሰፍሯል:-

«مَنْ رَدَّتْهُ الطِّيرَةُ عَنْ حَاجَتِه فَقدْ أشْرَكَ قَالُوا فَمَا كَفَّارَةُ ذَلِك؟ قَالَ أنْ تَقُولَ: اللهُمَّ لا خَيْرَ إلاَّ خَيْرُكَ ولاَ طَيْرَ إلاَّ طَيْرُكَ ولا إلهَ غَيْرُك».

«ገድ (ጢየረህ) ከጉዳዩ እንዲመለስ ምክንያት የሆነው ሰው የሽርክ ተግባር ፈፅሟል» በማለት መልዕክተኛው ተናገሩ:: «የእንዲህ ዓይነቱ ሐጢአት መካሻ (ከፋራ) ምንድን ነው?» ሲሉ ሶሃቦች ጠየቋቸው:: «አንተ መልካም ካልከው ውጭ መልካም ነገር የለም:: አንተ ከምታስገኘው ውጭ ገድ የለም:: ከአንተ ውጭ ሌላ አምላክ የለም፥ ማለት ነው» በማለት መለሱ::

ፈድል ቢን አባስ (ረ.ዐ.) የሚከተለውን መናገራቸው ተዘግቧል::

«إنَّمَا الطِّيَرَةُ مَا امْضَاكَ أوْ رَدَّكَ».

«ጢየረህ ወደ ጉዳይህ እንድትሄድ ወይም ከጉዳይህ እንድትቀር ምክንያት የሆነህ ነው።»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. «ንቁ፤ ገደቢስነታቸው ከአላህ ዘንድ ብቻ ነው፤» የሚለውን የቁርአን አንቀፅ :- «ገደቢስነታችሁ ከናንተው ጋር ነው» ከሚለው ጋር በማቀናጀት የሚፈጠረውን ፅንሰ ሃሳብ መረዳት።

2. የ«ዓዳዋ» ክልክልነት።

3. በገድ ማመን በጥብቅ የተወገዘ መሆኑ።

4. የ«ሐመህ» ውጉዝነት።

5. የ«ሰፈረህ» ውጉዝነት።

6. ፈዕል (ተስፈኝነት) ከነኝህ አይፈረጅም። ተወዳጅም ነው።

7. የፈዕል ትርጓሜ።

8. ከላይ ከተጠቀሰው አንዱ ከአንድ ሙስሊም ልቦና ውስጥ ቢከሰት አይጎዳውም። አላህ በ«ተወኩል» ያስወግድለታል።

9. ከነኝህ አንዱ ልቦና ውስጥ በሚከሰትበት ወቅት የሚደረግ ዱዓ።

10. በገድ ማመን (ጢየረህ) ሽርክ መሆኑ በግልፅ ተመልክቷል።

11. የተወገዘው የ«ገድ» (ጢየረህ) ዓይነት።

# ምዕራፍ ሃያ ዘጠኝ
## ኮከብ ቆጠራ (አስትሮሎጅ)

ቡኻሪ እንደዘገቡት ቀታዳህ ተከታዩን ተናግረዋል:-
«አላህ ከዋክብትን የፈጠረው ለሦስት ዓላማዎች ነው:-
1. ለሰማይ ጌጥና ውበት፤
2. ለሰይጣናት መቀጥቀጫዎችና
3. ለመንገደኞች የጉዞ ምልክት::
«ከነኝህ ከሦስቱ ውጭ ለሌላ ግልጋሎት የተጠቀመባቸው ስህተት ፈፅሟል:: እጣ ፈንትውን አርክሷል:: የዕውቀት ወሰንንም አልፏል::»

የጨረቃን እንቅስቃሴ መማርን ቀታዳህ ሲጠሉ፣ ኢብን ዑየይነህ አልፈቀዱም:: አህመድና ኢስሐቅ ግን ፈቅደዋል:: አቡ ሙሳ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ):-

«ثَلاَثَةٌ لا يَدْخُلُونَ الجَنَّةَ مُدْمِنُ الخَمْرِ ومُصَدِّقٌ بالسِّحْرِ وقَاطِعُ الرَّحِمِ».

«ሦስት ሰዎች ጀነትአይገቡም፤ የመጠጥ ሱሰኛ፣ በድግምት የሚያምን እና ዝምድናን ቆራጭ» ብለዋል::(አህመድና ኢብን ሒብባን ዘግበውታል)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ከዋክብት የተፈጠሩበት ዓላማ::
2. ከተጠቀሰው ውጭ ለሌላ ግልጋሎት ማዋል እንደማይገባ::
3. የጨረቃን እንቅስቃሴ መማርን አስመልክቶ የዑለሞች የአመለካከት ልዩነት::
4. ሐሰት መሆኑን እያወቀ እንኳ ቢሆን ከድግምት አንዳች ነገር ባመነ ሰው ላይ የተሰነዘረ ዛቻ::

# ምዕራፍ ሰላሳ
## በጨረቃ እንቅስቃሴ ዝናብን ስለመሻት (ስንዋእ)

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَتَجْعَلُونَ رِزْقَكُمْ أَنَّكُمْ تُكَذِّبُونَ﴾

*«ሲሳያችሁንም (ዝናብን) እናንተ የምታስተባብሉ ታደርጋላችሁን?» (አል-ዋቂዐህ :82)*

አቡ ማሊክ አል-አሽዐሪይ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«أَرْبَعٌ فِي أُمَّتِي مِنْ أَمْرِ الجَاهِلِيَّةِ لا يَتْرُكُونَهُنَّ: الفَخْرُ بِالأَحْسَابِ، والطَّعْنُ فِي الأَنْسَابِ، والاسْتِسقَاءُ بِالنُّجُومِ، والنِّيَاحَةُ». وقَالَ: النَّائِحَةُ إِذَا لَمْ تَتُبْ قَبْلَ مَوْتِهَا تُقَامُ يَوْمَ القِيَامَةِ وعَلَيْهَا سِرْبَالٌ مِنْ قَطِرَانٍ ودِرْعٌ مِنْ جَرَبٍ».

«ከተካታዮቼ ውስጥ ከቅድመ ኢስላም የጃሂልያ ዘመን የተወረሱ አራት ልምዶች አሁንም ድረስ ይገኛሉ:: እነርሱም በዘር መኩራራት፣ የሌሎች ዘሮችን ክብር ማጉደፍ፣ በከዋክብት ዝናብን መሻትና ሙሾ ማውረድ ናቸው::» (ሙስሊም ዘግበውታል)

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት ዘይድ ኢብን ኻሊድ ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«صَلَّى لَنَا رَسُولُ اللهِ ﷺ صلاةَ الصُّبْحِ بالحُدَيْبِيَةِ عَلى إِثْرِ سَماءٍ كَانَتْ مِنَ الليلِ فَلَمَّا انْصَرَفَ أَقْبَلَ عَلَى النَّاسِ فَقَالَ هَلْ تَدْرُونَ مَاذَا قَالَ رَبُّكُمْ؟ قَالوا: اللهُ ورَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ: قَالَ: أَصْبَحَ مِنْ عِبَادِي مُؤْمِنٌ بِي وكَافِرٌ. فأَمَّا مَنْ قَالَ مُطِرنَا بِفَضْلِ اللهِ ورَحْمَتِهِ فذلِكَ مُؤْمِنٌ بِي كَافِرٌ بالكَواكِبِ. وأَمَّا مَنْ قَال: مُطِرْنَا بِنَوءِ كَذَا وكَذَا فَذالِكَ كَافِرٌ بِي مُؤْمِنٌ بالكَواكِبِ.»

የአላህ መልዕክተኛ ሁደይቢያ ላይ ሌሊት ካፊያ ከጣለ በኋላ የሱብሂን ሶላት አሰገዱን:: ሰግደው እንዳጠናቀቁ ፊታቸውን ወደ ሰዎች በማዞር:- «ፈጣሪያችሁ ምን እንዳለ ታውቃላችሁን?» ሲሉ

ጠየቁ:: «አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ» የሚል ምላሽ ተሰጣቸው:: «ከባሮቼ ከፊሎቹ በተመሳሳይ ጊዜ በኔ ላይ አማኞችም፣ ካፊሮችም ይሆናሉ:: በአላህ እዝነትና ትሩፋት ዝናብ ለማግኘት በቃን፥ ያለ በኔ አምኖ በከዋክብት ክዷል:: በእገሌ፣ በእገሌ ከዋክብት እንቅስቃሴ ዝናብ አገኘን፥ ያለ በኔ ክዶ በከዋክብት አምኗል፥ ብሏል» አሉ::

ቡኻሪና ሙስሊም ኢብን ዓባስን በመጥቀስ ተመሳሳይ መንፈስ ያለው ዘገባ አስተላልፈዋል::

በቅድመ ኢስላም የጃሂሊያ ዘመን አረቦች ዝናብ በሚዘንብ ጊዜ፣ በዚህ ኮከብ እንቅስቃሴ (ነውእ) ነው የዘነበልን፥ የሚል ዓይነት አባባል ነበራቸው:: ይህን በማስመልከት አላህ ተከታዩን የቁርአን አንቀፅ አወረደ:-

﴿ فَلَآ أُقْسِمُ بِمَوَٰقِعِ ٱلنُّجُومِ ۝ وَإِنَّهُۥ لَقَسَمٌ لَّوْ تَعْلَمُونَ عَظِيمٌ ۝ إِنَّهُۥ لَقُرْءَانٌ كَرِيمٌ ۝ فِى كِتَٰبٍ مَّكْنُونٍ ۝ لَّا يَمَسُّهُۥٓ إِلَّا ٱلْمُطَهَّرُونَ ۝ تَنزِيلٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ۝ أَفَبِهَٰذَا ٱلْحَدِيثِ أَنتُم مُّدْهِنُونَ ۝ وَتَجْعَلُونَ رِزْقَكُمْ أَنَّكُمْ تُكَذِّبُونَ ﴾

*«በከዋክብት መጥለቂያዎች እምላለሁ፤ እርሱም ብታውቁ ታላቅ መሐላ ነው:: እርሱ የከበረ ቁርአን ነው:: በተጠበቀ መጽሐፍ ውስጥ ነው:: የተጥራሩት እንጂ ሌላ አይነካውም:: ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው:: በዚህ ንግግር እናንተ ቸልተኞች ናችሁን? ሲሳያችሁንም (ዝናብን) እናንተ የምታስተባብሉ ታደርጋላችሁን?» (አል-ዋቂዐህ : 75-80)*

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ዋቂዐህ 82» ትርጉም::
2. በቅድመ ኢስላም የጃሂልያ ዘመን የነበሩ አራት ልምዶች ተወስተዋል::
3. ከነኝህ ልምዶች መሐከል ከፊሎቹ ለኩፍር ያበቃሉ::
4. ከኢስላም የሚያስወጣ የኩፍር ዓይነት::
5. አላህ:- «ባሪያዬ በተመሳሳይ ጊዜ በኔ ያምናል፣ ይክዳልም» ማለቱ ተወስቷል:: ሰበቡም የሚለገሳቸው ፀጋ እንደሆነ ተመልክቷል::
6. በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ስር ኢማን የሚኖረውን ሚና መረዳት::

7. በእንዲህ ዓይነት ሁኔታዎች ስር ኩፍር የሚኖረውን ሚና መረዳት::

8. «በእገሌ በእገሌ ከዋክብት ዝናብ አገኘን» የሚለውን አባባል መረዳት::

9. አንድን የማይታወቅ እውነታ ጥያቄዎችን በማንሳት ማስተማር:: ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ):- «ፈጣሪያችሁ ምን እንዳለ አውቃችሁን?» ሲሉ ሶሐቦችን ጠይቀዋል::

10. ሙሾ እያወረዱ ለሙታን ማልቀስ በጥብቅ የተወገዘ ተግባር ነው::

# ምዕራፍ ሰላሳ ስንድ
## (የአላህ ፍቅር)

አላህ እንዲህ ይላል:-

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادًا يُحِبُّونَهُمْ كَحُبِّ ٱللَّهِ ﴾

*«ከሰዎችም ከአላህ ሌላ ባእታትን አላህን እንደሚወዱ አድርገው የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አሉ::» (አል-በቀራህ :165)*

﴿ قُلْ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمْ وَأَبْنَآؤُكُمْ وَإِخْوَٰنُكُمْ وَأَزْوَٰجُكُمْ وَعَشِيرَتُكُمْ وَأَمْوَٰلٌ ٱقْتَرَفْتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٌ تَخْشَوْنَ كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرْضَوْنَهَآ أَحَبَّ إِلَيْكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَجِهَادٍ فِى سَبِيلِهِۦ فَتَرَبَّصُوا۟ حَتَّىٰ يَأْتِىَ ٱللَّهُ بِأَمْرِهِۦ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴾

*«አባቶቻችሁና ወንዶች ልጆቻችሁም፣ ሚስቶቻችሁም፣ ዘመዶቻችሁም፣ የሰበሰባችኋቸው ሐብቶችም፣ መክሰርዋን የምትፈሩት ንግድም፣ የመትወዷቸው መኖሪያዎችም ከናንተ ዘንድ ከአላህና ከመልዕክተኛው፣ በርሱ መንገድ ከመታገልም ይበልጥ የተወደዱ እንደሆኑ አላህ ትዕዛዙን እስኪያመጣ ድረስ ተጠባበቁ::» (አል-ተውባህ: 29)*

አነስ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለውን ተናግረዋል:-

«لا يُؤمِنُ أَحَدُكُمْ حتَّى أَكُونَ أَحَبَّ إليْهِ مِنْ وَلَدِهِ وَوالِدِهِ والنَّاسِ أَجْمَعِينَ».

*«ከናንተ አንዳችሁ ከልጁ፣ ከወላጆቹና ከሰው ዘር ባጠቃላይ ከርሱ ዘንድ እኔ ይበልጥ ተወዳጅ እስካልሆንኩ ድረስ፣ አላመነም::» (ቡኻሪና ሙስሊም)*

ቡኻሪና ሙስሊም አነስን (ረዐ) ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) የሚከተለው ተናግርዋል:-

«ثَلاثٌ مَنْ كُنَّ فِيهِ وَجَدَ بِهِنَّ حَلاوَةَ الإيمَانِ: أَنْ يَكُونَ الله ورَسُولُهُ أَحَبَّ إليْهِ مِمَّا سِوَاهُمَا وأَنْ يُحِبَّ المَرْءَ لا يُحِبُّهُ إلاَّ لله. وأَنْ يَكْرَهِ أَنْ يَعُودَ في الكُفرِ بَعْدَ إذْ أنْقَذَهُ الله مِنْهُ كَمَا يَكْرَهُ أَنْ يُقْذَفَ في النَّارِ».

«ሦስት ባህሪያት ያሉት ሰው የኢማንን ለዛ አጣጥሟል፤ ከማንም ይበልጥ አላህና መልዕክተኛው ከሱ ዘንድ ተወዳጅ መሆናቸው፣ አንድን ሰው ሲወደው ለአላህ ብሎ መሆኑና አላህ ከኩፍር ካዳነው በኋላ እንደገና ወደ ኩፍር መመለስን ከእሳት ውስጥ የመጨመር ያህል ሲጠላ።»

በሌላ ዘገባ ደግሞ:-

«لا يَجِدُ أحدٌ حَلاوَةَ الإيمانِ حتَّى يُحِبَّ المَرْءَ لا يُحِبُّه إلاَّ لله».

«ከናንተ አንዳችሁ አንድን ሰው ሲወድ ለአላህ ብቻ ብሎ እስካልሆነ ድረስ የኢማንን ለዛ አያጣጥምም»

የሚል ተወስቷል።

የአላህ መልዕክተኛ (ሰዐወ) ተከታዩን መናገራቸውን ኢብን አባስ (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«مَنْ أحَبَّ في الله وأبغَضَ في الله، ووالى في الله وعَادى في الله فإنَّمَا تَنالُ ولايَةَ الله بِذلِكَ، ولَنْ يَجِدَ عَبْدٌ طَعْمَ الإيمَانِ وإنْ كَثُرَتْ صلاتُهُ وصَومُه حتَّى يَكُونَ كذلِكَ، وقَدْ صَارَتْ عامَّةُ مُواخَاةِ النَّاسِ عَلى أمرِ الدُّنْيا وذَلِكَ لا يُجْدِي عَلىأهْلِهِ».

«ለአላህ ሲል የወደደና ለአላህ ሲል የጠላ፣ ለአላህ ሲል የተወዳጀና ለአላህ ሲል ወዳጅነቱን ያቋረጠ የአላህን ወዳጅነት ያተርፋል። አንድ ባሪያ ባህሪው እንዲህ እስካልሆነ ድረስ ሶላቱና ፆሙ የቱን ያህል ቢበዙም የኢማንን ለዛ አያጣጥምም። አብዛኛዎቹን ሰዎች ከሌሎች ጋር የሚያወዳጃቸው አለማዊ ጉዳይ ነው። እንዲህ አይነቱ ወዳጅነት ደግሞ ቅንጣት አይፈይድም።» (ኢብን ጀሪር ዘግበውታል)

ኢብን አባስ:- «በነርሱ (መካከል) ምክንያቶች በተቆረጡ ጊዜ» (አል-በቀራህ: 165) የሚለውን ቁርአናዊ ቃል «ፍቅር ነው» ሲሉ አብራርተውታል።

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አልበቀራህ 105» ትርጉም።
2. የአንቅፅ «አልተውባህ 29» ትርጉም።
3. የአላህን መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ከገንዘብም፣ ከቤተሰብም፥ ሌላው ቀርቶ ከራስም በላይ ማፍቀር ግዴታ ነው።

4. ዘገባው ላይ የተወሳው «አያምንም» የሚል ቃል ከኢስላም ሙሉ በሙሉ መውጣትን አያመለክትም::

5. ኢማን ለዛና ጣዕም አለው:: ሰዎች ሊያጣጥሙት ይችላሉ:: የማያገኙት ሰዎችም አሉ::

6. አራት ባህሪያት ተጠቅሰዋል:: ያለነርሱ የአላህን የቅርብ ወዳጅነት ማግኘትም ሆነ የኢማንን ለዛ ማጣጣም አይቻልም::

7. የሰዎች ወዳጅነት የታነፀባቸው መሠረቶች ዓለማዊ ጉዳዮች መሆናቸውን ሶሃቦች መገንዘባቸው የሚገኙበትን ተጨባጭ ሁኔታ ምን ያህል ጠልቀው ይረዱ እንደነበር ያሳያል::

8. የአንቀፅ «አልበቀራህ 166» ትርጉም::

9. ከሙሽሪኮች መካከል አላህን በጥብቅ የሚያፈቅሩ እንደሚገኙ ተመልክቷል::

10. ከአንቀፅ «አል ተውባህ 26» ላይ የተጠቀሱትን ስምንት ነገሮች ከአላህና ከመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) አብልጦ ማፍቀር በጥብቅ መወገዙ::

11. አንድ ሰው አንድን አካል እንደ አላህ አድርጎ ካፈቀረ ይህ ድርጊቱ ታላቅ ሽርክ (ሺርኩል አክበር) ይሆናል::

# ምዕራፍ ሰላሳ ሁለት
# አላህን ብቻ መፍራት

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ إِنَّمَا ذَٰلِكُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ يُخَوِّفُ أَوْلِيَآءَهُۥ فَلَا تَخَافُوهُمْ وَخَافُونِ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴾

*«ይሃችሁ ሰይጣን ብቻ ነው:: ወዳጆቹን ያስፈራቸዋል:: አትፍሯቸውም፤ ምዕመናንም እንደሆናችሁ ፍሩኝ::» (አል-ኢምራን: 175)*

﴿ إِنَّمَا يَعْمُرُ مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ مَنْ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ وَأَقَامَ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَى ٱلزَّكَوٰةَ وَلَمْ يَخْشَ إِلَّا ٱللَّهَ فَعَسَىٰٓ أُو۟لَٰٓئِكَ أَن يَكُونُوا۟ مِنَ ٱلْمُهْتَدِينَ ﴾

*«የአላህን መስጊዶች የሚሠራው በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነ፣ ሰላትንም በደንብ የሰገደ፣ ግዴታ ምፅዋትንም የሰጠ፣ ከአላህም ሌላ ማንንም ያልፈራ ሰው ብቻ ነው፤ እነዚያ ከተመሩት ጭምር መሆናቸው ተረጋገጠ::» (አል-ተውባህ: 78)*

﴿ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ فَإِذَآ أُوذِىَ فِى ٱللَّهِ جَعَلَ فِتْنَةَ ٱلنَّاسِ كَعَذَابِ ٱللَّهِ ﴾

*«ከሰዎችም በአላህ አመንን የሚል ሰው አለ፤ ከአላህም ማዛወር በተሰቃዬ ጊዜ የሰዎችን ማሰቃየት እንደ አላህ ቅጣት ያደርጋል::» (አል-ዐንከቡት: 10)*

አቡሰዒድ «*መርፋዕ*» በሆነ ሰነድ ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«إنَّ مِنْ ضَعْفِ اليَقِينِ أنْ تُرضِيَ النَّاسَ بِسَخَطِ الله. وأنْ تَحْمَدَهُمْ عَلى رِزْقِ الله وأنْ تَذُمَّهُمْ على ما لَمْ يُؤتِكَ الله. إنَّ رِزْقَ الله لا يَجُرُّهُ حِرْصُ حَرِيصٍ لا يَرُدُّهُ كَرَاهِيَةُ كَارِهٍ».

«አላህ የማይፈቅደውን በመፈፀም ሰዎችን ማስደሰትህ፣ አላህ በለገሰህ ሪዝቅ (ሲሳይ) ሌሎችን ማወደስህና ሰዎችን አላህ በሰጣቸው ጉድለት መተቸትህ የእምነትህን ድክመት ያመለክታል:: የአላህ ሪዝቅ በሰዎች ጉጉት የሚመጣ ወይም ሰዎች ስላልፈለጉ የሚቀር አይደለም::»

አዒሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«مَنِ التَمَسَ رِضَى الله بِسَخَطِ النَّاسِ رَضِيَ الله عَنْهُ وأَرْضَى عَنْهُ النَّاسُ. ومَنِ التَمَسَ رِضَى النَّاسِ بِسَخَطِ الله سَخَطَ الله عَلَيهِ وأَسْخَطَ عَلَيْهِ النَّاسُ»

«የአላህን ውዴታ በመሻት ሰዎችን ያስከፋ አላህ ይወደዋል፤ ሰዎችም እንዲወዱት ያደርጋል:: አላህን በማስቆጣት የሰዎችን ውዴታ የከጀለ አላህ ይቆጣበታል፤ ሰዎች እንዲጠሉትም ያደርጋል::» (ኢብን ሒብባን ዘግበውታል)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አሊ-ዒምራን 175» ትርጉም::
2. የአንቅፅ «አል ተውባህ 18» ትርጉም::
3. የአንቀፅ «አል ዐንከቡት 10» ትርጉም::
4. እምነት (የቂን) ሊጠናከር ወይም ሊደክም ይችላል:
5. የእምነትን መዳከም ከሚያሳዩ ምልክቶች ሦስቱ ተወስተዋል::
6. አላህን ብቻ መፍራት ግዴታ ነው::
7. አላህን ብቻ የፈራ ሰው የሚያገኘው የላቀ ምንዳ::
8. አላህን ያልፈራ የሚጠብቀው አስከፊ ቅጣት::

# ምዕራፍ ሰላሳ ሦስት
## በአላህ ብቻ መመካት

አላህ እንዲህ ይላል:-

﴿ وَعَلَى ٱللَّهِ فَتَوَكَّلُوٓا۟ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴾

*«ምዕመናን እንደሆናችሁ በአላህ ላይ ተመኩ::» (አል-ማኢዳህ :23)*

﴿ إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ وَإِذَا تُلِيَتْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتْهُمْ إِيمَٰنًا وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ﴾

*«ፍፁም ምዕመናን እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩት፤ በነሱም ላይ አንቀፆች በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸው፤ በጌታቸው ላይ ብቻ የሚመኩ ናቸው::» (አል-አንፋል :2)*

﴿ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ حَسْبُكَ ٱللَّهُ وَمَنِ ٱتَّبَعَكَ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴾

*«አንተ ነብይ ሆይ ! በቂህ አላህ ነው፤ ለተከተሉህም ምዕመናን በቂያቸው ነው::»(አል-አንፋል: 64)*

﴿ وَمَن يَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ حَسْبُهُۥٓ ﴾

*«በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው::»(አል-ጠላቅ:3)*

ኢብን አብባስ (ረዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

﴿حَسْبُنَا الله ونِعْمَ الوَكيلُ﴾ قَالَها إبراهيمُ عليه السلام حينَ أُلقيَ في النَّارِ. وقَالَها مُحَمَّدٌ صلَّى الله عليه وسلَّم حينَ قَالُوا لَهُ:

﴿إنَّ النَّاسَ قعدْ جَمَعُوا لَكُمْ فَاخْشَوْهُم فَزَادَهُمْ إيمَاناً ﴾.

«ሐስቡን አላሁ ወኒዕመል ወኪል» (አላህ በቂያችን ነው፤ በርሱ መመካት ምን አማረ!) የሚለውን ቃል ነቢዩ ኢብራሂም እሳት ውስጥ በተጣሉ ዕለት ብለውታል:: ነቢዩ ሙሐመድም :- «ሰዎች ጦር አከማችተውላችኋልና ፍሯቸው ባሏቸው ጊዜ

ሁኔታው ኢማናቸውን ጨመረላቸው፤ ሐስቡነላህ ወኒዕመል ወኪል» አሉም።(ቡኻሪና ነሳኢ)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. በአላህ መመካት (ተወኩል) ግዴታ ነው።
2. «ተወኩል» የኢማን ጥንካሬና ድክመት ከሚለካባቸው መመዘኛዎች አንዱ ነው።
3. የአንቀፅ «አል አንፋል 2» ትርጉም።
4. የአንቀፅ «አል አንፋል 64» ትርጉም።
5. የአንቀፅ «አል ጦላቅ 3» ትርጉም።
6. «ሐስቡነላህ ወኒዕመል ወኪል» የሚለው ቃል ክብደት፤ ኢብራሂምም፣ ሙሐመድም ፈታኝ ሁኔታዎች በገጠሟቸው ጊዜ ብለውታል።

## ምዕራፍ ሰላሳ ስራት
## <u>ከአላህ ቅጣት መዘናጋት ከተውሂድ ጋር ይቃረናል</u>

አላህ እንዲህ ይላል:-

﴿ أَفَأَمِنُوا۟ مَكْرَ ٱللَّهِ ۚ فَلَا يَأْمَنُ مَكْرَ ٱللَّهِ إِلَّا ٱلْقَوْمُ ٱلْخَـٰسِرُونَ ﴾

*«የአላህንም ማዘናጋት አይፈሩምን? የአላህንም ማዘናጋት ከከሳሪዎች ህዝቦች ውጭ የሚተማመን የለም::»(አል-አዕራፍ: 99)*

﴿ قَالَ وَمَن يَقْنَطُ مِن رَّحْمَةِ رَبِّهِۦٓ إِلَّا ٱلضَّآلُّونَ ﴾

*«ስህተት ውስጥ ያሉት ቢሆኑ እንጂ ከጌታህ እዝነት ተስፋ የሚቆርጥ ማነው?» (አል-ሐጅር፥ 15-56)*

ኢብን ዓብባስ (ረዐ) እንዳስተላለፉት:-

«أَنَّ رَسُولَ الله ﷺ سُئِلَ عَنِ الكَبائِرِ فَقَالَ الشِّرْكُ بالله واليَأْسُ مِنْ رَوْحِ الله والأَمْنُ مِنْ مَكْرِ الله».

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ስለ ታላላቅ ወንጀሎች ተጠይቀው ሲመልሱ:- «በአላህ ላይ ማሻረክ፣ ከአላህ እዝነት ተስፋ መቁረጥና አላህ ከሚያመጣው ጥፋት መተማመን::» ብለዋል::

ኢብን መስዑድ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ):-

«أَكبَرُ الكَبَائِرِ الإِشْرَاكُ بالله والأَمْنُ مِنْ مَكْرِ الله والقُنُوطُ مِنْ رَحْمَةِ الله واليَأْسُ مِنْ رَوْحِ الله».

«የታላላቅ ወንጀሎች ሁሉ ቁንጮ በአላህ ማሻረክ፣ አላህ ከሚያመጣው ጥፋት መተማመንና ከአላህ እዝነት ተስፋ መቁረጥ ናቸው::» ብለዋል:: (አብዱረዛቅ ዘግበውታል)

### <u>ጠቃሚ ነጥቦች</u>

1. የአንቀፅ «አል አዕራፍ 99» ትርጉም::
2. የአንቀፅ «አል ሂጅር 56» ትርጉም::
3. አላህ ከሚያመጣው ጥፋት ተማምኖ ለተቀመጠ የተሰነዘረ አስደንጋጭ ዛቻና ውግዘት::
4. ከአላህ «ራህመት» ተስፋ የቆረጠም ተወግዟል::

# ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት
# <u>የአላህን ውሳኔ (ቀደር) በትዕግሥት ማስተናገድ (ሶብር) የኢማን አካል ስለመሆኑ</u>

አላህ እንዲህ ይላል:-

﴿وَمَن يُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ يَهْدِ قَلْبَهُۥ ۚ وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ﴾

*«በአላህም የሚያምን ሰው ልቡን ለትዕግሥት ይመራዋል:: አላህም ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነው::» (አል-ተጋቡን:11)*

ዓቅለማህ:- «ይህ (ከአንቀፁ ላይ የተጠቀሰው) ሰው አንዳች ችግር ሲገጥመው ከአላህ መሆኑን በመረዳት፣ በእርካታ የሚያስተናግድ ነው» ብለዋል::

ሙስሊም አቡሁረይራን ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«اثْنَتَانِ في النَّاسِ هُمَا بِهِمْ كُفْرٌ: الطَّعْنُ في النَّسَبِ والنِّيَاحَةُ عَلَى المَيِّتِ».

«ከሰዎች ላይ የሚታዩ ሁለት ባህሪያት የኩፍር መገለጫዎች ናቸው፤ የሌሎችን ዘር ክብር ማጉደፍና ለሙታን ሙሾ ማውረድ::»

ቡኻሪና ሙስሊም ኢብን መስዑድን በመጥቀስ «መርፉዕ» በሆነ ሰነድ እንደዘገቡት መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«لَيْسَ مِنَّا مَنْ ضَرَبَ الخُدُودَ وشَقَّ الجُيُوبَ ودَعَا بِدَعْوى الجَاهِلِيَّةِ».

«በሃዘን ወቅት ፊቱን የሚመታ፣ ልብሱን የሚቀድና በቅድመ ኢስላም አረቦች ይፈፀም እንደነበረው አለቅጥ ድምፅን ከፍ በማድረግ ሙሾ የሚያወርድ ከኛ ውጭ ነው::»

አነስ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«إذا أرَادَ الله بعَبدِهِ الخيرَ عَجَّلَ له العقوبة في الدنيا وإذَا أرَادَ الله بِعَبدِهِ الشَّرَّ أمْسَكَ عَنهُ بِذَنْبِهِ حتَّى يُوافى بِهِ يَوْمَ القِيامَةِ».

«አላህ ለባሪያው ደግን ነገር ሲወስንለት ቅጣቱን በዚህች ዓለም ያደርግለታል:: መጥፎ ሲወስንበት ደግሞ ሐጢአቱን ሁሉ በመያዝ ቅጣቱን እስከ ዕለተ ቂያማ ያዘገይበታል::»

እንዲህም ሲሉ ተደምጠዋል:-

«إِنَّ عِظَمَ الجَزَاءِ مَعَ عِظَمِ البَلَاءِ. وإِنَّ الله تَعَالَى إِذَا أَحَبَّ قَوْماً ابتَلَاهُمْ. فَمَنْ رَضِيَ فَلَهُ الرِّضَا ومَنْ سَخِطَ فَلَهُ السَّخَطُ».

«ታላቅ ምንዳ ከታላቅ ፈተና ጋር ነው:: አላህ ሰዎችን ሲወዳቸው ይፈትናቸዋል:: የሚደርስበትን ፈተና ሁሉ በትዕግሥ ያስተናገደ የአላህን እርካታ ይጎናፀፋል: የተበሳጨ የአላህን ቁጣ ያተርፋል::» (ቲርሚዚ)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ተጋቡን 11» ትርጉም::
2. ይህ ባህሪ ኢማናዊ ነው::
3. የሌሎችን የዘር ክብር ማጉደፍ ክልክል መሆኑ ተወስቷል::
4. በሃዘን ወቅት ፊታቸውን የሚመቱ፣ ልብሶቻቸውን የሚቀዱና ሙሾ የሚያወርዱ በጥብቅ ተወግዘዋል::
5. አላህ ለባሪያው ኸይርን የመሻቱ ምልክት::
6. ክፉን ነገር የማቀዱ ምልክት::
7. አላህ ባሪያውን የመውደዱ ምልክት::
8. በአላህ ውሳኔዎች መበሳጨት ክልክል መሆኑ::
9. የሚደርሱበትን ፈተናዎች በፀጋና በትዕግሥት ያስተናገደ የሚያገኘው የላቀ ምንዳ::

# ምዕራፍ ሰላሳ ስድስት
# አንድን ተግባር ለታይታ መፈፀም (ሪያእ) ክልክል ስለመሆኑ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَمَن كَانَ يَرْجُوا۟ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلْيَعْمَلْ عَمَلًا صَٰلِحًا وَلَا يُشْرِكْ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدًۢا ﴾

*«እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ወደ እኔ የሚወረድልኝ ብጤያችሁ ሰው ብቻ ነኝ:: የጌታውንም መገናኘት የሚፈልግ ሰው መልካም ሥራን ይስራ፤ በጌታውም መገዛት አንድንም አያጋራ::»(አል-ካህፍ:110)*

አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«أَنَا أَغْنَى الشُّرَكَاءِ عَنِ الشِّرْكِ مَنْ عَمِلَ عَمَلاً أَشْرَكَ مَعِي فِيْهِ غَيْرِي تَرَكْتُهُ وشِرْكَه».

«አላህ፥ ሽሪክ እንዲደረግብኝ ፈፅሞ አልሻም፤ ከኔ ጋር ሌላን አካል በማጋራት አንድን ተግባር የፈፀመ ከነሽርኩ እተወዋለሁ፥ ብሏል::» (ሙስሊም ዘግበውታል)

አቡሰዒድ መርፉዕ በሆነ ሰነድ ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«ألا أُخبِرُكُم بِمَا هُوَ أَخوَفُ عَلَيْكُمْ عِنْدي مِنَ المَسيحِ الدَّجَّالِ؟ قَالُوا بَلى يَا رَسُولَ الله. قَالَ الشِّرْكُ الخَفِيُّ يَقُومُ الرَّجُلُ فَيُصَلِّي فَيُزَيِّنُ صلاتَهُ لِمَا يَرى مِنْ نَظَرِ رَجُلٍ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) :- «ከአል-መሲህ ደጃል የበለጠ ለናንተ የምፈራላችሁን ልንገራችሁን?» በማለት ጠየቁ:: «አዎ! የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ይንገሩን::» አሏቸው- ሰሃቦች:: «ድብቅ ሽርክን ነው:: አንድ ሰው ሶላት ለመስገድ ይቆማል:: ሌላ ሰው እየተመለከተው እንደሆነ ሲያውቅ ባማረ ሁኔታ ይሰግዳል» አሉ:: (አህመድ ዘግበውታል)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ካህፍ 110» ትርጉም::

2. አላህ አንድን ተግባር ሙሉ በሙሉ በኢኽላስ ለርሱ ብቻ እስካልተፈፀመ ድረስ- ውድቅ እንደሚያደርገው::

4. አላህ እንዲህ ዓይነቱን ተግባር የማይቀበልበት ሰበብ ተወስቷል::

5. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) «ሪያእ»ን ለሶሃቦቻቸው አጥብቀው ይጠነቀቁና ይፈሩ ነበር::

6. ለ«ሪያእ» የሰጡት ትርጓሜ፤ አንድ ሰው ሶላት ይሰግዳል:: ሌሎች እየተመለከቱት እንደሆነ ሲያውቅ ሶላቱን እጅግ ያሳምራል::

## ምዕራፍ ሰላሳ ሰባት
## አንድ ሰው በመልካም ተግባሩ የዚህችን ዓለም ፀጋ መሻቱ ከሽርክ ይፈረጃል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ مَن كَانَ يُرِيدُ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيْهِمْ أَعْمَٰلَهُمْ فِيهَا وَهُمْ فِيهَا لَا يُبْخَسُونَ ○ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَيْسَ لَهُمْ فِى ٱلْءَاخِرَةِ إِلَّا ٱلنَّارُ وَحَبِطَ مَا صَنَعُوا فِيهَا وَبَٰطِلٌ مَّا كَانُوا يَعْمَلُونَ﴾

*«ቅርቢቱን ህይወትና ጌጧን የሚሹ የሆኑትን ሰዎች ስራዎቻቸውን ምንዳዋን በርሷ ውስጥ ወደ እነርሱ እንሞላላቸዋለን:: እነርሱም በርሷ ውስጥ ምንም አይጎድልባቸውም:: እነዚያ እነሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ለነርሱ ከእሳት በቀር የሌላቸው ናቸው:: የሰሩትም ስራ በርሷ ውስጥ ተበላሸ:: በቅርቢቱ ዓለም ይሰሩት የነበሩትም በጎ ሥራ ብልሹ ነው::»(ሁድ:15-16)*

ቡኻሪ እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን መናገራቸውን አቡ ሁረይራ አስተላልፈዋል:-

«تَعِسَ عَبْدُ الدِّينَارِ تَعِسَ عَبْدُ الدِّرْهَمِ تَعِسَ عَبْدُ الخَمِيصَةِ تَعِسَ عَبْدُ الخَمِيلَةِ، أَنْ أُعطِي رَضِيَ وإِنْ لَمْ يُعْطَ سَخِطَ تَعِسَ وانْتَكِسَ وإذَا شِيكَ فَلا انْتُقِشَ طُوبى لِعَبدٍ أَخَذَ بِعَنَانِ فَرَسِهِ فِي سَبِيلِ الله، أَشْعَثَ رَأْسُهُ، مُغْبَرَّةٌ قَدَمَاهُ إنْ كَانَ فِي الحِرَاسَةِ كَانَ فِي الحِرَاسَةِ وإنْ كَانَ فِي السَّاقَةِ كَانَ فِي السَّاقَةِ إنِ اسْتَأْذَنَ لَمْ يُؤْذَنَ لَهُ، وإنْ شَفَعَ لَمْ يُشَفَّعْ».

«የገንዘብ ባሪያ ጠፋ (ከሰረ)፤ የልብሶች ባሪያ ጠፋ፤ ሲሰጠው ይደሰታል፣ ሲነፈገው ይበሳጫል:: ጠፋ፤ ለውድቀት ተዳረገም:: እሾህ ሲወጋው ማውጣት አይቻል:: መጨረሻው ያማረ አይሁን:: የፈረሱን ልጓም ይዞ በአላህ መንገድ (ፊ ሰቢሊላህ) የተንቀሳቀሰ፤ ፀጉሩ ተንጨባሮ፣ እግሩ በአባሯ ተሸፍኖ፤ በጥበቃ ስራ ላይ ሲሰማራ ነቅቶ ይጠብቃል:: በተራ ወታደርነት ሲመደብ ተግባሩን በሚገባ ያከናውናል:: ፈቃድ ቢጠይቅ አይፈቀድለትም::

ሰዎችን ለማሽማገል ቢቀርብ ሽምግልናው ተደማጭነት የለውም:: እንዲህ ዓይነቱ ሰው እጅግ እድለኛ ነው::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ሰዎች የአኼራን ተግባር ፈፅመው ዱንያን መከጀላቸው::

2. የአንቀፅ «ሁድ 15-16» ትርጉም::

3. አንድን ሙስሊም «የገንዘብ ባሪያ፣ የልብስ ባሪያ ወዘተ» በሚል ቅፅል መጥራት እንደሚፈቀድ::

4. «ሲሰጠው ይደሰታል፣ ሲነፈገው ይበሳጫል» የሚለው አገላለጽ::

5. ጠፋ፤ ለውድቀት ተዳረገም ማለታቸው::

6. «እሾህ ሲወጋው የማውጣት አቅሙ አይኑረው» በማለት መራገማቸው::

7. ከዘገባው ላይ የተጠቀሱ ውብ ባህሪያት ያሉትና በአላህ መንገድ ላይ የሚታገል ሰው የላቀ ክብር::

## ምዕራፍ ሰላሳ ስምንት

## ዑለሞችንና መሪዎችን አላህ ሐላል ያደረገውን ነገር ሐራም፣ ሐራም ያደረገውን ደግሞ ሐላል ሲያደርጉ መከተል እነርሱን አምላክ (ረብ) አድርጎ መያዝ ነው

ኢብን ዓብባስ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

«يُوشَكَ أَنْ تَنْزِلَ عَلَيْكُمْ حِجَارَةٌ مِنَ السَّمَاءِ. أَقُولُ قَالَ رَسُولُ اللهِ ﷺ وَتَقُولُونَ قَالَ أَبُو بَكْرٍ وعُمَرُ».

«እኔ፣ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል እያልኩ እናንተ አቡበክርና ዑመር እንዲህ አሉ ትሉኛላችሁ? ከሰማይ የድንጋይ ዶፍ ሊዘንብባችሁ ቀርቧል::»

ኢማም አህመድ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:- «የአንድን የሐዲስ ዘገባ ሰነድ ትክክለኛነት በሚገባ እያወቁ ለሱፊያን ግላዊ አመለካከት ቅድሚያ የሚሰጡ ሰዎች እጅግ ያስደንቁኛል:: አላህ እንዲህ ሲል (ሙዕሚኖችን) አስጠንቅቋል:-

﴿فَلْيَحْذَرِ ٱلَّذِينَ يُخَالِفُونَ عَنْ أَمْرِهِۦٓ أَن تُصِيبَهُمْ فِتْنَةٌ أَوْ يُصِيبَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ﴾

«እነዚያ ትዕዛዙን የሚጥሱ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ::» (አል-ኑር :63)

ከአንቀፁ ላይ «መከራ» በሚል የተወሳው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ሽርክ ነው:: አንድን የነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) አስተምህሮች ውድቅ ማድረግ ቀልብን ለጥመት በመዳረግ ለጥፋት ያበቃል::

ዐደይ ኢብን ሐቲም እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«أَنَّهُ سَمِعَ النَّبِيَّ ﷺ يَقْرَأُ هذِهِ الآيَةَ:

﴿ٱتَّخَذُوٓا۟ أَحْبَارَهُمْ وَرُهْبَـٰنَهُمْ أَرْبَابًا مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَٱلْمَسِيحَ ٱبْنَ مَرْيَمَ وَمَآ أُمِرُوٓا۟ إِلَّا لِيَعْبُدُوٓا۟ إِلَـٰهًا وَٰحِدًا ۖ لَّآ إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ ۚ سُبْحَـٰنَهُۥ عَمَّا يُشْرِكُونَ﴾

فَقُلْتُ لَهُ إِنَّا لَسْنَا نَعْبُدُهُم، قَالَ: أَلَيْسَ يُحَرِّمُونَ مَا أَحَلَّ اللهُ فَتُحَرِّمُونَهُ، وَيُحَلِّلُونَ مَا حَرَّمَ اللهُ فَتُحِلُّونَه؟ فَقُلْتُ بَلَى. قَالَ: فَتِلْكَ عِبَادَتُهُمْ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን የቁርአን አንቀፅ ሲያነቡ አዳምጥኩ፤ «ሊቃውንቶቻቸውንና መነኩሳቶቻቸውን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ፤» (አል-ተውባህ :31)

«አናመልካቸውም ነበር» አልኳቸው:: «አላህ ሐላል ያደረገውን ሐራም፣ ሐራም ያደረገውን ሐላል ሲያደርጉ ያለ ተቃውሞ ትቀበሏቸው የለምን?» አሉ:: «አዎ» አልኳቸው:: «እነርሱን ማምለክ ማለት ይኸው ነው::» ሲሉ አብራሩልኝ::» (አህመድና ቲርሚዚ)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ኑር 63» ትርጉም::
2. የአንቀፅ «አል ተውባህ 31» ትርጉም::
3. የ«ዒባዳ» ትክክለኛ ትርጓሜ::
4. ኢብን ዓብባስ የአቡበክርንና የዑመርን፣ አህመድ ደግሞ የሱፍያንን ስም በመጥቀስ ምሳሌ መስጠታቸው::
5. ሁኔታዎች በሚያስደንቅ አኳኋን ተቀያይረዋል:: የሐይማኖት ሰዎችን ማምለክ እንደ ትልቅ የዒባዳ ክንውን ይቆጠራል፤ «ዊላያ» በሚል ስያሜ:: ሊቃውንትን ማምለክ እውቀት ሆኗል፤ ጥበብ:: ነገሮች እጅግ ተለዋወጠው ከዚህ የከፋ ሁኔታም ተከሰተ:: መጥፎ ሰዎችንና መሐይማንን ማምለክ ተጀመረ::

# ምዕራፍ ሰላሳ ዘጠኝ
## ከአላህና ከመልዕክተኛው ዳኝነት ውጭ የሌሎችን ዳኝነት መሻት መናፍቅነት ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ يَزْعُمُونَ أَنَّهُمْ ءَامَنُوا۟ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْكَ وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبْلِكَ يُرِيدُونَ أَن يَتَحَاكَمُوٓا۟ إِلَى ٱلطَّٰغُوتِ وَقَدْ أُمِرُوٓا۟ أَن يَكْفُرُوا۟ بِهِۦ وَيُرِيدُ ٱلشَّيْطَٰنُ أَن يُضِلَّهُمْ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا ۝ وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا۟ إِلَىٰ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ وَإِلَى ٱلرَّسُولِ رَأَيْتَ ٱلْمُنَٰفِقِينَ يَصُدُّونَ عَنكَ صُدُودًا ۝ فَكَيْفَ إِذَآ أَصَٰبَتْهُم مُّصِيبَةٌۢ بِمَا قَدَّمَتْ أَيْدِيهِمْ ثُمَّ جَآءُوكَ يَحْلِفُونَ بِٱللَّهِ إِنْ أَرَدْنَآ إِلَّآ إِحْسَٰنًا وَتَوْفِيقًا﴾

*«ወደነዚያ እነርሱ በአንተ ላይ በተወረደውና ከአንተ በፊትም በተወረደው አምነናል ወደሚሉት አላየህመን? በእርሱ እንዲክዱ በእርግጥ የታዘዙ ሲሆኑ ወደ ጣኦት መፋረድን ይፈልጋሉ:: ሰይጣንም (ከእውነት) የራቀን መሳሳት ሊያሳስታቸው ይፈልጋል::» (አል-ኒሳእ :60)*

﴿وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا تُفْسِدُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ قَالُوٓا۟ إِنَّمَا نَحْنُ مُصْلِحُونَ﴾

*«ለነርሱም በምድር ላይ አታበላሹ በተባሉ ጊዜ እኛ አሳማሪዎች ብቻ ነን ይላሉ::» (አል-በቀራህ :11)*

﴿وَلَا تُفْسِدُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَٰحِهَا وَٱدْعُوهُ خَوْفًا وَطَمَعًا ۚ إِنَّ رَحْمَتَ ٱللَّهِ قَرِيبٌ مِّنَ ٱلْمُحْسِنِينَ﴾

*«በምድርም ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ:: ፈርታችሁና ከጅላችሁም ተገዙት:: የአላህ ችሮታ ከበጎ አድራጊዎች ጋር ነውና::» (አል-አዕራፍ.:*56)

﴿أَفَحُكْمَ ٱلْجَٰهِلِيَّةِ يَبْغُونَ ۚ وَمَنْ أَحْسَنُ مِنَ ٱللَّهِ حُكْمًا لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ﴾

*«የመሃይምነትን ፍርድ ይፈልጋሉን? ለሚያረጋግጡ ሰዎች ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?» (አል-ሚእዳህ:50)*

አብደላ ኢብን ዑመር (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) :-

«لا يُؤمِنُ أَحَدُكُمْ حتَّى يَكُونَ هَوَاهُ تَبَعاً لِمَا جِئْتُ بِهِ».

«ከናንተ አንዳችሁ፣ ስሜቱ እኔ ካመጣሁት መልዕክት ጋር እስካልተጣጣመ ድረስ አላመነም» ብለዋል:: (ነውውይ ሶሒሕ ዘገባ መሆኑን አፅድቀዋል)

ሸዕብይ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

በአንድ የሁዳና በአንድ ሙናፊቅ መካከል ውዝግብ ተነሳ:: የሁዳው:- «ውዝግባችንን ሙሐመድ ይፍታልን» የሚል ሐሳብ አቀረበ:: ጉቦ እንደማይቀበሉ ጠንቅቆ ያውቃል:: ሙናፊቁ ደግሞ «የየሁዳዎች ብይን ይሻለናል» አለ:: ጉቦ እንደሚቀበሉ በመረዳቱ:: ጁሐይና ውስጥ ይገኝ የነበረ አንድ ቄስ የሚሰጠውን ብይን ለመቀበል ተስማሙ:: ይህን በማስመልከት «አል ኒሳእ 6» ወረደች::

በሌላ ዘገባ እንደተወሳው ደግሞ ይህች አንቀፅ የወረደችው ሁለት ሰዎችን በማስመልከት ነው::

አንደኛው:- «ጉዳያችንን ከነቢዩ ዘንድ እናቀርብ» ሲል፥ ሌላኛው «ከብዕብ ኢብነል አሽረፍ ዘንድ እናቀርብ» አሉ:: በመጨረሻም ከዑመር ዘንድ አቀረቡት:: አንደኛው ታሪኩን አጫወታቸው:: የመልዕክተኛውን ዳኝነት ለመቀበል ፈቃደኛ ላልሆነው:- «የተባለው እውነት ነውን?» ሲሉ ጠየቁት:: «አዎ» አላቸው:: አንገቱን በሰይፍ ቀልተው ገደሉት::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ኒሳእ 60» ትርጉም:: ስለ ጣኦት ጥሩ ግንዛቤ ያስጨብጣል::
2. የአንቀፅ «አል በቀራህ 11» ትርጉም::
3. የአንቀፅ «አል አዕራፍ 56» ትርጉም::
4. የአንቀፅ «አል ማኢዳህ 50» ትርጉም::
5. «አል ኒሳእ 60» የወረደችበትን ሰበብ አስመልክቶ ሸዕብይ ያስተላለፉት ቁም ነገር::
6. የእውነተኛ እምነትና ትክክለኛ ያልሆነ እምነት መለያ ባህሪያት::
7. የዑመርና የሙናፊቁ ታሪክ::
8. አንድ ሰው ኢማን አለው ሊባል የሚችለው ስሜቱ ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ካመጡት መልዕክት ጋር ሙሉ በሙሉ መጣጣም ሲችል ብቻ ነው::

## ምዕራፍ አርባ
## የአላህን ስሞችና ባህሪያት ስለመካድ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَهُمْ يَكْفُرُونَ بِالرَّحْمَٰنِ قُلْ هُوَ رَبِّي لَا إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ وَإِلَيْهِ مَتَابِ ﴾

*«እነሱ በአል ረህማን የሚክዱ ሲሆኑ»(አል-ሒጅር :30)*

ሶሒሕ አል ቡኻሪ ውስጥ እንደሰፈረው ዓሊይ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

«حَدِّثُوا النَّاسَ بِمَا يَعْرِفُونَ أَتُرِيدُونَ أَنْ يُكَذَّبَ اللهُ ورَسُولَهُ ؟»

«ሰዎችን በእውቀት ደረጃቸው ልክና በሚገባቸው መልኩ አስተምሩ:: አላህንና መልዕክተኛውን እንዲያስተባብሉ ትሻላችሁን?»

ኢብን አባስ ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«أَنَّه رَأى رَجُلاً انْتَفَضَ لمَّا سَمِعَ حَدِيثاً عَنِ النَّبِيِّ ﷺ في الصِّفَاتِ اسْتِنْكاراً لِذَلِكَ. فَقَالَ مَا فَرَقُ هؤُلاءِ يَجِدُونَ رِقَّةً عِنْدَ مُحْكَمِهِ ويَهْلِكُونَ عِنْدَ مُتَشَابِهِهِ».

አንድ ሰው ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ስለ አላህ ባህሪያት ሲናገሩ ያደመጠውን ላለመቀበል ሲያንገራግር ተመለከቱት፤ የሰማውን ባለማመን:: «የነኝህ ሰዎች ችግር ምንድን ነው? አሻሚ ያልሆነ (ሙሕከም) የቁርአን አንቀፅ ሲነበብ በመስማማት ይቀበላሉ:: አሻሚ ትርጉም ያላቸው (ሙተሻቢህ) የቁርአን አንቀፆች ሲደመጡ ላለመቀበል በማንገራገር ለጥፋት ይዳረጋሉ» ሲሉ ተናገሩ::

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ረህማን የሚል ቃል ሲያወሱ ሙሽሪኮች አስተባበሉ:: አላህ:-

﴿ وَهُمْ يَكْفُرُونَ بِالرَّحْمَٰنِ ﴾

«በአል ረህማን የካዱ ሲሆኑ»
የሚል የቁርአን አንቀፅ አወረደ::

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. ከአላህ ስሞችና ባህሪያት አንዱንም አለመቀበል ከኢስላም ውጭ ያደርጋል::

2. የአንቀፅ «አል ረዐድ 30» ትርጉም።

3. ታዳሚው ሊረዳው የማይችለውን ነገር ከመናገር መቆጠብ ተገቢ ነው።

4. የዚህ ምክንያቱ ተወስቷል። በማወቅም ይሁን ባለማወቅ የአላህንና የመልዕክተኛውን አስተምህሮቶች ለመካድ ጥፋት ሊዳርግ ስለሚችል።

5. የኢብን ዓብባስ ገለፃ። አሻሚ የቁርአን አንቀጾች ካስተላለፉት መልዕክት አንዱንም ያስተባበለ ለጥፋት የተዳረገ መሆኑን በአፅንኦት ገልፀዋል።

# ምዕራፍ አርባ አንድ
# የአላህን ፀጋዎች መካድ ኩፍር ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ يَعْرِفُونَ نِعْمَتَ ٱللَّهِ ثُمَّ يُنكِرُونَهَا وَأَكْثَرُهُمُ ٱلْكَٰفِرُونَ ﴾

«የአላህን ፀጋ ያውቃሉ፣ ከዚያም ይክዱታል:: አብዛኛዎቻቸውም ከሐዲዎች ናቸው» (አል-ነሕል:83)

ሙጃሂድ ስለዚህ አንቀፅ ትርጉም ሲናገሩ:- «አንድ ሰው ይህ ከወላጆቼ የወረስኩት ገንዘቤ ነው ማለቱ ከዚህ ውስጥ ይካተታል» ብለዋል::

አውን ኢብን ዐብደላህ ደግሞ:- « እገሌ ባይኖር ይህ አይሆንም ነበር፡ ይላሉ» ብለዋል::

ኢብን ቁተይባህ:- «ይህ የሆነው በአምላኮቻችን ትድግና ነው፣ ይለሉ» ሲሉ አብራርተውታል::

አላህ :- «ባሪያዬ በተመሳሳይ ወቅት በኔ ያምናል፣ ይክዳልም» እንዳለ ለተወሳበትና በዘይድ ኢብን ልኻሊድ ለተላለፈው ዘገባ አቡል ዓባስ እንዲህ ሲሉ ተጨማሪ ማብሪሪያ ሰጥተዋል:-

«አላህ ፀጋውን ከርሱ ውጭ ወደ ሌላ አካል በማስጠጋት ሽርክ የፈፀሙ ሰዎችን በጥብቅ ያወገዘባቸው የቁርአንና የሐዲስ ዘገባዎች በርካታ ናቸው::» ከሰለፎች ከፊሎቹ:- «ንፋሱ ጥሩ ነበር፤ ፓይለቱ የሚደነቅ ነው» እና መሰል በአብዛኛዎቹ ሰዎች ዘንድ የሚደመጡ አባባሎች በቀላሉ ለሽርክ እንደሚዳርጉ መናገራቸው ተመልክቷል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ለአላህ ፀጋዎች እውቅና የመስጠትና አንድን የአላህ ፀጋ የመካድ ትርጉም::

2. በአብዛኛዎቹ ሰዎች ምላስ ዘወትር ሲነገር የሚደመጥ ነው::

3. እንዲህ ዓይነት አባባሎች የአላህን ፀጋ ከመካድ መቆጠራቸው::

4. በአንድ ሰው ልቦና ውስጥ ሁለት ፍፁም ተቃራኒ የሆኑ ነገሮች በአንድ ላይ ተስማምተው መኖር አይችሉም::

# ምዕራፍ አርባ ሁለት
## ለአላህ ባላንጣዎችን ስለማበጀት

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿فَلَا تَجْعَلُوا لِلَّهِ أَندَادًا وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ﴾

*«እናንተም (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትሆኑ ለአላህ ባላንጣዎችን አታድርጉ::»(አል-በቀራህ:22)*

ኢብን ዓብባስ ይህን «አያ» በማስመልከት ሲናገሩ:-

«الأَندَادُ هُوَ الشِّرْكُ، أَخْفَى مِنْ دَبِيبِ النَّمْلِ عَلى صَفاةٍ سَوْدَاء فِي ظُلمَةِ الليْلِ، وهُوَ أَنْ تَقُولَ: واللهِ وَحَيَاتِكَ يَا فُلانَ وحَيَاتِي، وتَقُولَ: لَولاَ كُلَيْبَةُ هَذَا لأَتَانَا اللصُوصُ، ولَولا البطّ فِي الَّدارِ لأَتَى اللصُوصُ، وقَوْلِ الرَّجُلِ لِصَاحِبهِ: مَا شَاءَ الله وَشِئْتَ، وقَوْلِ الرَّجُل: لَولاَ الله وفُلاَنٌ لاَ تَجْعَل فيهَا فُلاناً، هَذَا كلُّهُ به شِرْكٌ».

«ባላንጣ ሽርክ ነው:: በድቅድቅ ጨለማ ከጥቁር ድንጋይ ላይ የምትጓዝ ጥቁር ጉንዳን ከምታሰማው ኮቴ ይበልጥ የተደበቀ ሽርክ:: በቀላሉ ሽርክ ላይ ልትወድቅ ትችላለህ:: ለምሳሌ ለወንድምህ፥ በአላህና በአንተ ህይወት ወይም በህይወቴ ፥ ማለትህ ሽርክ ነው :: ይህ ውሻ ወይም ይህ ዳክዬ ባይኖር ሌባ ዘርፎን ነበር ማለትህም ሽርክ ነው:: አንድ ሰው ለባልደረባው በአላህና በአንተ ፍላጎት ወይም አላህና እገሌ ባይኖሩ ማለቱ እና መሰል አባባሎች ሽርክ ናቸው::» (ኢብን አቡ ሐቲም ዘግበውታል::)

ዑመር ኢብን አል ኸጧብ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«مَنْ حَلَفَ بِغَيْرِ الله فَقَدْ كَفَرَ أَوْ أَشْرَكَ».

«ከአላህ ሌላ ባሉ አካላት የማለ ክህደት ወይም ሽርክ ፈፅሟል::» (ቲርሚዚ ዘግበውታል::)

ኢብን መስዑድ እንዲህ ሲናገሩ ተደምጠዋል:-

«لأَنْ أَحْلِفَ بالله كَاذِباً أَحَبُّ إِليَّ مِنْ أَنْ أَحْلِفَ بِغَيْرِهِ صَادِقاً».

«ከአላህ ውጭ ባሉ አካላት በእውነት ከምምል በአላህ በሐሰት መማልን እመርጣለሁ::»

ሁዘይፈህ እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ):-

«لا تَقُولُوا مَا شَاءَ اللهُ وشَاءَ فُلانٌ ولكِنْ قُولُوا مَا شَاءَ اللهُ ثُمَّ شَاءَ فُلانٌ».

«በአላህና በእገሌ በጐ ፈቅድ አትበሉ:: በአላህ በዚያም በእገሌ በጐ ፈቃድ፣ ብቻ በሉ::» ብለዋል:: (አቡዳውድ ሶሒሕ በሆነ ሰነድ ዘግበውታል) «በአላህና በአንተ እጠበቃለሁ» የሚለውን አባባል አጥብቀው ይጠሉ እንደነበር ተዘግቧል:: ኢብራሂም ኑኸዕይ «በአላህና ከዚያም በአንተ» ማለትን ግን ፈቅደዋል:: «አላህ ከዚያም እገሌ ባይኖር» በሉ እንጂ «አላህና እገሌ ባይኖሩ፣ አትበሉ» ሲሉም ተናግረዋል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል በቀራህ 22» ትርጉም::
2. ሶሃቦች ታላላቅ ሽርኮችን የሚያስጠነቅቁ የቁርአን አንቀፆች መለስተኛዎቹንም እንደሚያካትቱ ይረዱ ነበር::
3. ከአላህ ውጭ ባለ ሌላ አካል መማል ሽርክ ነው::
4. ከአላህ ውጭ ባሉ አካላት በእውነት መማል፣ በአላህ በሐሰት ከመማል የበለጠ ወንጀል ነው::
5. ከላይ ከተጠቀሱት አባባሎች ውስጥ በ«ወ» እና በ«ሱምመ» መካከል ያለው ልዩነት::

## ምዕራፍ አርባ ሦስት

## <u>በአላህ ተምሎ የተነገረውን ያልተቀበለ</u>

ኢብን ዑመር እንደስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ):-

«لاَ تَحْلِفُوا بِآبَائِكُمْ مَنْ حَلَفَ بِاللهِ فَلْيَصْدُقْ وَمَنْ حُلِفَ لَهُ بِاللهِ فَلْيَرْضَ، وَمَنْ لَمْ يَرْضَ فَلَيْسَ مِنَ اللهِ».

«በአባቶቻችሁ አትማሉ፤ በአላህ የማለ እውነትን ብቻ ይናገር፤ በአላህ የተማለለትም ሰው የተነገረውን አምኖ ይቀበል፤ ያልተቀበለ ከኛ ውጪ ነው» ብለዋል:: (ኢብን ማጃህ ሐሰን በሆነ ሰነድ ዘግበውታል)

### <u>ጠቃሚ ነጥቦች</u>

1. በአያት ቅድመ አያቶች መማል የተወገዘ ነው::
2. አንዳች ነገር በአላህ ተምሎ የተነገረው ሰው የተነገረውን አምኖ መቀበል ይገባዋል::
3. አምኖ ያልተቀበለ በጥብቅ ተወግዟል::

# ምዕራፍ አርባ አራት
## «በአላህና በአንተ በጎ ፈቃድ» በማለት ስለመናገር

ቁተይለህ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«أنَّ يَهُودِيًّا أتَى النَّبيَّ ﷺ فقَالَ: إنّكُمْ تُشْرِكُونَ: تَقُولونَ مَا شَاءَ الله وَشِئْتَ، وتَقُولونَ والكَعْبَةِ، فأمَرَهُمُ النَّبيُّ ﷺ إذَا أرَادُوا أنْ يَحْلِفُوا أنْ يَقُولُوا: ورَبِّ الكَعْبَةِ وأنْ يَقُولُوا: مَا شاءَ الله ثُمَّ شِئْتَ».

አንድ የሁዳ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ በመምጣት :- «እናንተ የሽርክ ተግባር ትፈፅማላችሁ፣ በአላህና በአንተ በጎ ፈቃድ+ ትላላችሁ፣ በካዕባም ትምላላችሁ» አላቸው:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) + ተከታዮቻቸው መማል ሲፈልጉ «ወረቢል ካዕባ» (በካዕባ ጌታ) በማለት እንዲምሉ፣ «በአላህ ከዚያም በአንተ በጎ ፈቃድ» እንዲሉም አዘዙ:: (ነሳኢ ዘግበውታል፣ ሶሒሕ ብለውታልም)

ነሳኢ ኢብን ዓባስን ጠቅሰው ተከታዩን ዘገባ አስፍረዋል:-

«أنَّ رَجُلاً قَالَ للنَّبيِّ ﷺ مَا شَاءَ الله وشِئْتَ، فقَالَ أجَعَلْتَنِي لله نِدًّا؟ مَا شَاءَ الله وَحْدَهُ».

አንድ ሰው ለነቢዩ:- «በአላህ እና በአንተ በጎ ፈቃድ» አላቸው:: «ለአላህ ባላንጣ (ኒድ) ታደርገኛለህ? በአላህ በጎ ፈቃድ ብቻ በል» አሉት::

የአዒሻ ወንድም ጡፈይል እንዲህ ሲሉ ማስተላለፋቸውን ኢብኑ ማጃህ ዘግበዋል:-

«رأَيْتُ فِيمَا يَرَى النَّائِمُ كأنِّي أتَيْتُ عَلى نَفَرٍ مِنَ اليَهُودِ قُلْتُ: إنَّكُمْ لأنْتُمُ القَوْمُ لَوْلا أنَّكُمْ تَقُولُونَ عُزَيْرٌ ابنُ الله، قَالُوا وإنَّكُمْ لأنْتُمُ القَوْمُ لَولا أنَّكُمْ تَقُولونَ مَا شَاءَ الله وَشَاءَ مُحَمَّدٌ. ثُمَّ مَرَرْتُ بِنَفَرٍ مِنَ النَّصَارَى فقُلْتُ إنَّكُمْ لأنْتُمُ القَوْمُ لَولا أنَّكُمْ تَقُولُونَ المَسِيحُ ابنُ الله قَالُوا وإنَّكُمْ لأنْتُمُ القَوْمُ لَولا أنَّكُمْ تَقُولُونَ مَا شَاء الله وشَاء مُحَمَّدٌ. فَلَمَّا أصْبَحتُ أخْبَرْتُ بِهَا مَنْ

أخبَرْتُ ثُمَّ أتَيْتُ النَّبيَّ ﷺ فأخْبَرْتُهُ قَالَ هَلْ أخبَرْتَ بِهَا أحداً؟ قُلْتُ نَعَمْ، قَالَ فَحَمِدَ الله وأثْنَى عَلَيْه ثُمَّ قال: أمَّا بَعْدُ: فإنَّ طُفَيلاً رأى رُؤْياً أخبَرَ بِهَا مَنْ أخبَرَ مِنْكُم وإنَّكُمْ قُلْتُم كَلِمَةً كَانَ يَمنَعُنِي كَذَا وكَذَا أنْ أنْهَاكُمْ عَنْها فَلا تَقُولُوا: مَا شَاء الله وشَاءَ مُحمَّدٌ ولكِنْ قُولُوا: مَا شَاء الله وَحْدَهُ».

በህልሜ ወደ አንድ የየሁዶች ስብስብ የሄድኩ ይመስለኛል:: «ኡዘይር የአላህ ልጅ ነው፥ የማትሉ ቢሆን ኖሮ የአላህ ህዝቦች ነበራችሁ::» አልኳቸው:: «በአላህና በሙሐመድ በጎ ፈቃድ፥ የማትሉ ቢሆን ኖሮ እናንተም የአላህ ህዝቦች ነበራችሁ» አሉኝ:: ከዚያም በአንድ የክርስቲያኖች ስብስብ አለፍኩ:: «እየሱስ የአላህ ልጅ ነው፥ የሚል እምነት ባይኖራችሁ ኖሮ የአላህ ህዝቦች ነበራችሁ» አልኳቸው:: «በአላህና በሙሐመድ በጐ ፈቃድ፥ የማትሉ ቢሆን ኖሮ እናንተም የአላህ ህዝቦች ነበራችሁ» አሉኝ:: ሲነጋ በህልሜ ያየሁትን ላገኘኋቸው ሰዎች አጫወትኩ:: ከዚያም ከመልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ በመሄድ ይህንኑ ነገርኳቸው:: «ለሰዎች አውርተሃልን?» አሉኝ:: «አዎ» አልኳቸው:: ለአላህ ምስጋናና ውዳሴ አቀረቡ:: ከዚያም:- «ጡፈይል አንድ ህልም አይቷል:: ከመካከላችሁ ለተወሰኑት መናገሩንም አጫውቶኛል:: የምትሏቸው አባባሎች ነበሩ:: እንዳልከለክላችሁ ይህ፣ ይህ ሁኔታ ይዞኝ ነበር:: በአላህና በሙሐመድ በጎ ፈቃድ፥ አትበሉ:: በአላህ በጎ ፈቃድና ፍላጎት ብቻ በሉ» አሉ::

## <u>ጠቃሚ ነጥቦች</u>

1. የሁዳዎች መለስተኛውን ሽርክ ማወቃቸው::

2. የሰዎች የግንዛቤ ችሎት በግላዊ ስሜታቸው ሊታፈን ይችላል::

3. «ለአላህ ባላንጣ አደረከኝን?» የሚለው ነቢያዊ ቃል ከፍተኛ ትኩረትን ይሻል:: «የፍጡራን ሁሉ ፈርጥ ሆይ! ከርስዎ ውጭ ሌላ መጠጊያ የለኝም» የሚለው የአንድ ገጣሚ አባባል ምን ያህል የተወገዘ ነው!

4. ይህ ከትልቁ ሽርክ የሚካተት አይደለም:: «እንዳልከለክላችሁ ይህ፣ ይህ ሁኔታ ይዞኝ ነበር» የሚለው የመልዕክተኛው ቃል ይህንኑ ያመለክታል::

5. ትክክለኛ ህልም የወህይ (ረዕይ) አንድ ክፍል ነው::

6. ህልም፣ አንዳንድ የሸሪዓው አሕካሞች እንዲደነገጉ ምክንያት ሆኗል::

## ምዕራፍ አርባ አምስት
## ጊዜን መራገም አላህን ማወክ ነው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَقَالُوا مَا هِيَ إِلَّا حَيَاتُنَا الدُّنْيَا نَمُوتُ وَنَحْيَا وَمَا يُهْلِكُنَا إِلَّا الدَّهْرُ ۚ وَمَا لَهُم بِذَٰلِكَ مِنْ عِلْمٍ ۖ إِنْ هُمْ إِلَّا يَظُنُّونَ﴾

*«እርሷም (ህይወት) የቅርቢቱ ህይወታችን እንጅ ሌላ አይደለችም:: እንሞታለን፤ ህያውም እንሆናለን:: ከጊዜ ማለፍ በስተቀር ሌላ አያጠፉንም፥ አሉ :: ለነርሱ በዚህ በማለት ምንም ዕውቀት የላቸውም:: እነርሱ የሚጠራጠሩ እንጅ ሌላ አይደሉም::» (አል-ጃሲያ :24)*

ቡኻሪና ሙስሊም አቡ ሁረይራን ጠቅሰው እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«قالَ الله تَعَالى: يُؤْذِيني ابنُ آدَمَ يَسُبُّ الدَّهْرَ وأنَا الدَّهْرُ أُقَلِّبُ اللَيْلَ والنَّهارَ».

«አላህ፥ የሰው ልጅ ያውከኛል:: ጊዜን ይሰድባል:: ጊዜ እኔው ነኝ:: ሌሊት ቀኑን፥ ቀን ደግሞ ሌሊቱን ተከትለው እንዲመጡ አደርጋለሁ፥ ብሏል::»

በሌላ ዘገባ ደግሞ :-

«لا تَسُبُّوا الدَّهْرَ فَإِنَّ الله هُوَ الدَّهْرُ».

«ጊዜን አትሳደቡ፤ ጊዜ አላህ ራሱ ነው»
የሚል ተወስቷል::

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. ጊዜን መሳደብ የተወገዘ ነው::
2. አላህን እንደማወክ ይቆጠራል::
3. «ጊዜ አላህ ራሱ ነው» የሚለው አገላለፅ ትኩረት ይሻል::
4. ይህ ሐጢአት አስበውት ብቻ ሳይሆን ሳያስቡትም ሊከሰት የሚችል ነው::

## ምዕራፍ አርባ ስድስት
## «የዳኞች ሁሉ የበላይ ዳኛ» በሚሉና መሰል ስያሜዎች መጠራት

ቡኻሪ እንደዘገቡት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን መናገራቸውን አቡ ሁረይራ (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«إِنَّ أَخْنَعَ اسم عِنْدَ الله رَجُلٌ تَسَمَّى مَلِكَ الأَمْلاكِ لاَ مَالِكَ إِلاَّ الله».

«ከአላህ ዘንድ እጅግ ርካሽ ♦ የዓለማት ንጉሥ♦ በሚል ስያሜ የሚጠራ ነው:: ከአላህ ሌላ የዓለማት የበላይ ገዥና ንጉሥ የለም::»

ሱፍያን እንደሚሉት «ሻሃን ሻህ» ተብሎ መሰየምም እንዲሁ የተወገዘ ነው:: በሌላ ዘገባ እንደተወሳው:-

«أَغْيَظُ رَجُلٍ عَلى الله يَوْمَ القِيامَةِ وأَخْبَثُهُ».

«የቂያማ ዕለት ከአላህ ዘንድ እጅግ የተጠላና የተናቀ ሰው የዓለማት ንጉሥ በሚል ስያሜ የሚጠራ ነው::»

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. «የንጉሦች ሁሉ ንጉሥ» በሚል ስያሜ መጠራት የተከለከለ ነው::

2. ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸው ሌሎች የማዕረግ ስሞችም የተወገዙ ናቸው::

3. ለእንዲህ ዓይነት ጥቃቅን ጉዳዮች አፅንኦት መስጠቱን ልብ ልንል ያሻል:: ሰዎች ስያሜውን የሚጠቀሙት ለተጠሪዎች መለኮታዊ ማዕረግ ለመቸር ባይሆንም::

4. ልዕልናና ክብር የሚገባው አላህ ብቻ ነው::

## ምዕራፍ አርባ ሰባት
## የአላህን ስሞች ስለ ማላቅና ለዚሁ ሲባል ስምን ስለመቀየር

አቡ ሹረይህ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«أنَّه كَانَ يُكَنَّى أَبَا الحَكَم فقَالَ لَهُ النَّبيُّ ﷺ إنَّ الله هُوَ الحَكَمُ وإلَيْهِ الحُكْمُ فقَالَ إنَّ قَوْمِي إذَا اخْتَلَفُوا فِي شَيءٍ أتَوْنِي فَحَكَمْتُ بَيْنَهُمْ فَرضِيَ كِلاَ الفَرِيقَينِ، فقَال مَا أحْسَنَ هَذا. فَمَالَكَ مِنَ الوَلَدِ؟ قَالَ شُرَيْحٌ ومُسْلِمٌ وعَبْدُالله: قال فَمَنْ أكْبَرُهُم ؟ قُلْتُ: شُرَيْحٌ، قَالَ: فأنْتَ أبُو شُرَيْح».

አቡልሐኪም በሚል ስያሜ ነበር የምታወቀው:: ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ):- «ሐኪም አላህ ብቻ ነው፤ ሑክም (ብይን) የርሱ ብቻ እንጅ የሌላ የማንም መብት አይደለም::» አሉ:: «ህዝቦቼ በአንዳች ነገር ሲወዛገቡ ከኔ ዘንድ ይቀርባሉ:: ብይን እሰጣቸዋለሁ:: ሁሉም ወገኖች በምሰጠው ብይን ይስማማሉ::» አልኳቸው:: «ይህ ውብ ነገር ነው:: ልጆች አሉህ?» ሲሉ ጠየቁኝ:: «አዎ፣ ሦስት ልጆች አሉኝ፤ ሹሪህ፣ ሙስሊምና አብደላህ ይባላሉ::» አልኳቸው:: «ከሦስቱ ትልቁ የትኛው ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ:: «ሹሪህ» አልኳቸው:: «ከአሁን በኋላ አቡ ሹረይህ በሚል ስያሜ ነው የምትጠራው» አሉኝ:: (አቡዳውድና ሌሎችም)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአላህን ስሞችና ባህሪያት ማላቅ:: በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ክብራቸውን አለማጉደፍ::
2. ለዚሁ ሲባል ስምን እንኳ መቀየር::
3. የበኩርን ልጅ ለመጠሪያነት (ኩንያ) መጠቀም::

## ምዕራፍ አርባ ስምንት
## በአላህ፣ በመልዕክተኛው ወይም በቁርአን መቀለድ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَلَئِن سَأَلْتَهُمْ لَيَقُولُنَّ إِنَّمَا كُنَّا نَخُوضُ وَنَلْعَبُ ۚ قُلْ أَبِاللَّهِ وَآيَاتِهِ وَرَسُولِهِ كُنتُمْ تَسْتَهْزِئُونَ ﴾

*«በእርግጥ ብትጠይቃቸው እኛ የምንዘባርቅና የምንጫወት ብቻ ነበርን ይላሉ፤ በአላህና በአንቀፆቹ፣ በመልዕክተኛውም ታላግጡ ነበራችሁን?» (አል-ተውባህ :65)*

ተከታዩ ዘገባ ኢብን ዑመር፣ ሙሐመድ ኢብን ካዕብ፣ ዘይድ ኢብን አስለምና ቀታዳ በጋራ ያስተላለፉት ነው:-

«أنَّهُ قَالَ رَجُلٌ في غَزْوَةِ تَبُوكٍ مَا رَأَيْنَا مِثْلَ قُرَّائِنَا هؤُلاءِ أرْغَبَ بُطُوناً ولاَ أكْذَبَ ألْسُناً ولا أجْبَنَ عِنْدَ اللقَاءِ. يَعْنِي رَسُولَ الله ﷺ وأصْحَابَهُ القُرَّاءِ، فَقَالَ لهُ عَوْفُ بنُ مَالِكٍ كَذَبْتَ ولكِنَّكَ مُنَافِقٌ لأُخْبِرَنَّ رَسُولَ الله ﷺ فَذَهَبَ عَوْفٌ إلى رَسُولِ الله ﷺ لِيُخْبِرَهُ فَوَجَدَ القُرآنَ قَدْ سَبَقَهُ. فَجَاءَ ذَلِكَ الرَّجُلُ إلى رَسُولِ الله ﷺ وقَدِ ارتَحَلَ ورَكِبَ نَاقَتَهُ فَقَالَ يَا رَسُولَ الله إنَّمَا كُنَّا نَخُوضُ ونَتَحَدَّثُ حَدِيثَ الرَّكْبِ نَقْطَعُ بهِ عَنَّا الطَّرِيقَ. قال ابن عمر: كأنِّي أنْظُرُ إلَيْهِ مُتَعَلِّقاً بِنَسْعَةِ نَاقَةِ رَسُولِ الله ﷺ وأنَّ الحِجَارَةَ تَنْكُبُ رِجْلَيْهِ وهُوَ يَقُولُ إنَّمَا كُنَّا نَخُوضُ ونَلْعَبُ. فَيَقُولُ لَهُ رَسُولُ الله ﷺ: ﴿أبالله وآيَاتِهِ ورَسُولِهِ كُنْتُمْ تَسْتَهْزِؤنَ. لاَ تَعتَذِرُوا قَد كَفَرتُم بَعدَ إيمَانِكُم﴾ . مَا يَلْتَفِتُ إلَيْهِ ومَا يَزِيدُهُ عَلَيْهِ

የተቡክ ዘመቻ ዕለት ነበር:: አንድ ሰው :- «ከነኝህ (ከነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እና ከሰሃቦቻቸው) የበለጠ ሆዳም፣ ውሸታምና በውጊያ ወቅት ፈሪ አይተን አናውቅም» አለ:: አውፍ ኢብን ማሊክ:- «ዋሸህ! ሙናፊቅ ነህ:: ያልከውን ለመልዕክተኛው እነግራለሁ»

አለውና ሄደ- ያደመጠውን ሊነግራቸው:: ቁርአን ቀድሞት አገኘው:: ይህን የተናገረው ሰው ከመልዕክተኛው ዘንድ መጣ:: ከግመላቸው ላይ ወጥተው ጉዞ ጀምረዋል:: «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የመንገድ መቁረጫ ወሬ ነው፤እየቀለድንና እየተጫወትን ነበር» አላቸው:: የመልዕክተኛው ግመል አንገት የታሰረበትን ገመድ ይዞ፣ እግሩ ከመንገድ ላይ ድንጋዮች ጋር እየተላተመ በሩጫ ሲከተላቸው ይታየኛል::

«እየተጫወትንና እየተቀላለድን ነበር» ሲላቸው በድጋሜ፤ «በአላህ፣ በአንቀጾቹና በመልዕክተኛው ትቀልዱላችሁን? ምክንያታችሁን አትደርድሩ:: ከእምነታችሁ በኋላ ክዳችኋል» አሉት:: ዞረው አልተመለከቱትም:: ሌላ ያሉት ነገርም አልነበረም::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. እጅግ ጠቃሚ ነጥብ ነው:: በእንዲህ ዓይነቶቹ ጉዳዮች የቀለደ ካፊር ነው::

2. የአንቀፁ ትክክለኛ ትርጓሜ ይኸው ነው፤ ድርጊቱን የፈፀመው ሰው ማንም ይሁን ማን::

3. ገንቢ አስተያየት (ነሲሐ) አፍራሽ ከሆነ ትችትና ሐሜት ይለያል::

4. አላህ የሚወደው ይቅር ባይነት በአላህ ጠላቶች ላይ መኖር ካለበት ጥላቻ ተለይቶ ሊታወቅ ይገባል::

5. የተጠቀሱት ምክንያቶች ተቀባይነት የላቸውም:: ውድቅ ሊደረጉ የሚገባቸው ሰበቦች አሉ::

## ምዕራፍ አርባ ዘጠኝ
## «ይህን ገንዘብ ያገኘሁት በጉልበቴና በእውቀቴ ነው» ማለት ከተውሂድ ጋር ይቃረናል

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَلَئِنْ أَذَقْنَٰهُ رَحْمَةً مِّنَّا مِنۢ بَعْدِ ضَرَّآءَ مَسَّتْهُ لَيَقُولَنَّ هَٰذَا لِى وَمَآ أَظُنُّ ٱلسَّاعَةَ قَآئِمَةً وَلَئِن رُّجِعْتُ إِلَىٰ رَبِّىٓ إِنَّ لِى عِندَهُۥ لَلْحُسْنَىٰ ۚ فَلَنُنَبِّئَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِمَا عَمِلُوا۟ وَلَنُذِيقَنَّهُم مِّنْ عَذَابٍ غَلِيظٍ ﴾

*«ካገኘችውም መከራ በኋላ ከኛ የሆነን እዝነት ብናቀምሰው ይህ (በኔ ለሥራዬ የተገባኝ) ነው:: ሰዓቲቱም መጭ ናት ብዬ አላስብም:: ወደ ጌታዬም ብመለስ ለኔ ከርሱ ዘንድ መልካሚቱ ገነት በእርግጥ አለችኝ፥ ይላል፤ እነዚያንም የካዱትን ሥራዎቻቸውን በእርግጥ እንነግራቸዋለን:: ከብርቱውም ስቃይ በእርግጥ እናቀምሳቸዋለን::» (አል-ሰጅዳህ:50)*

ሙጃሂድ ይህን አንቀጽ ሲያብራሩ:- «መልካም ነገር ያገኘሁት በጥረቴ ነው» ማለት እንደሆነ ተናግረዋል::

ኢብን ዓብባስ ደግሞ:- «መልካሙ ነገር የተገኘው ከአላህ ሳይሆን ከኔ ነው::» ሲሉ አብራርተውታል::

﴿ قَالَ إِنَّمَآ أُوتِيتُهُۥ عَلَىٰ عِلْمٍ عِندِىٓ ۚ ﴾

*«ሀብቱን የተሰጠሁት ከኔ ዘንድ ባለው እውቀት ብቻ ነው» (አል-ቀሰስ: 78)*

የሚለውን የቁርአን አንቀፅ አስመልክቶ ቀታዳ ሲናገሩ:- «በእውቀቴ፣ በጥረቴና ልፋቴ» ብለዋል:: ሌሎች ምሁራን ደግሞ:- «ከአላህ በሆነ እውቀት:: እኔ ለዚያ እውቀት የተገባሁ ነኝ» ብለውታል:: ይህ፥ «ባለኝ ክብር የተሰጠሁት ነው» ከሚለው የቀታዳህ ትርጉም መንፈስ ጋር ይጣጣማል::

አቡ ሁረይራ (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«إِنَّ ثَلاثَةً مِنْ بَنِي إِسَرائيلَ أَبْرَصَ وَأَقْرَعَ وأعْمَى فأرادَ الله أنْ

يَبْتَلِيَهُمْ فَبَعَثَ إِلَيهمْ مَلَكاً فَأَتَى الأَبْرَصَ فَقَالَ: أَيُّ شَيءٍ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ لَوْنٌ حَسَنٌ وجِلدٌ حَسَنٌ ويَذهَبُ عَنِّي الذِي قَدْ قَذِرَنِي النَّاسُ بِهِ قَالَ فَمَسَحَهُ فَذَهَبَ عَنْهُ قَذَرُهُ فأُعْطِيَ لَوناً حَسَناً وجِلْداً حَسَناً. قَالَ فأيُّ المَالِ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ الإِبلَ أَوِ البَقَرَ شكّ إسحاق. فأُعْطِيَ نَاقَةً عُشَرَاءَ، وقَالَ بَارَكَ الله لَكَ فِيهَا. قَالَ فأَتَى الأَقْرَعَ فَقَالَ: فأيُّ شَيءٍ أَحَبُّ إِلَيْكَ، قَالَ: شَعْرٌ حَسَنٌ ويَذْهَبَ عَنِّي الذِي قَدْ قَذِرَنِي النَّاسُ بِهِ فَمَسَحَهُ فَذَهَبَ عَنْهُ وأُعْطِيَ شَعْراً حَسَناً. فَقَالَ أيُّ المَالِ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ البَقَرَ أوِ الإِبلَ. فأُعْطِيَ بَقَرَةً حَامِلاً قَالَ بَارَكَ الله لَكَ فيهَا. فأَتَى الأَعْمَى فقَالَ: أيُّ شَيءٍ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ: أَنْ يَرُدَّ الله إِلَيَّ بَصَرِي فأُبْصِرَ بِهِ النَّاسَ فَمَسَحَهُ فَرَدَّ الله إِلَيْهِ بَصَرَهُ. قَالَ أيُّ المَالِ أَحَبُّ إِلَيْكَ؟ قَالَ الغَنَمَ. فأُعْطِيَ شَاةً وَالِداً. فَأُنْتِجَ هذَانِ وَوُلِّدَ هذَا فَكَانَ لِهذَا وَادٍ مِنَ الإِبِلِ ولِهَذَا وَادٍ مِنَ البَقَرِ ولِهَذَا وَادٍ مِنَ الغَنَمِ. قَالَ: ثُمَّ إِنَّه أَتَى الأَبْرَصَ في صُورَتِهِ وهَيئَتِهِ فَقَالَ: رَجُلٌ مِسْكينٌ قَدْ انْقَطَعَت بيَ الحِبَالُ في سَفَرِي فَلا بَلاَغَ لِيَ اليَوْمَ إلاَّ بالله ثُمَّ بِكَ. أسأَلُكَ بالذِي أَعْطَاكَ اللَّوْنَ الحَسَنَ والجِلْدَ الحَسَنَ والمَالَ بَعِيراً أَتَبَلَّغُ بهِ فِي سَفَرِي. فَقَالَ الحُقُوقُ كثِيرةٌ. فَقَالَ كأَنِّي أعْرِفُكَ أَلَمْ تَكُنْ أَبْرَصَ يَقْذَرُكَ النَّاسُ، فَقِيراً فأعْطَاكَ الله عَزَّ وجَلَّ المَالَ؟ فَقَالَ: إِنَّمَا وَرِثْتُ هذَا المَالَ كَابِراً عَنْ كَابِرٍ. فَقَال: إنْ كُنْتَ كَاذِباً فَصَيَّرَكَ الله إلى مَا كُنْتَ. وأَتَى الأَقْرَعَ فِي صُورَتِهِ فَقَالَ له مِثْلَ مَا قَالَ لِهَذا. ورَدَّ عَلَيْهِ مَا رَدَّ

عليهِ هذَا. فقَالَ: إنْ كُنتَ كَاذِباً فصَيَّرَكَ الله إلى مَا كُنتَ. قَالَ: وأتَى الأعْمَى فِي صُورتِهِ فقَال: رَجُلٌ مِسْكينٌ وابْنُ سَبيلٍ، قَدِ انْقَطَعَتْ بيَ الحِبَالُ فِي سَفَري فَلاَ بَلاَغَ ليَ اليَوْمَ إلاَّ بالله ثُمَّ بِكَ أَسْأَلُكَ بالذِي رَدَّ عَلَيْكَ بَصَرَكَ شَاةً أتَبَلَّغُ بهَا في سَفَري. فقَال: قَدْ كُنتُ أعْمَى فَرَدَّ الله إليَّ بَصَرِي. فَخُذْ مَا شِئْتَ وَدعْ مَا شِئْتَ. فوَالله لا أجْهَدُكَ اليوْمَ بشيءٍ أخَذْتَهُ لله. فقَالَ: أمْسِكْ مَالَكَ فإنَّمَا أبْتُلِيتُمْ فقَد رَضِيَ الله عَنْكَ وَسخَطَ عَلى صَاحِبَيْكَ».

«ከበኒ እስራኤሎች መካከል ሦስት ሰዎች- አንደኛው ለምፃም፣ ሌላኛው በራ፣ ሦስተኛው ደግሞ እውር አላህ ሊፈትናቸው ፈለገ:: መላኢካ ላከባቸው:: ለምፅ ያለበትን ሰው መጣና:- «በጣም የምትወደው ነገር ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው:: «መልካም መልክና መልካም ቆዳ:: ሰዎች እኔን እንዲጠየፉኝ ምክንያት የሆነው በሽታዬም እንዲወገድልኝ» ሲል መለሰ:: አበሰው- መላኢካው:: አስፀያፊው ሁኔታም ተወገደለት:: መልካም መልክ ተሰጠ:: «ከገንዘብ የትኛው ነው ካንተ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ» በማለት ጠየቀው:: «ግመል ወይም ላም» መለሰለት:: እርጉዝ ግመል ተሰጠው:: «አላህ ይባርክልህ» ሲልም መረቀው:: ወደ በራው ሰውዬ በመሄድም:- «እጅግ የምትወደው ነገር ምንድን ነው?» አለው:: «መልካም ፀጉር፣ ሰዎች እንዲፀየፉኝ ምክንያት የሆነው በራዬም እንዲወገድ» አለ:: አበሰው:: በራው ተወገደለት:: ማራኪ ፀጉርም ተሰጠው:: «ከገንዘብ የትኛው ነው ካንተ ዘንድ ይበልጥ ተወዳጅ» ሲል ጠየቀው:: «ላም» አለ:: ያረገዘች ላም ተሰጠው:: «አላህ ይባርክልህ» አለው:: ከእውሩም ዘንድ በመምጣት:- «ይበልጥ የምትወደው ነገር ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው:: «አላህ የዓይኔን ብርሃን መልሶልኝ ሰዎችን መመልከት መቻል» በማለት መለሰለት:: አበሰው:: አላህ የዓይኑን ብርሃን መለሰለት:: «ከገንዘብ የትኛውን ነው ይበልጥ የምትወደው?» ሲልም ጠየቀው:: «ፍየል» አለ:: ወላድ የሆነች ፍየል ተሰጠው:: ሁሉም ተራብቡ፣ ተበራከቱ:: አንደኛው አንድ ሸለቆ ግመል፣ሌላኛው አንድ ሸለቆ ከብት፣ ሦስተኛው ደግሞ የአንድ ሸለቆ ፍየል ባለሀብቶች ሆኑ:: በሌላ ወቅት መላኢካው ድሮ

በነበረው መልክና አኳኋን ሆኖ ለምፃም ወደነበረው ሰው መጣና፡- «ችግር የደረሰብኝ መንገደኛ ነኝ። አላህና አንተ ከምትለግሱኝ ችሮታ በስተቀር ጉዞዬን ለመቀጠል የሚያስችለኝ ስንቅ የለኝም። ለመዳረሻዬ የሚሆነኝ ስንቅ ታቀብለኝ ዘንድ መልካም መልክ፣ መልካም ቆዳና ይህን ሁሉ ግመል በለገሰህ አምላክ ስም እማፀንሃለሁ» አለው። «እያሌ ጉዳዮች አሉብኝ፤ ልረዳህ አልችልም» አለው። «የማውቅህ ይመስለኛል። ሰዎች የሚፀየፉህ ለምፃምና ድሃ አልነበርክም?- አላህ ጥሩ መልክና ቆዳ እንዲሁም ሀብት ለገሰህ» አለው። «ከአያት ቅድመ አያቶቼ የወረስኩት ነው» አለ። «ሐሰት ከተናገርክ (አላህ) ድሮ ወደ ነበርክበት ሁኔታ ይመልስህ» አለው። መላጣ ወደነበረው ሰው በጥንቱ መልክና አኳኋን ሆኖ በመምጣትም ለዚያኛው ያለውን አለው። ይህኛውም ያኛው የሰጠውን ዓይነት ምላሽ መለሰለት። «ሐሰት ከተ ነገርክ ድሮ ወደ ነበርክበት ሁኔታ አላህ ይመልስህ» አለው። በጥንቱ መልክና አኳኋን ሆኖ እውር ከነበረው ሰው ዘንድ መጣና «በጉዞ ላይ እያለሁ ስንቅ የተቋረጠብኝና ችግር የደረሰብኝ መንገደኛ ነኝ። ከአንተና ከአላህ ከማገኘው ችሮታ ውጭ ለመዳረሻዬ የሚሆን ስንቅ የለኝም። ለመዳረሻዬ የሚሆነኝ እንዲት ፍየል ትሰጠኝ ዘንድ የዓይንህን ብርሃን በመለሰለህ አምላክ (ስም) እማፀንሃለሁ» አለው። «እውር ነበርኩ፤ አላህ ዓይኔን መለሰልኝ። ያሻህን ውሰድ። በአላህ ይሁንብኝ! ልዑልና ኃያል ለሆነው አላህ ስል ዛሬ የምትወስደውን ነገር መልስ ብዬ አላስቸግርህም»አለው። «ገንዘብህን ያዝ። እናንተን ለመፈተን ነው የመጣሁት። አላህ በአንተ ረክቶ በሁለቱ ወዳጆችህ ተቆጥቷል» አለ ።» (ቡኻሪና ሙስሊም)

## <u>ጠቃሚ ነጥቦች</u>

1. የአንቀፅ «አል ሰጅዳህ 50» ትርጉም።

2. «ይህ ለኔ (በሥራዬ የተገባኝ) ነው» የሚለው ቁርአናዊ ቃል ትርጉም።

4. ከላይ የተጠቀሰው ታሪክ እጅግ የሚያስገርምና የሚያስደንቅ አስተምህሮትን ይዟል።

## ምዕራፍ ሃምሳ

## ከአላህ ውጭ ያሉ ሃይላትን ማምለክን የሚገልፁ ማናቸውም ዓይነት ስሞች የተወገዙ ናቸው

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿فَلَمَّآ ءَاتَىٰهُمَا صَٰلِحًا جَعَلَا لَهُۥ شُرَكَآءَ فِيمَآ ءَاتَىٰهُمَا ۚ فَتَعَٰلَى ٱللَّهُ عَمَّا يُشْرِكُونَ﴾

*«መልካምን ልጅ በሰጣቸው ጊዜ በሰጣቸው ልጅ ስም ለርሱ ተጋሪዎችን አደረጉለት:: አላህም ከሚያጋሩት ሁሉ ላቀ::» (አል-አዕራፍ:90)*

ኢብን ሐቲም እንደሚሉት:- «ዓብዱል ሙጦሊብ የሚለው ስም ሲቀር ዓብዱ ዓምር፣ ዓብዱ ካዕበህ እና መሰል ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት ባሪያ (ዓብድ) መሆንን የሚገልፀ ማናቸውም ዓይነት ስሞች ውጉዝ እንደሆኑ አጠቃላይ የዑለሞች ስምምነት አለ::» ኢብን ዓባስ ካላይ የተጠቀሰውን የቁርአን አንቀፅ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል:-

«لَمَّا تَغَشَّاهَا آدَمُ حَمَلَت فأتاهَا إبْلِيسُ فقَالَ: إنِّي صَاحِبُكُمَا الذي أخرَجْتُكُمَا مِنَ الجَنَّة لَتُطِيْعَنِي أوْ لأجْعَلَنَّ لَهُ قَرنَي إيلٍ فَيَخْرُجُ مِنْ بَطْنِكِ فَيَشُقُّهُ ولأفعَلَنَّ ولأفعَلَنَّ يُخَوِّفُهُمَا سَمِّيَاهُ عَبْدَ الحَارِثِ فأَبَيَا أنْ يُطِيعَاهُ فَخَرَجَ مَيِّتاً. ثُمَّ حَمَلَتْ فأتَاهُمَا فقَالَ مِثْلَ قَوْلِهِ فأَبَيَا أنْ يُطِيعَاهُ فَخَرَجَ مَيِّتاً. ثُمَّ حَمَلَتْ فأتاهُمَا فذَكَرَ لَهُمَا فأدْرَكَهُمَا حُبَّ الوَلَدِ فَسَمَّيَاهُ عَبْدَ الحَارِثِ فَذلِكَ قَوْلُهُ: ﴿جَعَلا لَهُ شُرَكَاءَ فِيمَا آتاهُمَا﴾».

አደም ከእርሷ (ከሃዋ) ጋር ግንኙነት ፈፀመ:: አረገዘች:: ሸይጧን ቀረባቸውና:- «ከጀነት ለመባረር ምክንያት የሆንኳችሁ እኔ ነኝ:: የማዛችሁን ትፈፅማላችሁ:: ልጃችሁን ዓብዱል ሐሪስ በሚል ስያሜ ጥሩት:: ካለበለዚያ ሁለት ባለ ቅርንጫፍ ቀንዶች እንዲኖሩት አደረጋለሁ:: ሲወለድ ሆድሽን እየተረተረ ይወጣል:: ከዚህ ሌላም ይህን፣ ይህን እፈፅማለሁ::» አላቸው:: ኣልተቀበሉትም:: ልጃቸው ሞቶ ተወለደ:: ለሁለተኛ ጊዜ

አረገዘች:: ሸይጧን በድጋሜ መጣ:: በፊት ያለውን ደገመላቸው:: ሊቀበሉት ፈቃደኛ አልሆኑም:: ልጃቸው ሞቶ ተወለደ፡፡ ለሦስተኛ ጊዜ አረገዘች:: ሸይጧን ቀረባቸው:: ከልጅ ፍቅር የተነሳ ሐሳቡን፥ በመቀበል «ዓብዱል ሐሪሥ» አሉት- ልጃቸውን::

«መልካምን ልጅ በሰጣቸው ጊዜ በሰጣቸው ልጅ ስም ለርሱ ተጋሪዎችን አደረጉ» የሚለው ቁርአናዊ ቃል የሚያመለክተው ይህንን ክስተት ነው:: (ኢብን ሐቲም ዘግበውታል)

ኢብን ሐቲም ሶሒሕ በሆነ ሰነድ እንደዘገቡት ቀታዳ:- «ተጋሪዎችን አደረጉለት፥ የሚለው ቃል የሚያመለክተው መታዘዝን እንጂ ማምለክን አይደለም» ብለዋል::

ኢብን ሐቲም እንደዘገቡት ሙጃሂድ:-

﴿ لَئِنْ ءَاتَيْتَنَا صَٰلِحًا ﴾

«መልካምን ልጅ በሰጠናቸው ጊዜ»

የሚለውን ቁርአናዊ ቃል አስመልክተው ሲናገሩ:- «ልጃችን ምን አልባትም ሰው ላይሆን ይችላል የሚል ስጋት አደረባቸው::» ብለዋል:: ሐሰንን፣ ሰዒድንና ሌሎችንም በመጥቀስ ተመሳሳይ መንፈስ ያለው ዘገባ አስፍረዋል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት ባርነትን የሚገልፁ ስሞች ሁሉ የተወገዙ ናቸው::

2. የአንቀፅ «አል አዕራፍ 190» ትርጉም::

3. ይህ ሽርክ በስያሜ ብቻ የመጣ ነው:: ከአላህ ውጭ ላሉ ኃይላት እውነተኛ ባርነት ታስቦ አይደለም::

4. መልካም ልጆችን ከአላህ መለገስ «ሹክር» የሚያስፈልገው ፀጋ ነው::

5. ሰለፎች በመታዘዝ (ጧዐ) የሚመጣን ሽርክ ከአምልኮ (ዒባዳ) ሽርክ ለይተው ተመልክተውታል::

# ምዕራፍ ሃምሳ አንድ
# አላህ መልካም ስሞችና ባህርያት አሉት

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَلِلَّهِ ٱلْأَسْمَآءُ ٱلْحُسْنَىٰ فَٱدْعُوهُ بِهَا ۖ وَذَرُوا۟ ٱلَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِىٓ أَسْمَٰٓئِهِۦ﴾

*«ለአላህ መልካም ስሞች አሉት፤ (ስትፀልዩ)፤ በርሷም ጥሩት፤ እነዚያንም ስሞቹን የሚያጣምሙትን ተውዋቸው::» (አል-አዕራፍ:180)*

ኢብን አቢ ሐቲም እንዳስተላለፉት ኢብን ዓባስ :- «የሚያጣምሙትን» የሚለውን ቁርአናዊ ቃል «የሚያጋሩትን» ሲሉ ተርጉመውታል:: አልላት እና ዑዝዛ የሚሉት የጣኦታት ስሞች የቃል መሠረት «ኢላህ» እና «ዓዚዝ» የሚሉት የአላህ ስሞች እንደሆኑም ተናግረዋል::

አዕመሽ ደግሞ:- «ስሞቹን የሚያጣምሙ» የሚለውን ሐረግ:- «ከነርሱ ያልሆነውን የሚጨምሩ» ሲሉ እንደተረጎሙት ተመልክቷል::

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ለአላህ መልካም ስሞችን ማፅደቅ::
2. የአላህ ስሞች መልካም መሆናቸው::
3. በአላህ መልካም ስሞች ዱዓ እንድናደርግ ታዘናል::
4. የአላህን ስሞች የሚያጣምሙ መሐይማንን ችላ ማለት ተገቢ ነው::
5. የ«ኢልሃድ» (ማጣመም) ትርጉም::
6. የአላህን ስሞች ያጣመመ በጥብቅ ተወግዟል::

## ምዕራፍ ሃምሳ ሁለት

## ለአላህ ሰላምታ ማቅረብ የተከለከለ ነው

ሶሒሕ አል ቡኻሪ እንደዘገቡት ኢብን መስዑድ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«إذَا كُنَّا معَ النَّبيِّ ﷺ في الصَّلاةِ قُلْنَا السَّلامُ عَلى الله مِنْ عَبَادِهِ السَّلامُ علَى فُلَانٍ وَفُلان فقَالَ النبيُّ ﷺ لاَ تَقُولوا السَّلامُ عَلى الله فَإنَّ الله هُوَ السَّلامُ».

ከነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ጋር በምንሰግድበት ወቅት «ለአላህ ከባሮቹ ሰላምታ፤ ለእገሌ ከእገሌ ሰላምታ» እንል ነበር:: «በአላህ ላይ ሰላምታ ይስፈን፣ አትበሉ:: አላህ ራሱ ሰላም ነው» አሉን- መልዕክተኛው::

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. የሰላም ትርጓሜ::
2. ሰላም ሰላምታ ነው::
3. ለአላህ ተገቢው አይደለም::
4. ምክንያቱ ተገልጿል::
5. አግባብነት ያለውንና የሌለውን ድርጊት ያውቁ ዘንድ ሙስሊሞችን ማስተማር እንደሚገባ::

## ምዕራፍ ሃምሳ ሦስት
## «አላህ ሆይ! ከፈለግክ ምህረትን ለግሰኝ» ማለት የተከለከለ ስለመሆኑ

ሶሒሕ አል-ቡኻሪ አቡ ሁረይራን በመጥቀስ እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«لاَ يَقُلْ أَحَدُكُمْ: اللهُمَّ اغْفِر لي إنْ شِئْتَ اللهُمَّ ارْحَمْنِي إنْ شِئْتَ. لِيَعزم المَسْأَلَةَ فَإنَّ الله لا مُكْرِهَ لَهُ».

«ከእናንተ አንዳችሁ፥አላህ ሆይ! ከፈለግክ ምህረትህን ለግሰኝ፤ ከፈለግክ እዘንልኝ፥ አይበል:: ጥያቄውን በእርግጠኝነት ያቅርብ:: አላህን የሚያስገድደው ኃይል የለም፤» ብለዋል:: ሙስሊም ደግሞ:-

«ولْيَعْزِمِ الرَّغْبَةَ فَإنَّ الله لا يَتَعَاظَمُهُ شَيءٌ أعْطَاهُ».

«ከፍተኛ ጉጉት ይኑረው:: አላህ ምንም ነገር መስጠት አይቸግረውም::»

የሚል ዘግበዋል::

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. በዱዓ ወቅት መጠራጠር የተከለከለ ነው::
2. ምክንያቱ ተብራርቷል::
3. «ጥያቄውን በእርግጠኝነት ያቅርብ» የሚለው አገላለፅ ትኩረት ይሻል::
4. በዱዓ ወቅት ከፍተኛ ጉጉት ያስፈልጋል::
5. የዚህም ምክንያት ተወስቷል::

# ምዕራፍ ሃምሳ ስራት
## «የኔ አገልጋይ» ወይም «ባሪያዬ» ማለት የተከለከለ ስለመሆኑ

ቡኻሪ አቡሁረይራን ጠቅሰው እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«لا يَقُلْ أحَدُكُمْ أطْعِمْ رَبَّكَ وضِيء رَبَّكَ. ولْيَقُلْ سَيِّدِي ومَوْلايَ، ولاَ يَقُلْ أحَدُكُمْ: عَبْدِي وأَمَتِي وَلْيَقُلْ: فَتَاي وَفَتاتِي وغُلاَمِي».

«ከናንተ አንዳችሁ ለአገልጋዩ :- ለጌታህ ምግብ አቅርብ፤ ለጌታህ መብራት አቅርብ፤ አገልጋዬ፤ ባሪያዬ፥ አይበል:: አገልጋዩ፣ አለቃዬም (ሰይዲ)፣ አስተዳዳሪዬ (መውላዬ) ይበል:: አለቃው ደግሞ አገልጋዮቹን፥ አንተ ወጣት ልጅ፣ ቆንጅት፥ በማለት ይጥራ::»

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. አገልጋዬ፣ ባሪያዬ ማለት የተከለከለ ነው::

2. አንድ አገልጋይ አለቃውን «ጌታዬ» በማለት መጥራቱ የተከለከለ ነው:: አለቃውም «ለጌታህ ሦግብ አቅርብ» ማለቱ ተወግዟል::

3. አለቃው አገልጋዮቹን «ወጣት፣ ቆንጅት» በማለት እንዲጠራ ታዟል::

4. አገለጋዩ አለቃውን ማለት የሚገባው «አለቃዬ፣ አስተዳዳሪዬ» እንደሆነ ትምህርት ተሰጥቷል::

5. ማስተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ግልፅ ነው:: የተውሂድ ጉዳይ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል:: በቃላት ደረጃ እንኳ ቢሆን::

# ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት
## በአላህ ስም የጠየቀ ተቀባይነት ሊያገኝ እንደሚገባው

ኢብን ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«مَنْ سَألَ بالله فاعْطُوهُ، ومَنِ اسْتَعَاذَ بالله فأعِيذُوهُ، ومَنْ دَعاكُمْ فأجِيبُوهُ ومَنْ صَنَعَ إلَيْكُمْ مَعْروفاً فَكَافِئُوهُ. فإنْ لَمْ تَجِدُوا مَا تُكَافِئُونَهُ فادعوا لَهُ حتَّى تُرَوا أنَّكُمْ قَدْ كافَأتُمُوهُ».

«በአላህ ስም የጠየቀን ስጡት፤ በአላህ ስም ጥበቃ ለከጀለ ጥበቃችሁን አትንፈጉት:: ጥሪ ላቀረበላችሁም ጥሪውን ተቀበሉ:: መልካም ውለታ ለዋለላችሁ ውለታውን መልሱ:: ውለታውን የምትመልሱበት መንገድ ብታጡ እንኳ ዱዓ አድርጉለት፤ ዱዓችሁ ውለታውን የሚመጥን መሆኑ እስኪሰማችሁ ድረስ::» (አቡ ዳውድና ነሳኢ)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. በአላህ ስም ጥበቃን ለከጀለ ጥበቃን አለመንፈግ::
2. በአላህ ስም ለጠየቀ መስጠት::
3. የሰዎችን ግብዣ (ጥሪ) መቀበል::
4. መልካም ለዋለ ሰው ውለታውን መመለስ::
5. ውለታን ለመመለስ አቅሙ ለሌለው ሰው ዱዓ ራሱ ውለታን መክፈል ነው::
6. «ዱዓችሁ ውለታውን መመጠኑ እስኪሰማችሁ ድረስ» የሚለው ሀረግ ልዩ ትኩረት ያሻል::

# ምዕራፍ ሃምሳ ስድስት
# በአላህ ፊት (ክብር) የሚጠየቀው ጀነት ብቻ ስለመሆኑ

ጃቢር (ረዐ) እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«لا يُسْألُ بِوَجْهِ الله إلاَّ الجَنَّةُ».

«በአላህ ፊት (ወጅህ) ከጀነት ውጭ ሌላ ነገር አይጠየቅም::» (አቡ ዳውድ)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. በአላህ ክብር (ወጅህ) መጠየቅ የሚገባው ነገር እጅግ የላቀ ሊሆን ይገባል::
2. «ፊት» ከአላህ ባህሪያት አንዱ ነው::

# ምዕራፍ ሃምሳ ሰባት

## ቁጭት

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ يَقُولُونَ لَوْ كَانَ لَنَا مِنَ ٱلْأَمْرِ شَيْءٌ مَّا قُتِلْنَا هَٰهُنَا ﴾

*«ከነገሩ ለኛ አንዳች በነበረን ኖሮ እዚህ ባልተገደልን ነበር፣ ይላሉ::» (አል-ዒምራን :154)*

﴿ ٱلَّذِينَ قَالُوا۟ لِإِخْوَٰنِهِمْ وَقَعَدُوا۟ لَوْ أَطَاعُونَا مَا قُتِلُوا۟ ﴾

*«እነዚያ ከትግል የቀሩ ሲሆኑ ለወንድሞቻቸው በታዘዙን ኖሮ ባልተገደሉ ነበር ያሉ ናቸው::»(አል-ዒምራን :168)*

ቡኻሪ እንዳሰፈሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሶዐወ) ተከታዩን መናገራቸውን አቡ ሁረይራ (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«احْرِصْ عَلَى مَا يَنْفَعُكَ واسْتَعِنْ باللهِ ولاَ تَعْجَزَنَّ وإنْ أصَابَكَ شَيءٌ فَلاَ تَقُلْ: لَوْ أنِّي فَعَلْتُ كَذَا وكَذَا لَكَانَ كَذَا وكَذَا ولكِنْ قُلْ: قَدَّر اللهِ ومَا شَاءَ فَعَل، فَإنَّ لَوْ تَفْتَحُ عَمَل الشَّيْطَانَ».

«የሚጠቅምህን ነገር በትጋት ከጅል፤ የአላህን እገዛ ጠይቅ፤ አትስነፍ ፤ አንዳች ነገር ሲያገኝህ፣ ይህን ፈፅሜ ቢሆን ኖሮ ይህ በሆነ ነበር፣ እያልክ አትቆጭ:: ይልቁንም፣ አላህ የወሰነው ሆኗል:: የከጀለው ተፈፅሟል፣ በል :: ቁጭት የሸይጧንን ተግባር ከፋች ናትና::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. አል ዒምራን ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱት ሁለት አንቀጾች ትርጉም::

2. ቁጭት በጥብቅ የተወገዘ ነው::

3. ምክንያቱም ተጠቅሷል:: ለሸይጧን ተግባር በር ከፋች ነው::

4. መልዕክተኛው ችግር በደረሰብን ወቅት ምን ማለት እንደሚገባን አስተምረውናል::

5. ጠቃሚን ነገር በትጋት መፈለግና ለዚህም የአላህን እርዳታ መጠየቅ ተገቢ ነው::

6. የዚህ ተቃራኒ የሆነው ባህሪ (ስንፍና) ተወግዟል::

## ምዕራፍ ሃምሳ ስምንት

## ንፋስን መሳደብ ስለ መከልከሉ

ኡበይ ኢብን ካዕብ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«لا تَسُبُّوا الرِّيحَ فإذَا رَأَيْتُمْ مَا تَكْرَهُونَ فَقُولُوا: اللهُمَّ إنَّا نَسأَلُكَ مِنْ خَيْرِ هذِهِ الرِّيحِ وخَيْرِ مَا فِيهَا وخَيْرِ ما أُمِرَتْ بِهِ. ونَعُوذُ بِكَ مِنْ شَرِّ هذِهِ الرِّيح وشَرِّ ما فِيهَا وشَرِّ ما أُمِرَتْ بِهِ».

«ንፋስን አትሳደቡ፤ የምትጠሉት ነገር ሲገጥማችሁ:- አላህ ሆይ! ከዚህ ንፋስ፣ ካመጣውና ከታዘዘበት መልካም ነገር እንጠይቅሀለን:: ከንፋሱ፣ ከሚያመጣውና ከታዘዘበት መጥፎ ነገር ትጠብቀን ዘንድ እንማፀንሃለን+ በሉ::» (ቲርሚዚ)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. ንፋስን መሳደብ ውግዝ መሆኑ::
2. አንድ ሰው የሚጠላው ነገር ሲገጥመው ማለት የሚገባው ትክክለኛ ነገር::
3. ንፋስ በመለኮታዊ ትዕዛዝ (መመሪያ) ሥር መሆኑ::
4. በመልካምም፣ በመጥፎም ሊታዘዝ እንደሚችል::

# ምዕራፍ ሃምሳ ዘጠኝ
## አላህን በክፉ መጠርጠር ስለመከልከሉ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ يَظُنُّونَ بِٱللَّهِ غَيْرَ ٱلْحَقِّ ظَنَّ ٱلْجَٰهِلِيَّةِ ۖ يَقُولُونَ هَل لَّنَا مِنَ ٱلْأَمْرِ مِن شَىْءٍ ۗ قُلْ إِنَّ ٱلْأَمْرَ كُلَّهُۥ لِلَّهِ ۗ يُخْفُونَ فِىٓ أَنفُسِهِم مَّا لَا يُبْدُونَ لَكَ ۖ يَقُولُونَ لَوْ كَانَ لَنَا مِنَ ٱلْأَمْرِ شَىْءٌ مَّا قُتِلْنَا هَٰهُنَا ۗ قُل لَّوْ كُنتُمْ فِى بُيُوتِكُمْ لَبَرَزَ ٱلَّذِينَ كُتِبَ عَلَيْهِمُ ٱلْقَتْلُ إِلَىٰ مَضَاجِعِهِمْ ۖ وَلِيَبْتَلِىَ ٱللَّهُ مَا فِى صُدُورِكُمْ وَلِيُمَحِّصَ مَا فِى قُلُوبِكُمْ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴾

*«ከዚያም ከጭንቅ በኋላ ፀጥታን፣ ከእናንተ ከፊሎችን የሚሸፍንን እንቅልፍ፣ በእናንተ ላይ አወረደ፣ ከፊሎቹን ነፍሶቻቸው በእርግጥ አሳሰቧቸው:: እውነት ያልሆነን የመሐይምነት መጠራጠር በአላህ ላይ ይጠራጠራሉ:: ከነገሩ ለኛ ምንም የለንም ይላሉ:: ነገሩ ሁሉ ለአላህ ነው፣ በላቸው:: ለእናንተ የማይገለጹትን በነፍሶቻቸው ውስጥ ይደብቃሉ፣ ከነገሩ ለኛ አንዳች በነበረን ኖሮ፣ እዚህ ባልተገደልን ነበር፣ ይላሉ:: በቤታችሁ ውስጥ በኾናችሁም ኖሮ እነዚያ በነርሱ ላይ መገደል የተፃፈባቸው ወደ መውደቂያቸው በወጡ ነበር በላቸው፣ አላህ(ፍርዱን ሊፈጽምና) በደረቶቻችሁም ውስጥ ያለውን ሊፈትን በልቦቻችሁም ውስጥ ያለውን ነገር ሊገልጽ (ይህን ሰራ)፣ አላህም በደረቶች ውስጥ ያለን ሁሉ አዋቂ ነው» (አል-ዒምራን :154)*

﴿ ٱلظَّآنِّينَ بِٱللَّهِ ظَنَّ ٱلسَّوْءِ ۚ عَلَيْهِمْ دَآئِرَةُ ٱلسَّوْءِ ۖ ﴾

*«በአላህ ክፉ ጥርጣሬን ተጠራጣሪዎቹን በነሱ ላይ ክፉ ክባቢ አለባቸው::»(አል-ፈትሕ :6)*

ኢብኑል ቀይም የመጀመሪያውን አንቀፅ ሲያብራሩ እንዲህ ብለዋል:-

«ይህ ከአንቀፁ ላይ የተጠቀሰው መጠራጠር፣ አላህ መልዕክተኛውን አይረዳም፤ ተልዕኳቸው ይከስማል የሚል ዓይነት

ጥርጣሬ እንደነበር ተነግሯል። መልዕክተኛው የገጠማቸው ችግርና መከራ በአላህ እቅድና ኘላን፣ እንዲሁም በጥበቡ የተከሰተ አይደለም የሚል ነበርም ተብሏል። የአላህን ጥበብ፣ እቅድና ኘላን (ቀደር) መካድ። የመልዕክተኛው ዲን ከሌሎች ዲኖች ሁሉ የበላይ ይሆናል፡ የሚለውን መለኮታዊ ቃል ኪዳን አለመቀበል እንደሆነም ተገልጿል። በአል ፈትህ ምዕራፍ ላይ የተገለፀውና ሙናፊቆችና ሙሽሪኮች እንደፈፀሙት የተወሳው መጥፎ ጥርጣሬ ይኸው ነው። መጥፎ የተባለበት ምክንያት ለአላህ የማይገባው በመሆኑ ነው። ጥበቡን ያኮስሳል። የቃል ኪዳኑን እውነተኛነት ያረክሳል።

«ባጢል በሐቅ ላይ ዘለዓለማዊ የበላይነትን ይጎናፀፋል የሚል እምነት፤ በዚህ ፍጥረተ ዓለም ውስጥ የሚከሰቱ ክስተቶች በአላህ እቅድና ኘላን መፈፀማቸውን መካድ፤ እቅድና ኘላኑ ከፍተኛ ጥበብ ያዘለ መሆኑን አለመቀበልና ክስተቶቹ የሚፈፀሙት ያለ ጥበብ ነው፣ የሚል እምነት የነዚያ የካዱት ሰዎች ጥርጣሬ ነው። ከፍተኛ የእሳት ቅጣት ይጠብቃቸዋል።

«አብዛኛዎቹ ሰዎች ከግላዊ ህይወታቸው ጋር በተያያዘና አላህ በሌሎች ላይ እንዲከሰት በሚፈቅደው ሁኔታ መጥፎ ጥርጣሬ አላቸው። አላህን፣ ስሞቹንና ባህሪያቱን በጥልቅ የተረዳ፣ በመለኮታዊ ጥበብ ያመነ ካልሆነ ማንም ውሳኔዎቹን በፀጋ መቀበል፣ በእርካታ ማስተናገድ ይከብደዋል።ብልሆች ይህንን ጥበብ የላቀ ትኩረይ ይቸሩታል። በአላህ ላይ ላደረባቸው ክፉ ጥርጣሬ ሁሌም ተውበት ያደርጋሉ። ምህረቱን ይለምናሉ።

«የሰዎችን ሁኔታ ረጋ ብለህ ብታስተውል፣ በጥልቅ ብትመረምር በአላህ እቅድና ኘላን ሲማረሩ ብዙ ጊዜ ይገጥምሃል። ይህ መሆን ነበረበት፤ ያ መከሰት አልነበረበትም ሲሉ ታደምጣለህ። አንተስ ከእንዲህ ዓይነቱ ግድፈት የፀዳህ ነህ? ራስህን ፈትሽ። የፀዳህ ከሆንክ ዕድለኛ ነህ። ካልሆንክ ግን ለስኬት መብቃትህን እጠራጠራለሁ።»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. የአንቀፅ «አል ዒምራን 154» ትርጉም
2. የአንቀፅ «አል ፈትህ 6» ትርጉም
3. ከእንዲህ ዓይነት ግድፈት ሊድን የሚችለው የአላህን ማንነት በጥልቅ የተረዳ፣ መልካም ስሞቹንና ባህሪያቱን በትክክል ያወቀ ብቻ ነው።

# ምዕራፍ ስድሳ
## የአላህን ዕቅድና ኻላን (ቀደር) መካድ

ኢብን ዑመር እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«والذي نفْسُ ابن عُمَرَ بِيَدِهِ لَوْ كَانَ لأَحَدِهِمْ مِثْلُ أُحُدٍ ذَهَباً ثُمَّ أنْفَقَهُ في سَبيلِ الله مَا قَبِلَهُ الله مِنْهُ حتَّى يُؤْمِنَ بالقَدْرِ» ثم استدل بقول النبي ﷺ: «الإيمانُ أنْ تُؤْمِنَ بالله ومَلائِكَتِهِ وكُتُبِهِ ورُسُلِهِ واليَوْمِ الآخِرِ وتُؤْمِنَ بالقَدَرِ خَيْرِهِ وشَرِّهِ».

«የኢብን ዑመር ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! ከናንተ ለአንዳችሁ የኡሁድን ተራራ የሚያክል ወርቅ ቢኖረውና በአላህ መንገድ ቢመጸውተው በቀደር እስካላመነ ድረስ አላህ አይቀበለውም::» ለዚህ አባባላቸው:- «ኢማን በአላህ፣ በመላኢኮች፣ በመጽሐፍት፣ በመልዕክተኞችና በቀጣዩ ዓለም መኖር፣ እንዲሁም በቀደር- መልካምም ይሁን ክፉ- ማመንህ ነው::» በማለት ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ያሰሙትን ንግግር በዋቢነት አቀረቡ::

ዑባዳት ኢብን ሷሚት ለልጃቸው ተከታዩን ምክር መለገሳቸውን ሙስሊም ዘግበዋል:-

«أنَّهُ قَالَ لابنِهِ يا بُنَيَّ! إنَّكَ لَنْ تَجدَ طَعْمَ الإيْمَانِ حتَّى تَعْلَمَ أنَّ ما أَصَابَكَ لَمْ يَكُنْ لِيُخْطِئَكَ ومَا أخْطأَكَ لَمْ يَكُنْ لِيُصِيبَكَ. سَمِعْتُ رَسُولَ الله ﷺ يَقُولُ: إنَّ أوَّلَ مَا خَلَقَ الله القَلَمَ فَقَالَ لَهُ أُكْتُبْ فَقَالَ رَبِّ! مَاذَا أكْتُبُ؟ قَالَ: أكْتُبْ مَقَادِيرَ كُلِّ شَيءٍ حتَّى تَقُومَ السَّاعَةُ. يَا بُنَيَّ سَمِعْتُ رَسُولَ الله ﷺ يَقُولُ: مَنْ مَاتَ عَلى غَيْرِ هذَا فَلَيْسَ مِنِّي».

ልጄ ሆይ! ያገኘህ ነገር ሊስትህ፣ የሳተህ ደግሞ ሊያገኝህ እንደማይችል እስካላመንክ ድረስ የኢማንን ለዛ አታጣጥምም:: የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ አድምጫለሁ:-

«አላህ በመጀመሪያ የፈጠረው ብዕርን ነው:: ጻፍ አለው:: ጌታዬ ሆይ! የምፅፈው ምንድን ነው? አለ:: እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ ያለውን የእያንዳንዱን ነገር ልኬታ (መቃዲር) ክተብ፥ ሲል

አዘዘው።» ልጄ ሆይ! የአላህ መልዕክተኛ:- «በዚህ እምነት ሳይፀና የሞተ ሰው ከኔ ውጭ ነው።» ሲሉም አድምጫለሁ።

በሌላ የአህመድ ዘገባ ደግሞ:-

«أَنَّ أَوَّلَ مَا خَلَقَ الله تَعَالى القَلَمَ فَقَالَ لَهُ أَكْتُبْ فَجَرى فِي تِلْكَ السَّاعَةِ بِمَا هُوَ كَائِنٌ إلى يَوْمِ القِيامَةِ».

«ልዑል የሆነው አላህ መጀመሪያ የፈጠረው ብዕርን ነው። «ክተብ» ሲል አዘዘው። ከዚያን ዕለት አንስቶ እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ የሚከናወኑ ክስተቶች ያንዬ የተፃፉ ናቸው።»

በኢብን ወሕብ ዘገባ መሠረት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ):-

«فَمَنْ لَمْ يُؤمِنْ بالقَدَرِ خَيْرِهِ وشَرِّهِ أَحْرَقَهُ الله بالنَّارِ».

«በቀደር- መልካም ይሁን ክፉ- ያላመነ አላህ በእሳት ያቃጥለዋል።»ብለዋል።

በሙስነድና ሱነን ላይ እንደተወሳው ኢብን ደ..ለምይ ተከታዩን ዘገባ አስተላልፈዋል:-

«أَتَيْتُ أُبيَّ بنَ كَعْبٍ رضي الله عنه فَقُلْتُ في نَفْسِي شَيءٌ مِنَ القَدرِ فَحَدِّثْنِي بشيءٍ لَعَلَّ الله يُذْهِبُهُ مِنْ قَلْبِي. فَقَالَ لَوْ أَنْفَقْتَ مِثْلَ أُحُدٍ ذَهَباً مَا قَبِلَهُ الله مِنْكَ حتَّى تُؤمِنَ بالقَدرِ وتَعْلَمَ أَنَّ مَا أَصَابَكَ لَمْ يَكُنْ لِيُخْطِئَكَ ومَا أَخْطَأَكَ لَمْ يَكُنْ لِيُصِيبَكَ ولَوْ مُتَّ عَلَى غَيْرِ هَذَا لَكُنْتَ مِنْ أَهْلِ النَّارِ قَالَ فأَتَيْتُ عَبْدَ الله بنَ مَسْعُودٍ وحُذَيْفَةَ بنِ اليَمَانِ وزَيْدَ بن ثَابتٍ فَكُلُّهُمْ حَدَّثَنِي بِمِثْلِ ذلِكَ عَنِ النَّبيِّ ﷺ».

ከኡበይ ኢብን ካዕብ ዘንድ በመሄድ «ቀደርን አስመልክቶ ልቦናዬ ውስጥ ችግር አለብኝ። አንዳች ነገር ይንገሩኝ። ምን አልባትም አላህ ከልቦናዬ ውስጥ ያለውን ችግር ያስወገድልኝ ይሆናል» አልኳቸው። «የኡሁድን ተራራ የሚያክል ወርቅ ብትመፀውት እንኳ በቀደር እስካላመንክ ድረስ ምፅዋትህ ተቀባይነት የለውም። ያገኘህ ነገር ሊስትህ፣ የሳተህ ደግሞ ሊያገኝህ እንደማይችል አምነህ እስካልተቀበልክ ድረስ። እኔው ራሴ ልቤ በዚህ እምነት ላይ ሳይፀና ብሞት የእሳት ሰው እሆን ነበር።» አሉ።

አብደላህ ኢብን መስዑድ፣ ሁዘይፈት ኢብንል የማን እና ዘይድ ኢብን ሳቢትን አገኘኋቸው:: ሁሉም ነብዩን (ሶ.ዐ.ወ) ዋቢ በማድረግ ተመሳሳይ መልዕክት ነገሩኝ:: (ሐኪም ሶሒሕ ጥራዛቸው ውስጥ አስፍረውታል)

## <u>ጠቃሚ ነጥቦች</u>

1. በቀደር የማመን ግዴታነት::
2. በቀደር የማመን ትክክለኛ ትርጓሜ::
3. በቀደር ያላመነ መልካም ሥራዎቹ ተቀባይነት የላቸውም::
4. አንድ ሰው በቀደር እስካላመነ ድረስ የኢማንን ለዛ አያጣጥምም::
5. አላህ መጀመሪያ ያስገኘው ፍጡር ተወስቷል::
6. ከዚያን ዕለት አንስቶ እስከ ዕለተ ቂያማ ድረስ የሚከሰቱ ሁኔታዎች በሙሉ በአላህ እቅድና ኃላን መሠረት የሚፈፀሙ ናቸው::
7. በቀደር የማያምን ሰው ከርሳቸው መንገድ ውጭ መሆኑን ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ተናግረዋል::
8. አንዳች የሚያምታታ ነገር ሲፈጠርባቸው ኡለማዎችን በመጠየቅ ለማስወገድ መጣር የሰለፎች ልምድ ነበር::
9. ኡለሞች የሰጡት ምላሽ ረሱል (ሶ.ዐ.ወ) በጉዳዩ ላይ የሰጡት ብይን ብቻ በመሆኑ አጥጋቢ ነበር::

## ምዕራፍ ስድሳ አንድ
## ሰዓሊያን የሚጠብቃቸው አስከፊ ቅጣት

አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«قال الله تعالى: ومَنْ أظْلَمُ مِمَّنْ ذَهَبَ يَخْلُقُ كَخَلْقِي فَلْيَخْلُقُوا ذَرَّةً أوْ لِيَخْلُقوا حَبَّةً أوْ لِيَخْلُقُوا شَعِيرَةً».

«አላህ እንዲህ ብሏል:- የኔን ፍጡራን አስመስሎ ለመፍጠር ከሚሞክር የበለጠ ግፈኛ ማንው? (ከቻለ) አቶም፣ የጕመንዘር ቅንጣት ወይም ገብስ ይፍጠር::»

ዓኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) :-

«أشَدُّ النَّاسِ عَذَاباً يَوْمَ القِيَامَةِ الذِينَ يُضَاهِئُونَ بِخَلْقِ الله»

«የቂያማ ዕለት ከማንም በከፋ ሁኔታ ቅጣት የሚጠብቃቸው ከአላህ ጋር በፈጣሪነት የሚፎካከሩ ናቸው::» ብለዋል::

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት ኢብን አባስ ማስትላለፋቸውን ቡኻሪና ሙስሊም ዘግበዋል:-

«كُلُّ مُصَوِّرٍ في النَّارِ يُجْعَلُ لَهُ بِكُلِّ صُورةٍ صَوَّرَهَا نَفْسٌ يُعَذَّبُ بهَا في جَهَنَّم».

«እያንዳንዱ ሰዓሊ የእሳት ቅጣት ይጠብቀዋል:: በሰራው በእያንዳንዱ ስዕል ልክ ጀሀነም ውስጥ የሚቀጣበት ነፍስ ይበጅለታል::»

ኢብን ዓባስን በመጥቀስ ቡኻሪና ሙስሊም:-

«مَنْ صَوَّرَ صُورةً في الدُّنْيَا كُلِّفَ أنْ يَنْفُخَ فِيهَا الرُّوحَ ولَيْس بنَافخ».

«በዚህች አለም ውስጥ አንዲት ስዕል የሳለ የቂያማ ዕለት ሩህ እንዲያገባበት ይገደዳል፤ አይሳካለትም» መባሉን ዘግበዋል::

አቡ ሂያጅ ተከታዩን ማለታቸውን ሙስሊም ዘግበዋል:-

«ألا أبْعَثُكَ عَلى مَا بَعَثَنِي عَلَيْه رَسُولُ الله ﷺ ألاَّ تَدَعَ صُورةً إلاَّ طَمَسْتَهَا، ولاَ قَبْراً مُشرفاً إلاَّ سَوَّيْتَه»

አሊ፦ «የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዳከናወን ያዘዙኝን ተግባር ልዘዝህን? የምታገኛቸውን ስዕሎች በሙሉ አጥፋ፤ ከፍ ብሎ የታነፀ ቀብርም ካገኘህ አስተካክል» አሉ።

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. ሰዓሊያን በጥብቅ ተወግዘዋል።

2. የዚህም ምክንያቱ ከአላህ ጋር ሊኖር የሚገባው አደብ መጣሱ እንደሆነ «አላህን ከሚፎካከር የበለጠ ግፈኛ የለም» የሚለው የዘገባው ቃል ያመለክታል።

3. አላህ የሚሻውን የማድረግ ችሎታ እንዳለውና ፍጡራን ግን ቅንጣት እንደማይፈጥሩ «ከቻለ አቶም፣ የእህል ዘር ወይም የገብስ ፍሬ ይፍጠር» በሚለው ነቢያዊ ቃል ተመልክቷል።

4. ሰአሊያን የከፋ ቅጣት ይጠብቃቸዋል።

5. አላህ፦ በሳሏቸው ስዕሎች ልክ ነፍስ በመፍጠር ጀሀነም ውስጥ ይቀጣቸዋል።

6. ሩህ እንዲያገቡም ያስገድዳቸዋል።

7. ስዕሎችን ማጥፋትና መሰባበር እንደሚገባ።

## ምዕራፍ ስድሳ ሁለት
## መሐላን ማብዛት ስለ መከልከሉ

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَٱحۡفَظُوٓاْ أَيۡمَٰنَكُمۡۚ﴾

«መሐላዎቻችሁን ጠብቁ» (አል- ማኢዳህ :89)

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አቡ ሁረይራ (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«الحَلْفُ مَنْفَقَةٌ للسِّلْعَةِ مَمْحَقَةٌ للكَسْبِ»

«መሐላ ሸቀጥን ሊያስወድድ ቢችልም በረካን ግን ያብሳል::» (ቡኻሪና ሙስሊም)

ሰልማን እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«ثَلاثَةٌ لا يُكَلِّمُهُمُ الله ولا يُزَكِّيهِم ولَهُمْ عَذَابٌ أليمٌ: أُشَيْمِطُ زَانٍ، وعَائِلٌ مُسْتَكْبِرٌ، ورَجُلٌ جَعَلَ الله بِضَاعَتَه لا يَشْتَرِي إلاَّ بيَمِينِهِ ولاَ يَبِيعُ إلاَّ بِيَمِينِه».

«አላህ የቂያማ ዕለት ለሦስት ሰዎች ምህረትን አይለግስም፣ አያፀድቃቸውምም:: አጅግ አሳማሚ ቅጣት ይጠብቃቸዋል:: እነሱም የአዛውንት ሴሰኛ፣ ኩራተኛ የቅርብ ዘመድና ሸቀጡን በመሃላ እንጅ የማይሸጥ፣ በመሃላ እንጅ የማይገዛ ነጋዴ ናቸው::» (ጦበራኒ ዘግበውታል)

ኢምራን ኢብን ሁሰይን እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«خَيْرَ أُمَّتِي قَرْنِي، ثُمَّ الذِينَ يَلُونَهُمْ ثُمَّ الذِينَ يَلُونَهُمْ قَالَ عِمْرَانُ فَلاَ أدْرِي أَذَكَرَ بَعْدَ قَرْنِهِ مَرَّتَيْنِ أوْ ثَلاَثاً؟ ثُمَّ إنَّ بَعْدَكُمْ قَوْماً يَشْهَدُونَ ولا يَسْتَشْهَدُونَ وَلا يَخُونُونَ ولا يُؤتَمَنُونَ وَيَنْذُرُونَ ولاَ يُوفُونَ ويَظْهَرُ فِيهِمُ السِّمَنُ»

«ከተከታዮቼ በላጩ እኔ የምገኝበት ትውልድ ነው:: ከዚያም የሚቀጥለው፣ ከዚይም የሚቀጥለው፣ (ከርሳቸው ትውልድ በኋላ ሁለት ትውልዶችን ብቻ ያውሱ ወይም ሦስተኛ

ይጨምሩ አላስታውስም::) በመቀጠልም ሳይጠየቁ ምስክርነት የሚሰጡ፣ ፈፅሞ ሊታመኑ የማይችሉ፣ የሚሳሉ ግን ስለታቸውን የማይሞሉና ሰውነታቸው የገዘፈ ትውልዶች ከናንተ በኋላ ይመጣሉ::» (ቡኻሪ)

ኢብን መስዑድ እንዳስተላለፉት ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«خَيْرُ النَّاسِ قَرْنِي ثُمَّ الذِينَ يَلُونَهُمْ ثُمَّ الذِينَ يَلُونَهُم ثُمَّ يَجِيءُ قَوْمٌ تَسْبِقُ شَهَادَةُ أَحَدِهِمْ يَمِينَهُ وَيَمِينُهُ شَهَادَتَه».

«ከትውልድ ሁሉ በላጩ እኔ የምገኝበት ትውለድ ነው፤ ከዚያም ሚቀጥለው፤ ከዚያም የሚቀጥለው፤ በመቀጠልም ምስክርነታቸው መሐላቸውን፣ መሐላቸው ምስክርነታቸውን የሚቀድም ሰዎች ያሉበት ትውልድ ይመጣል::»

ኢብራሂም እንዲህ ብለዋል:-

«ህፃናት እያለን በችኮላ ምስክርነትን ስንሰጥ ወላጆቻችን ይገርፉን ነበር::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. መሐላን መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑ ተጠቅሷል::

2. መሐላ የሸቀጥን ዋጋ ከፍ የሚያደርግበት አጋጣሚ እንደሚኖር ተወስቷል::

3. በመሐላ ካልሆነ የማይሸጥና የማይገዛ ነጋዴ በጥብቅ ተወግዟል::

4. ብዙም አስፈላጊ ባልሆነ ድርጊት የከበደ ወንጀል መፈፀም::

5. ሳይጠየቁ መሐላ የሚደረድሩ ሰዎች በጥብቅ ተወግዘዋል::

6. ነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የመጀመሪያዎቹን ሦስት ወይም አራት ትውልዶች መልካምነት መስክረዋል:: ቀጣዮቹ ትውልዶች ምን ዓይነት ሊሆኑ እንደሚችሉም ተንብየዋል::

7. ለምስክርነት ሳይጠሩ የሚመሰክሩ ሰዎች ተወግዘዋል::

8. ሰለፎች በምስክርነትና በመሐላ ሰበብ ልጆቻቸውን ይቀጡ እንደነበር ተመልክትል::

# ምዕራፍ ስድሳ ሦስት

# ስለ አላህና መልዕክተኛው የጥበቃ ቃል ኪዳን (ዚመህ)

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿وَأَوۡفُواْ بِعَهۡدِ ٱللَّهِ إِذَا عَٰهَدتُّمۡ وَلَا تَنقُضُواْ ٱلۡأَيۡمَٰنَ بَعۡدَ تَوۡكِيدِهَا وَقَدۡ جَعَلۡتُمُ ٱللَّهَ عَلَيۡكُمۡ كَفِيلًاۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا تَفۡعَلُونَ﴾

*«ቃል ኪዳንም በገባችሁ ጊዜ በአላህ ቃል ኪዳን ሙሉ፤ መሐላዎቻችሁንም ካጠናከራችኋቸው በኋላ አታፍርሱ::» (አል-ነሕል:19)*

ቡረይዳህ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:-

«كَانَ رَسُولُ الله ﷺ إذَا أَمَّرَ أَمِيراً عَلى جَيشٍ أَوْ سَرِيَّةٍ أَوْصَاهُ بِتَقْوَى الله ومَنْ مَعَهُ مِنَ المُسْلِمِينَ خَيْراً». فَقَالَ اغْزُوا بِسمِ الله فِي سَبيلِ الله قَاتِلُوا مَنْ كَفَرَ بالله. اغْزوا ولا تَغلُوا ولاَ تَغْدِرُوا ولا تُمَثِّلُوا ولاَ تَقْتُلُوا وَلِيداً. وإذَا لَقِيتَ عَدُوَّكَ مِنَ المُشْرِكينَ فَادْعُهُمْ إلى ثَلاَثِ خِصَالٍ أوْ خَلاَلٍ فأَيَّتَهُنَّ أجَابُوا لَكَ فَاقْبَلْ مِنْهُمْ وكفَّ عَنهُمْ.

ثُمَّ ادْعُهُمْ إلى الإسْلاَمِ فَإنْ أَجَابُوا لَكَ فَاقْبَلْ مِنهُمْ ثُمَّ ادْعُهُمْ إلى التَّحَوُّلِ مِنْ دَارِهِمْ إلى دَارِ المُهَاجِرينَ وأَخْبِرْهُمْ أنَّهُمْ إنْ فَعَلُوا ذَلِكَ فَلَهُمْ مَا للمُهَاجِرينَ وعَلَيْهِمْ مَا عَلى المُهَاجِرينَ، فَإنْ أَبَوا أنْ يَتَحَوَّلُوا مِنْهَا فأَخْبِرْهُمْ أنَّهُمْ يَكُونُونَ كأَعْرابِ المُسْلِمينَ يَجْرِي عَلَيْهِمْ حُكْمُ الله تَعَالى ولاَ يَكُونُ لَهُمْ في الغَنِيمَـةِ والفَـيءِ شَـيءٌ إلاَّ أنْ يُجَـاهِـدُوا مـعَ المُسْلِمِيـنَ، فَإنْ هُمْ أَبَوْا فاسْأَلْهُمُ الجِزْيَةَ فَإنْ هُمْ أَجَابُوا لَكَ فَاقْبَلْ مِنهُمْ وكفَّ عَنهُمْ فَإنْ هُمْ أَبوا فَاستَعِنْ بالله وقَاتِلهُمْ، وإذَا حَاصَرْتَ

أَهْلَ حِصْنٍ فَأَرَادُوكَ أَنْ تَجْعَلَ لَهُمْ ذِمَّةَ اللهِ وذِمَّةَ نَبِيِّهِ فَلا تَجْعَلْ لَهُمْ ذِمَّةَ اللهِ وذِمَّةَ نَبِيِّهِ ولكنْ اجْعَلْ لَهُمْ ذِمَّتَكَ وذِمَّةَ أَصْحَابِكَ فَإِنَّكُمْ إِنْ تُخْفِرُوا ذِمَمَكُمْ وذِمَّةَ أَصْحَابِكُمْ أَهْوَنُ مِنْ أَنْ تُخْفِرُوا ذِمَّةَ اللهِ وذِمَّةَ نَبِيِّهِ، وإِذَا حَاصَرْتَ أَهْلَ حِصْنٍ فَأَرَادُوكَ أَنْ تُنْزِلَهُمْ عَلى حُكْمِ اللهِ فَلَا تُنْزِلْهُمْ ولكِنْ أَنْزِلْهُمْ عَلى حُكْمِكَ فَإِنَّكَ لاَ تَدْرِي أَتُصِيبَ فِيهِمْ حُكْمَ اللهِ أَمْ لاَ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ለአንድ ጦር አበጋዝ በሚሾሙበት ወቅት አላህን እንዲፈራና በስሩ ያሉ ሙስሊሞችን በመልካም ሁኔታ እንዲይዝ ይመክሩት ነበር:: እንዲህም ይሉት ነበር:- «በአላህ ስም ዝመቱ፤ በአላህ መንገድ:: አላህን የካደን ሁሉ ተዋጉ:: የገንዘብ ምርኮዎችን አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ለግል ጥቅማችሁ አታውሉ:: የገባችሁትን ቃል አታፍርሱ:: የሰዎችን አካል የመቆራረጥ አረመኒያዊ ተግባር አትፈፅሙ:: ህፃናትን አትግደሉ::

«ሙሽሪክ ጠላትህን በምታገኝበት ወቅት ሦስት ምርጫዎችን አቅርብለት:: ከሦስቱ አንዱን ከተቀበለህ ከግድያ ታቀብ:: ወደ ኢስላም ጥሪ አቅርብላቸው:: ከተቀበሉህ መልካም ሆነ:: ያሉበትን አገር ጥለው ወደ መዲና እንዲሰደዱ ጠይቃቸው:: ይህን ካደረጉ ሙሐጅሮች ያላቸው መብት እንደሚኖራቸው፣ በነርሱ ላይ የሚፀናው ግዴታ እንደሚፀናባቸው ንገራቸው:: ለመሰደድ ፈቃደኛ ካልሆኑ እንደበደዊን ሙስሊሞች ተቆጥረው የአላህ ህግ እንደሚፀናባቸው፣ ከምርኮ ገንዘብ- ከሙስሊሞች ጋር አብረው እስካል ዘመቱ ድረስ- ቅንጣት እንደማይደርሳቸው ግለፅላቸው:: አሻፈረን ካሉ ግብር (ጂዚያ) ጠይቃቸው:: ከተቀበሉህ ተቀበል:: ከውጊያውም ታቀብ:: አሻፈረን ካሉ በአላህ በመታገዝ ተዋጋቸው:: አንድን አካባቢ ከከበብክና ነዋሪዎቹ የአላህንና የመልዕክተኛውን የጥበቃ ቃል ኪዳን (ዚመህ) ከጠየቁህ አትቀበላቸው:: የአንተንና የባልደረቦችህን ዚማህ ብቻ ስጣቸው:: ቃል ኪዳናችሁን ብታፈርሱ እንኳ በአላህና በመልዕክተኛው ስም የሰጣችሁትን ቃል ከማፍረስ የአንተንና የባልደረቦችህን ማፍረስ ይቀላል:: የአላህን ውሳኔ ከጠየቁህ አትቀበል:: የራስህን ውሳኔ ብቻ ስጣቸው:: አንተ የምትሰጠው ብይን ከአላህ ፍላጎት ጋር መጣጣሙን የምታውቅበት ምንም መንገድ የለም::» (ሙስሊም)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. በአላህና በመልዕክተኛ «ዚመህ» እና በሙስሊሞች «ዚመህ» መካከል ያለው ልዩነት::

2. ከሁለት ጎጂ ሁኔታዎች ቀለል ያለውን መምረጥ::

3. «በአላህ ስም፣ በአላህ መንገድ ዝመቱ» የሚለው ነብያዊ ትዕዛዝ::

4. «በአላህ የካደን ሁሉ ተዋጉ» የሚል ትዕዛዝ መስጠታቸው::

5. «በአላህ ታገዝና ተፋለማቸው» በማለት የሰጡት ትዕዛዝ::

6. በአላህ «ሁክም» (ብይን) እና በዑለሞች «ሁክም» መካከል ያለው ልዩነት::

7. ሶሃቦች አስፈላጊ በሆነ ወቅት ብይን ይሰጣሉ:: የሚሰጡት ብይን ግን ከአላህ ፍላጎት ጋር ሊጣጣም ወይም ላይጣጣም ይችላል::

# ምዕራፍ ስድሳ ስራት
# ከአላህ መብት ጋር የተያያዘ መሐላ

ጁንዳብ ኢብን ዐብደላህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) እንዲህ ብለዋል:-

«قَالَ رَجُلٌ واللهِ لاَ يَغْفِرُ اللهُ لِفُلاَنٍ. فَقَالَ اللهُ تَعَالى مَنْ ذَا الذِي يَتَأَلَّى عَلَيَّ أَنْ لا أَغْفِرَ لِفُلانٍ؟ إنِّي قَدْ غَفَرْتُ لَهُ وأَحْبَطْتُ عَمَلَكَ».

«አንድ ሰው:- በአላህ ይሁንብኝ እገሌን አላህ አይምረውም፥ ሲል ተናገረ:: አላህም:- እገሌን እንደማልምረው በመሐላ ያፀደቀ ማን ነው? ለርሱ ምህረት ለግሼ ያንተን ተግባር ዋጋ ቢስ አድርጌዋለሁ፥ አለ::» (ሙስሊም)

ተናጋሪው አላህን በእጅጉ የሚያመልክ ሰው ነበር::
አቡ ሁረይራ እንዲህ ማለታቸው ተወስቷል:-

«تَكَلَّمَ بِكَلِمَةٍ أَوْبَقَتْ دُنْيَاهُ وآخِرَتَهُ».

«ዱንያውንም አኼራውንም ያጠፋች ንግግር ተናገረ::»

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. በአላህ ላይ መማል በጥብቅ የተወገዘ ነው::
2. እሳት ለእያንዳንዳችን እጅግ ቅርብ ናት::
3. ጀነትም እንዲሁ ቅርባችን ናት::
4. የምንናገራትን እያንዳንዷን ንግግር አላህ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል::
5. አንድ ሰው ባልጠበቀው ሁኔታ ምህረትን የሚጐናፀፍበት አጋጣሚ ይከሰታል::

# ምዕራፍ ስድሳ ስምንት
## አላህ ወደ ፍጡራኑ ባማላጅነት (ሽፋዐ) አይላክም

ጁበይር ኢብን ሙጥዒም (ረዐ) ተከታዩን አስተላልፈዋል:-

«جَاءَ أَعْرَابِيٌّ إلى النبيِّ ﷺ فَقَالَ يَا رَسُولَ الله! نُهِكَتِ الأَنْفُسُ وجَاعَ العِيَالُ وهَلَكَتِ الأَمْوَالُ فَاسْتَسْقِ لَنَا رَبَّكَ فَإِنَّا نَسْتَشْفِعُ باللهِ عَلَيْكَ وبِكَ عَلَى الله، فَقَالَ النَّبِيُّ ﷺ سُبْحَانَ اللهِ سُبْحَانَ اللهِ فَمَا زَالَ يُسَبِّحُ حتَّى عُرِفَ ذَلِكَ فِي وُجُوهِ أَصْحَابِهِ ثُمَّ قَالَ وَيْحَكَ أَتَدْرِي مَا اللهُ! إِنَّ شَأْنَ اللهِ أَعْظَمُ مِنْ ذَلِكَ إِنَّهُ لاَ يُسْتَشْفَعُ باللهِ عَلى أَحَدٍ».

አንድ በደዊን ከነብዩ (ሰ.ዐ.ወ) ዘንድ መጣና:- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! ሰዎች እያለቁ ነው:: ቤተሰብ ተርቧል:: ንብረቶቻችን ወድመዋል:: ዝናብን ይለግሰን ዘንድ አላህን ይማፀኑልን:: አላህን ወደርስዎ፣ እርስዎን ደግሞ ወደ አላህ በአማላጅነት ልከናል» አላቸው:: «ሱብሐነላህ!» አሉ መልዕክተኛው (ሶ.ዐ.ወ)፤ በመደጋገም ባልደረቦቻቸው ስሜታቸውን እስኪጋሩ ድረስ:: በመቀጠልም :- «ወዮልህ! የአላህን ማንነት በትክክል ታውቃለህ? አላህ አንተ ከምታስበው በላይ ነው:: አላህ ወደ ማንም በአማላጅነት አይላክም::» አሉት:: (አቡዳውድ)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. አላህን ወደ ማንም በአማላጅነት መላክ በጥብቅ ተወግዟል::
2. የመልዕክተኛው የቁጣ ስሜት ከባልደረቦቻቸው ላይም ተንፀባርቋል::
3. የእርሳቸውን ወደ አላህ በአማላጅነት መላክ አልተቃወሙም::
4. «ሱብሐነ ላህ» የሚለው ቃል ትርጓሜ::
5. ሙስሊሞች ነቢዩን (ሶ.ዐ.ወ) ዝናብ ያገኙ ዘንድ አላህን እንዲማፀኑላቸው ይጠይቋቸው ነበር::

## ምዕራፍ ስድሳ ስድስት

## ነብዩ (ሶ.ዐ.ወ) ስተውሂድ ጥብቅና መቆማቸውና የሽርክን መንገዶች ሁሉ መዝጋታቸው

አብደላህ ኢብን ሸኺረህ (ረዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«انطَلَقْتُ فِي وَفْدِ بَنِي عَامِرٍ إلى رَسُولِ الله ﷺ فقُلْنَا أَنْتَ سَيِّدُنَا فقَالَ السَّيِّدُ الله تَبَارَكَ وتَعَالى، قُلْنَا وأَفْضَلُنَا فَضْلاً وأَعْظَمُنَا طَوْلاً فقَالَ قُولُوا بِقَولِكُم أَوْ بَعْضَ قَولِكُمْ ولاَ يَستَجْرِيَنَّكُمُ الشَّيطانُ».

ከበኒ ዓሚር ልዑክ ጋር ወደ አላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ዘንድ ሄድን:: «እርስዎ አለቃችን (ሰይድ) ነዎት» አልናቸው:: «ሰይድ አላህ ነው፤ ልዑል የሆነው ጌታ» አሉን:: «ከሁላችንም እጅግ የላቁ፣ ቃልዎም እጅግ የከበረ» ስንል አሞካሸናቸው::«የመጣችሁበትን ጉዳይ ብቻ ተናገሩ፤» ሸይጧን መንገድ እንዳያስታችሁ» አሉን:: (አቡ ዳውድ ዘግበውታል)

አነሰ (ረዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«أَنَّ ناساً قَالُوا يَا رَسُولَ الله يَا خَيْرَنَا وابنَ خَيْرِنَا وَسَيِّدَنَا وابنَ سَيِّدِنَا، فَقَالَ أَيُّهَا النَّاسُ! قُولُوا بِقَوْلِكُمْ ولاَ يَسْتَهْوِيَنَّكُمُ الشَّيطانُ، أَنَا مُحَمَّدٌ عَبْدُ الله ورَسُولُهُ ما أُحِبُّ أَنْ تَرْفَعُونِي فَوْقَ مَنْزِلَتِي التِي أَنْزَلَنِي الله عَزَّ وجَلَّ».

ሰዎች :- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በላጫችን፣ የበላጫችን ልጅ፤አለቃችን፣ የአለቃችን ልጅ» ባሏቸው ጊዜ:- «እናንተ ሰዎች ሆይ! ሸይጧን በስሜታችሁ አይጫወት:: እኔ የአላህ ባሪያ ሙሐመድ ነኝ፤ የአላህ መልዕክተኛ:: አላህ ከለገሰኝ ደረጃ በላይ ከፍ እንድታደርጉኝ አልሻም» አሉ:: (ነሳኢ ዘግበውታል)

### ጠቃሚ ነጥቦች

1. ነቢዩ ሰዎችን ከግነት አስጠንቅቀዋል::
2. «አለቃችን» በሚል የማዕረግ ስም የተጠራ ሰው ማለት ያለበት ትክክለኛ ቃል::

3. «ሸይጧን መንገድ እንዳያስታችሁ» የሚለው ነቢያዊ ምክርና ማስጠንቀቂያ:: ምንም እንኳ እነርሱ የተናገሩት ሐቅ ቢሆንም::

4. «አላህ ከለገሰኝ ደረጃ በላይ ከፍ እንድታደርጉኝ አልሻም» ማለታቸው::

# ምዕራፍ ስድሳ ሰባት
## ስለ አላህ ተገቢውን ክብር ስለሰጡም

አላህ እንዲህ ብሏል:-

﴿ وَمَا قَدَرُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦ وَٱلْأَرْضُ جَمِيعًا قَبْضَتُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ وَٱلسَّمَـٰوَٰتُ مَطْوِيَّـٰتٌۢ بِيَمِينِهِۦ ۚ سُبْحَـٰنَهُۥ وَتَعَـٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴾

*«አላህንም በትንሳኤ ቀን ምድር በሙሉ ጭብጡ ስትሆን፣ ሰማያትም በሐይሉ የሚጠቀለሉ ሲሆን ከርሱ ጋር ሌላን በማጋራታቸው ተገቢ ክቡሩን አላከበሩትም» (አል-ዙመር :67)*

ኢብን መስዑድ (ረዐ) እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«قَالَ جَاءَ حَبْرٌ مِنَ الأَحْبَارِ إلى رَسُولِ الله ﷺ فَقَال: يَا مُحَمَّدُ إنَّا نَجِدُ أنَّ الله يَجْعَلُ السَّمٰواتِ على إصبَعٍ والأَرْضِينَ عَلى إصْبَعٍ والشَّجَرَ عَلى إصْبَعٍ وسَائِرَ الخَلْقِ عَلَى إصْبَعٍ فَيَقُولُ أنَا المَلِكُ فَضَحِكَ النَّبِيُّ حتَّى بَدَت نَوَاجِذُهُ تَصْدِيقاً لِقَوْلِ الحَبْرِ. ثُمَّ قَرَأَ ﴿وَمَا قَدَرُوا الله حَقَّ قَدْرِهِ والأَرْضُ جَمِيعاً قَبْضَتُهُ يَوْمَ القِيَامَةِ﴾.

ከቀሳውስት አንዱ ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ በመምጣት:- «ሙሐመድ ሆይ! አላህ ሰማያትን በአንድ ጣቱ፣ ምድሮችንም በአንድ ጣቱ፣ ዛፎችን በአንድ ጣቱና ሌሎችንም ፍጡራን በአንድ ጣቱ አድርጎ፥ የሁሉም ነገር የበላይ ገዥ እኔ ነኝ፥ እንደሚል ከቅዱስ መጽሐፋችን ውስጥ አግኝተናል» አላቸው:: ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ፈገግ በማለት የአባባሉን ትክክለኝነት አፀደቁ:: ከዚያም :- «አላህንም የትንሳኤ ቀን ምድር ሙሉ ጭብጡ ስትሆን ከርሱ ጋር ሌላን በማጋራት ተገቢውን ክብር አላከበሩትም» የሚለውን የቁርአን አንቀፅ አነበቡ::

ከሙስሊም ዘገባ ላይ ደግሞ:-

«والجِبَالَ والشَّجَرَ عَلى إصْبَعٍ ثُمَّ يَهُزُّهُنَّ فَيَقُولُ أنَا المَلِكُ أنَا الله».

ተራሮችንና ዛፎችን በአንድ ጣቱ ይይዛል:: ከዚያም ይወዘውዛቸዋል:: «እኔ የሁሉም ነገር የበላይ ገዥ ነኝ:: እኔ አላህ ነኝ::» ይላልም፥ የሚል ተወስቷል::

በቡኻሪ ዘገባ ላይ እንደተወሳው:-

«يَجْعَلُ السَّمٰـوَاتِ عَلَى إِصْبعٍ والمَاءَ والثَّرى عَلَى إِصْبَعٍ وسَائِرَ الخَلْقِ عَلى إِصْبَعٍ».

«ሰማያትን በአንድ ጣቱ፣ ውሃዎችንና አፈሮችን በአንድ ጣቱ፣ ሌሎችን ፍጡራን ደግሞ በአንድ ጣቱ ይይዛል::»

ሙስሊም ኢብን ዑመርን (ረዐ) ጠቅሰው መርፉዕ በሆነ ሰነድ እንደዘገቡት :-

«يَطْوِي الله السَّمٰـوَاتِ يَوْمَ القِيَامَةِ ثُمَّ يَأْخُذُهُنَّ بِيَدِهِ اليُمْنَى ثُمَّ يَقُولُ: أَنَا المَلِكُ أَيْنَ الجَبَّارُونَ؟ أَيْنَ المُتَكَبِّرونَ؟ ثُمَّ يَطْوِي الأَرْضِينَ السَّبْعَ ثُمَّ يَأْخُذُهُنَّ بِشِمَالِهِ ثُمَّ يَقُولُ: أَنَا المَلِكُ، أَيْنَ الجَبَّارُونَ؟ أَيْنَ المُتَكَبِّرونَ؟»

አላህ የቂያማ ዕለት ሰማያትን ይጠቀልላል:: ከዚያም በቀኝ እጁ ይይዛቸዋል:: እንዲህም ይላል:- «የሁሉም ነገር የበላይ ገዥ እኔ ነኝ:: አምባገነኖች የት አሉ:: ትዕቢተኞች የት አሉ::» ከዚያም ሰባቱን መሬቶች በመጠቅለል በግራ እጁ ይይዛል:: «የሁሉም ነገር የበላይ ገዥ እኔ ነኝ:: አምባገነኖች የት አሉ:: ትዕቢተኞች የት አሉ::» በማለት ይጠይቃል::

ኢብን ዓባስ (ረዐ) እንዳስተላለፉት:-

«مَا السَّمٰـوَاتُ السَّبْعُ والأَرْضُونَ السَّبْعُ فِي كَفِّ الرَّحمنِ إلاَّ كَخَرْدَلَةٍ فِي يَدِ أَحَدِكُمْ».

«ሰባቱ ሰማያት ከኩርስይ አንፃር ሲታዩ ከአንድ ጋሻ መሬት ላይ የወደቁ ሰባት ዲርሃሞችን ያክል ናቸው::» መባሉ ተወስቷል::

ኢብን ወሕብን ጠቅሰው ዩኑስ አጫውተውኛል በማለት ኢብን ጀሪር እንደተናገሩት የአላህ መልዕክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ተከታዩን ማለታቸውን ኢብን ዘይድ አባታቸውን ዋቢ በማድረግ አስተላልፈዋል:-

«مَا السَّمـوَاتُ السَّبْعُ في الكُرْسِي إلاَّ كَدَرَاهِمَ سَبْعَةٍ أُلْقِيَتْ فِي تُرْسٍ».

«ሰባቱ ሰማያት ከኩርስይ አንፃር ሲታዩ ከአንድ ጋሻ መሬት ላይ የወደቁ ሰባት ዲርሃሞችን ያክል ናቸው::»

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አቡ ዘር (ረዐ) አስተላልፈዋል:-

«مَا الكُرْسِيُّ فِي العَرْشِ إلاَّ كَحَلَقَةٍ مِنْ حَدِيدٍ أُلْقِيَتْ بَيْنَ ظَهْرَي فَلَاةٍ مِنَ الأَرْضِ».

«ኩርስይ ከአርሽ አንፃር ሲታይ ከሰፊ ሜዳ ላይ የወደቀችን የጣት ቀለበት ያክል ነው::»

ኢብን መስዑድ እንዲህ ሲሉ ተደምጠዋል:-

«بَيْنَ السَّمَاءِ الدُّنْيَا والتِي تَلِيهَا خَمْسُمائَةِ عَامٍ، وبَيْنَ كُلِّ سَمَاءٍ خَمْسُمائَةِ عَامٍ، وبَيْنَ السَّمَاء السَّابِعَةِ والكُرْسِيِّ خَمْسُمائَةِ عَامٍ، وبَيْنَ الكُرْسيِّ والمَاءِ خَمْسُمائَةِ عَامٍ، والعَرْشُ فَوْقَ المَاءِ واللهُ فَوْقَ العَرْشِ لاَ يَخْفى عَلَيهِ شَيءٌ مِنْ أعَمَالِكُمْ».

«በታችኛውና በሚቀጥለው ሰማይ፣ እንዲሁም በሰማያት መካከል የአምስት መቶ ዓመታት ርቀት ይገኛል:: በሰባተኛው ሰማይና በኩርስይ መካከል የአምስት መቶ ዓመታት ርቀት አለ:: በኩርስይና በውሃው መካከልም የአምስት መቶ ዓመታት ርቀት አለ:: ዓርሽ ከውሃው በላይ ነው:: አላህ ደግሞ ከአርሽ በላይ ነው:: ከተግባራችሁ መካከል ከአላህ ቁጥጥር ውጭ የሆነ አንድም ተግባር የለም::» (ኢብን መሕድይ)

መስዑድይ አሲምን ጠቅሰው ተመሳሳይ ዘገባ አስተላልፈዋል:: አል ሐፊዝ ዘሕበይም ዘግበውታል:: «ሌሎች ሰነዶችም አሉት::» ብለዋል::

ዓብባስ ኢብን አብዱል ሙጦሊብ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል:-

«هَلْ تَدْرُونَ كَمْ بَيْنَ السَّمَاءِ والأَرْضِ؟ قُلْنَا: اللهُ ورَسُولُهُ أَعْلَمُ. قَالَ: بَيْنَهُمَا مَسِيرَةُ خَمْسمائَةِ سَنَةٍ ومِنْ كُلِّ سَمَاءٍ إلى سَمَاءٍ مَسِيرَةُ خَمْسمائَةِ سَنَةٍ، وكِثَفُ كُلِّ سَمَاءٍ مَسِيرَةُ خمسمائَةِ سَنَةٍ، وبَيْنَ السَّمَاءِ السَّابِعَةِ والعَرْشِ بَحْرٌ بَيْنَ أَسْفَلِهِ وأَعْلاهُ كَمَا بَيْنَ السَّمَاءِ والأَرْضِ، واللهُ تَعَالى فَوْقَ ذَلِكَ ولَيْسَ يَخْفَى عَلَيْهِ شَيءٌ مِنْ أَعْمَالِ بني آدَمَ».

የአላህ መልዕክተኛ (ሶ.ዐ.ወ) «በሰማይና በምድር መካከል ያለው ርቀት ምን ያህል እንደሆነ ታውቃላችሁን?» ሲሉ ጠየቁ:- «አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ::» አልናቸው:: «በመካከላቸው ለ500 ዓመታት የሚያስኬድ ርቀት አለ:: በሰማያት መካከል ያለው ርቀትም እንዲሁ 500 ዓመታት ያስኬዳል:: የእያንዳንዱ ሰማይ ውፍረት 500 ዓመታት የሚያስኬድ ነው:: በሰባተኛው ሰማይና በዓርሽ መካከል ባህር አለ:: ጥልቀቱ ከሰማይ እስከ ምድር ያለውን ርቀት ይሸፍናል:: አላህ ከዚያ በላይ ነው:: ከአደም ልጆች ክንውኖች ለርሱ ስውር የሆነ አንድም የለም::» አሉን:: (አቡ ዳውድና ሌሎችም)

## ጠቃሚ ነጥቦች

1. «በትንሳኤ ቀን ምድር በሞላ ጭብጡ ስትሆን» የሚለው ቁርአናዊ ቃል ትርጉም::

2. እነኚህና መሰል የዕውቀት መስኮች በነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) ዘመን ከነበሩ የሁዶች ዘንድ ይታወቁ ነበር:: አልደበቋቸውም:: ሊበርዟቸውም አልሞከሩም::

3. ቁሱ ለነቢዩ (ሶ.ዐ.ወ) የሚያውቀውን በነገራቸው ጊዜ ያንን በማፅደቅ የቁርአን አንቀፅ ወረደ::

4. ቁሱ ይህንን ታላቅ ዕውነታ በነገራቸው ጊዜ ከልባቸው መሳቃቸው ተወስቷል::

5. አላህ እጆች እንዳሉት ተገልጿል:: በዕለተ ትንሳኤ ሰማያትን በቀኝ እጁ፣ ምድሮችን ደግሞ በግራ እጁ ይይዛል::

6. የአላህ እጅ «ግራ» ተብሎ ተገልጿል::

7. አምባገነኖችና ኩራተኞች ተዘክረዋል::

8. «ከአንዳችሁ መዳፍ ላይ ያረፈች የሰናፍጭ ዘር ቅንጣት» የሚለው አገላለፅ ትኩረት ይሻል::

9. ከሰማያት አንፃር የኩርስይ ግዝፈት::

10. ከኩርስይ አንፃር የዓርሽ ግዝፈት::

11. ዓርሽ ከኩርስይና ከውሃው የተለየና ራሱን የቻለ አካል መሆኑ::

12. በሰማያት መካከል ያለው ርቀት::

13. በሰባተኛው ሰማይና በኩርስይ መካከል ያለው ርቀት::

14. በኩርስይና በውሃው መካከል ያለው ርቀት::

15. ዓርሽ ከውሃው በላይ መሆኑ::

16. አላህ ከዓርሽ በላይ መሆኑ::

17. በሰማይና በምድር መካከል ያለው ርቀት::

18. የእያንዳንዱ ሰማይ ውፍረት አምስት መቶ ዓመታት ያክል መሆኑ::

19. ከሰማያት በላይ ያለው ባህር ጥልቀቱ አምስት መቶ ዓመታት ያክል እንደሆነ::

የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ ምስጋናና ውዳሴ ይገባው:: በነብዩ ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ የአላህ እዝነትና በረከት ይስፈን::

ተፈፀመ

# كتاب التوحيد

## الذي هو حق الله على العبيد

تأليف

**شيخ الإسلام محمد بن عبد الوهاب**

ترجمة ونشر

مؤسسة الهلال للنشر والاعلام

الطبعة الأولى: صفر ١٤١٩ هـ

الطبعة الثانية: شعبان ١٤١٩ هـ

ص . ب . : ١٦٠٢٣٩ اديس ابابا

**حقوق الطبع محفوظة**